# ጥበበ ዕንቆ አእባን

## "ከዜና አበውና ከኊልቆ አእባን"

ከመሪራስ አማን በላይ

2012 ዓ.ም.

# ማውጫ

ገጽ

መቅድም ---------------------------------------- 3

ምዕራፍ ፩ ---------------------------------------- 15

አዳም በእግዚአብሔር መልክ እንደምሳሌው ተፈጥሮ ሣለ ትእዛዝን ባለመጠበቁ ከገነት ወደ ምድረ ፋይድ ስለመውረዱና በዋሻ አለት ውስጥ ስለመኖሩ።

ምዕራፍ ፪ ---------------------------------------- 30

እግዚአብሔር የአቤልን መስዋእት ስለመቀበሉና በቃኤል እጅ አቤል ስለመገደሉ ሄኖክ ስለ መመረጡና መጻሕፍትን እንደጻፈ.

ምዕራፍ ፫ ---------------------------------------- 42

ኖህና ልጆቹ ከጥፋት ውኃ ስለመዳናቸው በእግዚአብሔር መልአክ እየተረዳ ስለአጸዋትና ስለ አእባን ምስጢር ስለመጻፉ

ምዕራፍ ፬ ---------------------------------------- 51

መልከጼዴቅ ከአብርሃም ወርቅና እጣን ከርቤም ስለመቀበሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለተከበሩት ድንጋዮች ስለአሳቸው ምስጢር

ምዕራፍ ፭ ---------------------------------------- 62

ጥበበዕንቁ ወአእባን የድንጋዮችና የእንቁ ጥበብ

ምዕራፍ ፮ ---------------------------------------- 187

ተራ ቁጥር ተሰጥቶዋቸው የተመዘገቡት የማእድን ድንጋዮችና እንቁዎች አፈሮችም

# መቅድም

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሁሉን ከእርሱ ለእርሱ ከፈጠረና ከአበጃጀ በኋላ "እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በመልኩ እንደምሳሌው ከምድር አፈር አበጀው"

ከአፈር እንደገል ተበጅቶ ወደ አፈር የሚመለሰው የሰው ገላ የሥጋ አካል ነው፡ ገነር ግን በእግዚአብሔር መልክ እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ ከእግዚአብሔር ምስጢር ስለተፈጠረውና ሰውን ሰው ስለሚያሰኘው ስለ ውስጥ ሰውነቱ አካል በመቀጠል እንደዚህ ይላል፡-

"በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፡ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። ዘፍ. 2፥7"

ስለ ሕያው ነፍስ አካል ምስጢር መግለጽ በመተው እንደ ሸክላ ገል ወደ አፈር ስለሚመለሰውና ስለፈራሹ ስለ ሥጋ ገላ አካል "ወደመጣህበት መሬት እስክትመለስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፡ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለስአለህ፡ ዘፍ. 3፥19" ይላል።

እንደዚሁ ጻድቅ ኢዮብም አለ፡- "ሌላውም ሰው መልካምን ነገር ከቶ ሳይቀምስ በተመረረች ነፍስ ይሞታል፡ በአፈር ውስጥ በአንድ ላይ ይተኛሉ፡ ትልም ይከድናቸዋል፡ ኢዮብ 21፥25"

በበኩሉ ዳዊትም አለ፡- "ፊትህን ስትሰውር ይደነግጣሉ፡ ነፍሳቸውንም ታወጣለህ፡ ይሞታሉም፡ ወደ አፈርም ይመለሳሉ። መዝ. 103፥29"

ሰሎሞንም እስ፦ "ሁሉ ወደ አንድ ቦታ ይሄዳል፡ ሁሉም ከአፈር ነው፡ ሁሉም ወደ አፈር ይመለሳል። መክ.3፥20

እንግዲህ የሰው ልጅ ሁሉ ከዚህ ዓለም አንድ በአንድ እስከሚለይና እስከሚሞት ድረስ እግዚአብሔር "ወደመጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ" ያለውን መለኮታዊ ቃል መሠረትና መመሪያ አድርገን ያስመታከት መሥራት አለብን። የሰራነውንም ሥራ ለተከታዩ ትውልድ አርአያና ምሳሌ እንዲሆናቸው በጥበብ የታገዘ በማስተዋል የተመሰረተ በእውቀትም የተደመደመና ያማረ መሆን አለበት።

ይህም ሥራ ብቻም አይደለም፡ እምነታችን በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ እንዲሆን ጭምር እንጂ፡ ምክንያቱም የሰው ልጅ ያለእምነት በሥራው ብቻ ዓለምን ቢገዛ ፍጻሜው ከንቱ ሆኖ ነው የሚቀር፡ እንዲሁ ያለ ሥራ በእምነት ብቻ እጸድቃለሁ ብሎ ተስፋ ቢያደርጉ ተስፋው ከንቱ ህልም ነው፡ ነገር ግን ሥራ ያለ እምነት እምነትም ያለ ሥራ መጽደቅና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለዘለዓለም መውረስ አይቻልምና፡ ሥራን ከእምነት ጋር እምነትንም ከሥራ ጋር በማዋሐድ ማድረግና መፈጸም አለብን።

እንግዲህ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ከፈጸምን እግዚአብሔር ስለእኛ ደስ ይለዋል፡ እኛም በእግዚአብሔር ቸርነት ጽድቅን ስለሠራን ጻደቅን፡ ጻድቃንንም ሆን፡ በጽድቃችንም እግዚአብሔር ይመሰገናል፡ ይከብራልም፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለዘለዓለም እንወርስ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በመቀበል

በእየሱስ ክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን እምነትን በሥራ ሥራንም በእምነት አናጸናው ዘንድ ከእግዚአብሔር ሥልጣንን አግኝተናል።

ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ እንዲህ ይላል፡- "ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው። ያዕ. 2፥26"

የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሳይፈጽሙ ፈቃዱንም ሳየደርጉ በህጉም ሳይሄዱ፡ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አታንሳ ያለውን ለመቃወም የእግዚአብሔርን ስም በሆነው ባልሆነው በከንቱ እያነሱ በክርስቶስ ስም ክርስቲያኖች ሳይሆኑ ክርስቲያኖች ነን ብለው የተነሱ ሐሰተኞች መምህራን አሉ።

ለዚህ ነው እንደሚመጡ አስቀድሞ እየሱስ ክርስቶስ እንደዚህ ብሉናል፡ "በዚያን ጊዜ ምንም፡- እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢሏችሁ አትመኑ፡ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉና፡ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ፡ እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ፡ ማቴ.24፥23"

እነዚህ የእግዚአብሔር ካህናት ሳይሆኑ ካህናትን በመምሰል እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጥፋትና ስህተት ጋር እንደተስማማ በመቁጠር እግዚአብሔርን እንደነርሱ ሐሰተኛ በማስመሰል፡ የዲያብሉስን ሐሰት አላማ በማንሳት የጥፋት እርኩሰትንም በማውሰብሰብ፡ በረከሰና በቀላ ከንቱ ደም የተለወሰን የኃጢአትን

ልብስ ተከናንበው ከንቱ የሐሰት ፍልስፍናን እንግበው ከየዋሆችና ከእግዚአብሔር ሰዎች ዘንድ ያለን የድካም ዋጋን ነጥቀው የአመጽ ገንዘብ ለማድረግ ከራሳቸው ፍልስፍና ገንዘብ ወዳድነት ብቻ የተነሣ ለዘዴ እንዲህ ይላሉ፡-

"ዓለም ልታልፍ ነው የጌታ መምጫ ደረሰ፡ ስለዚህ የአላችሁን ሁሉ አምጡ፡ አዋጡ ለእግዚአብሔር ስጡ፡ እኛ የእግዚአብሔር መልክተኞች ነን እያሉ በማታለልና በማስፈራራት ይዘርፋሉ ይነጥቃሉ።

የሥራ ውጤት /ምመወዝ/ ዋጋ የሆነውን ገንዘብ ያለ ድካም እንዳልተገኘ በማስመሰል ጽ ኑቅም ያለመልካም ሥራ እንደሚገኝ በማድረግ የሥራቸው ውጤትም ለተከታዩ ትውልድ ምሳሌና አርአያ እንዳይሆን "ዓለም ታልፋለች" ብለው በከንቱ ስብከት ደዌ፡ የሰውን ልብ እንዳደለራም ይገድላሉ። ዓለም ለነርሱ ብቻ ተፈጥራ በነሱ ጊዜ ብቻ ተወስና ሌላው ትውልድ እንደማይተካ ሳይመጣና ሳያያት ሳይኖርባትም እንደምታልፍ ይለፈልፋሉ።

ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ተማምነን የጸናን የአስተዋልንም እንዲህ እንላለን፡- እገሌ ከዓለም ተለየ ስንል ዓለምም ለሞተው ሰው ተለየች አለፈችው ማለት ነው።

ለምሳሌ እየሱስ ክርስቶስ ቃሉን ሰምቶ ለሚያደርገው ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል አብሮት እንደሚኖር ከእርሱ አእምሮ እንደማያልፍ ዳሩ ግን የተፈጠረባት ምድርና ሰማይ ነፍሱ ከሥጋው ከተለየ በኋላ እንደማይኖርባት ተመልሶም

እንደማይመጣበት እንደዚሁ አለን፡ "እውነት እላችኋለሁ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም፡ /ሉተቀበለው በቃሉ ለፀና/ ማቴ. 24፥34"

ሕይወት የሚሰጥ መንፈስ ነው፡ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፡ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው፡ ሕይወትም ነው፡ ነገር ግን ከእናንተ የማያምኑ አሉ። ዮሐ. 6፥63"

ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቀው ቢኖር የምፈርድበት እኔ አይደለሁም፡ የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፡ እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል። ዮሐ. 12፥47" ይለናልና።

እንግዲህ ማንኛውም ሰው በእምነት የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ እየጠበቀ ከዚህ ዓለም እስከሚለይና ዓለምም እስከምታልፈው ድረስ "ወደመጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ" ተብሎ ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ትእዛዝ በመቀበልና መርህ በማድረግ ያለመልካም ሥራ ጽድቅ እንደሌለ በማወቅ መቼ እንደሆነ እያንዳንዱ ሰው የሚሞትበትን ቀን ስለማያውቅ ነገር ግን ከዚህ ዓለም እንደሚለይ አውቆ እግዚአብሔርን በማወቅና በመፍራት በመተማመንም ሥራውን እየሠራ ተዘጋጅቶ መኖር አለበት፡ ያለ ሥራ ጽድቅ የለምና።

ነገር ግን ሥራውን አክብሮ ቢሰራ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደሆነ ያውቃል፡ ያምናልም፡ ቢሞትም በእየሱስ ክርስቶስ

በኩል ሕያው ነው፣ ቢያንቀላፋም ይነቃል፣ ይነግልም፣ የማያልፈውን አዲሱን ሰማይና ምድርን ይወርሳል፣ ከዚያች ቀን በኋላ ዳግመኛ ሞትን አያይም፣ የሚያደክመውም ነገር የለም፣ ተስፋ ሆኖት የኖረው የእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ሕይወት ይሆነዋል።

ስለዚህ በእውነት የኢትዮጵያ ልጆች የሆናችሁ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውት ሁሉ እግዚአብሔር በፍቃዱ ወደ የሰጠንን የጥበብ ጸጋን አስተውለን መመርመርና ማወቅ አለብን፣ የአወቅነውንም በሥራ መግለጽ አለብን፣ እግዚአብሔር የእኛን ሰውነት እንደሚገባ እኛም አገራችንን እንገንባ። አገራችን አካላችን ናትና እኛም የአንድ አካል ብልቶችዋ ነንና ተገጣጥመን በአንድ አካል እንቁም።

እግዚአብሔር አምላካችንን ተከታዩ ትውልድ ስለእኛ መልካም ሥራችንን አይቶ እንዲያመሰግነው ማሳየትና ማስተላለፍ የሁላችን ግዴታና አርአያነት ነው።

ስዚህ የድካማችንን ውጤት የሚገልጸውና ምሳሌ ሆኖ የሚቆየው ከእምነታችን ጋር ሠርተን የምናልፈው መልካም ሥራ ሲኖር ነው። ይህም ሥራ እግዚአብሔር አስቀድሞ የሌሎች ፍጥረቶቹን ተፈጥሮ ባህርያቸውን ለሰው ልጆች እንዲጋሩት እንዲሰለጥኑበትም ፈቅዶ በመስጠቱ ነው። እኛም ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ጸጋንና ሥልጣን አውቀን በማስተዋል ስንመረምር ስራችንም በጥበብ የታገዘ ሲሆን እውነተኛ ሰዎች ያሰኘናል። ሰውን

የሰው ልጅ የሚያስኘው መልካም ሥራው ነው፡ ባለ ሥነ ምግባር የሚያሰኘውም ስለዚህ ነው፡፡

ጥበብ ወደዚህ ዓለም ለሰው ልጆች ከተሰጠች ቆይታለች፡ ነገር ግን ከአንድአንድ ግለሰቦች ስግብግብነትና ምቀኝነት የተነሣ ተደብቃና ተሰውራ ኖራለች፡ አሁን ግን ለሚሻት እየተገለጠችና እየታየች ናት፡፡

የጥበብ መጀመሪያ መሰረትዋ እግዚአብሔርን ማወቅና መፍራት ትእዛዙንም መፈጸም ነው፡ እግዚአብሔርም ለሚፈሩትና ለሚያውቁት የጥበብን መንፈስ ያድላቸዋል፡ ምግባቸውንም ይሰጣቸዋል፡ መኖሪያቸውንም በማስተዋል እንዲገነቡና በእውቀት እንዲሰሩት ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ለምሳሌ አስቀድሜ ስለድንጋይ ቤት አሠራር ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡

1ኛ/ መጀመሪያ የእንጨት ሳንቃዎች በር በሚሆንበት መትከል ከመሐሉ ላይ የእንጨት ግንዶች መከመርና በበላዩ እየተመተሙ ገለባና ሳር መከመር ነው፡ ከዚያ በኋላ የኩበት ቆዳ ማልበስ ነው፡ የውኃ ጉርፍ አምጥቶ ደለል ወይም የላመ አሸዋ ያደረገውን ልም አፈር ከኩብቶች ፍግ ጋር አሽቶ በውኃ ማቡካት ነው፡ በዚህን ጊዜ የጮ የምድር ዝፍት ጭቃ ሲሆን እንደጡብ መጠፍጠፍና ሲደርቅ ለሽከላ የሚሆነውን ቀይ አፈርና የብረት ምክላ አፈር በውኃ አቡክቶ ጭቃውን ከክምሩ ላይ በእለው በኩበት ቆዳ ላይ አስተካክሉ እያስቀመጡ ማነጽና ማሸግ ነው፡፡ ከተደመደመ

በኋላ እንዲሁ ሲደርቅ አሁንም በቀዩ አፈር ጭቃ ከላይ እስከታች ድረስ መምረግ ነው፡

ከዚያ የበሩን ሳንቃ አንስቶ በውስጡ ዲን ነስንሶ በእሳት ማቃጠልና ማሸግ ነው፡ የተከመረው ግንድና ሳር ፍጉም ተቃጥሉ ሲያበቃና ሲበርድ ውስጡን መጥረግ ነው፡ እሳቱ ከበዛበት የድንጋይ ቤት ይሆናል፡ ለሁሉም ጥንቃቄና ስልት ያስፈልገዋል፡፡ ሌላው ደግሞ ተመሳሳይ ሆኖ በገለባው ፈንታ አሸዋ መከመርና ብረት ከሚሆን ከምኮላ አፈር ከቀይ አፈር የተቦካን ጭቃ በተከመረው አሸዋ ላይ የከብት ቆዳ አልብሶ ማነጽና ሲደርቅ እንደገና በበላዩ የጡብ ጭቃ መምረግ ነው፡ እንዳይናድ ተጠንቅቶ ከውስጥ ያለውን አሸዋ አውጥቶ እንጨትና ግንድ ከምሮ ከድንጋይ ከሰል ጋር በእሳት ማቀጠልና ማሸግ ነው፡ እንዳይቀልጥ እሳቱ አይብዛበት ከበዛበት የድንጋይ ቤት ላዩ ድቡልቡል ከብ ከሆነ እንቁላል ህንጻ ይባላል፡፡

2ኛ/ የጡብ ቤት ለመሥራት የምድሩን ዝፍት ከከብት ፍግ ጋር እያቦኩ ባለአራት ገጽ /ጣውላ/ ለሴዳ እየተመተሙ መጠፍጠፍ ሲደርቅ ከምሮ እሳቱ ሳይበዛ አቃጥሎ መተኮስ ነው፡ ከዚያ ጡብ ድንጋይ ይሆናል፡፡

3ኛ/ የጭቃ ቤት የሚባለው ጭቃውን ከገለባ ጋር አቡክቶ መጠፍጠፍና ሲደርቅ እንደጡብ ግንብ መገንባት ነው፡፡

ይህ የጭቃ ቤት አሠራር በጉጃም ውስጥ በጎዣምና በማቻከል የተሠሩ አብያተ ክርስቲያኖችና ባድማዎች እስከአሁን

ድረስ አሉ፡ እንዲሁ በሱዳንና በሌሎች አገሮች ቤታቸውንና አጥራቸውን እንደጡብ ሆኖ በተጠፈጠፈ ጭቃ ይሠራሉ።

4ኛ/ የምድር ቤት ደግሞ በምሥራቅ ሰሜን ኢትዮጵያ በአፋርና በሌሎች ቦታዎች ጭንጫና አሸዋ ከሆነው መሬት ላይ ቆፍረው ጉድጓዱን ከታች ጀምረው ይገነቡታል፡ ከምድር ወለል ሲደርስ ጠንካራ የሆኑትን የዛፍ ግንዶች በውጋግራ ይሁን ያለውጋግራ አመሳቅለው ያጋድሙአቸዋል፡ በበላይ ጭራሮ እንጨት ከተደረደረ በኋላ ቀይ አፈር የከብት ፍግ ይደለድሉበታል።

በበሩ በኩል በክረምት የውኃ ጐርፍ ድንገት እንዳይገባ ጉብታ እንዲኖረው ያደርጋሉ፡ ይህ የምድር ቤት በሙቀት ጊዜ በጣም የቀዘቀዘ ነው።

ይህ የምድር ቤት ለአንግዶችና ለአላፊ መንደኞች አይታወቅም፡ የእነዚህ ዓይነት ቤት አሠራር ብዙ ሺህ አመታቶች አስቆጥሮአል፡ ነገር ግን የሚበልጡት በምድር መናወጥ ተደምስሰዋል።

ሌላው ስለሐውልት አሠራር ጥበበ ዕንቁ አእባን ከተባለው ምዕራፍ ላይ ስለተዘረዘረ መተንተኑ አስፈላጊ አይደለምና ወደ ቅዱሱ ታሪክ እንመለስ። "ንጉሥ ዳዊት ለጉባኤው ሁሉ እንዲህ አለ፡- እኔም እንደጉልበቴ ሁሉ ለአምላኬ ቤት ለወርቁ እቃ ወርቁን ለብሩ እቃ ብሩን ለናሱ እቃ ናሱን ለብረቱ እቃ ብረቱን ለእንጨቱ እቃ እንጨቱን ደግሞም መረግድንና ለፈርጥ የሚገባ ድንጋይን የሚለጠፍ ድንጋይን ልዩ ልዩ መልክ ያለውንም ድንጋይ

የከበረውንም ድንጋይ ከየአይነቱ ብዙም እብክበረድ አዘጋጅቼአለሁ፡ 1/ዜና መ.ቀ.29፥2

አንቺ የተቸገርሽ በአውሎ ነፋስም የተናወጥሽ ያልተጽናናሽም እነሆ ድንጋዮችሽን ሸላልሜ እገነባለሁ፡ በሰንፔርም እመሠርትሽ አለሁ፡ የማንበሽንም ጉልላት በቀይ ዕንቁ በሮችሽንም በሚያብረቀርቅ እንቁ ዳርቻሽንም ሁሉ በከበሩ ድንጋዮች አሠራለሁ። ኢሳ. 54፥11

ይህ ሁሉ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለፈጠረውና ወደፊት ለሚሆነው ሁሉ ምሳሌና ምስጢር ነውና፡ "ዘአንሶሰው ከመ ያመጽእ እሳተ እምዓለመ ኮሬብ፡ ወመሬተ እምዓለመ ዱዳሌብ፡ ወማየ እምዓለመ ናጌብ፡ ወነፋሰ እምዓለመ አዜብ፡ ወእመ ሰፈራ ለዛቲ ዓለም በመደልው ይከውን ኩሉ ፍጥረት በቅድመ እግዚአብሔር ከመ ነጥብ"

እግዚአብሔር የአለንባትን ዓለም የዓለም ሐብት የሆኑትን አፈሩንና ድንጋዩን በምድሩዋ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ከመፍጠሩ በፊት ልምድድና ተንቀሳቃሽ ቃጠሎነት የአለውን እሳትን ከኮሬብ ዓለም፡ የረጋውንና ከባድ የሆነውን የምድርን አፈር ከዱላሌብ ዓለም፡

እንደ መስታዋት የጠራውንና ፈሳሽና ቀዝቃዛ የሆነውን ውኃን ከናጌብ ዓለም፡

ተንቀሳቃሽ ከመሆኑ የተነሣ የሚጋፋውንና የረቀቀውን ነፋስን ከአዜብ ዓለም፡

እንስቶና አቀላቅሉ እዋህዶም በአራቱ ባህርያት ዓለማችንን ፈጥሮልናል፣ ምድራውያን እንባል ዘንድ እኛንም ዓለምን ከፈጠረ በኋላ ፈጥሮናል።

ስለዚህ ዓለማችን በተፈጠረችበት አራት ባህርያት ማለት ከእሳት ከአፈር ከውኃ ከነፋስ የሥጋ አካላችንን ስለፈጠረ ያለነሱ በዚህ ዓለም ላይ መኖር አንችልም። እንዲያውም በእነሱ ላይ ስልጣን እንዲኖረንና ባህርዮቻቸውን እንድንጋራቸው ስለአደረገ የሰው ልጆች እግዚአብሔር በፈቀደልንና በሰጠን ጸጋ መጠቀም አለብን፣ እስተውለንም መመርመርና ማወቅ ነው እንጂ የሰነፎችን አሳብና ምክር ተቀብለን ከጥበብ ሥራ መራቅ የለብንም። ለዚህ ነው መጽሐፈ ጥበበ ዕንቆ እእባንን ለምወዳችሁና መልካም ነገር ለምመኝላችሁ ለኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ መልካም አስተሳሰብ እንዲኖራችሁ ከዜና አበውና ከትልቆ አእባን መጽሐፍቶች ውስጥ አስፈላጊውን መርጬ ጽፌ አሳትሜላችሁ አለሁ፣ ደርሷችሁም ልታነቡት የሆነው የእግዚአብሔር ፍቃድና ቸርነቱ ስለተጨመረበት ነው። አሁንም ታስተውሉና ትመረምሩ ዘንድ የጥበብንም ምስጢር ታውቁና ትገልጹ ዘንድ የእግዚአብሔር ጸጋና እርዳታ አይለያችሁ፣ ተባብረንና ተከባብረን በአንድ ላይ እናት አገራችን ኢትዮጵያን ከድህነት ኑሮ አውጥተን ከንቱነትንና ውሸትን ከእኛ አጥፍተን በዘመናዊ ጥበብ ጉዳና ወደ እድገትና ወደ ብልጽግና ሕይወት ለማሻገርና ለማድረስ እግዚአብሔር ያብቃን፣ አሜን ይሁንልን። ይህ መጽሐፈ ጥበብ ዘእንቆ እእባን ሊጻፍና ታትሞ ለእናንተ

ለኢትዮጵያውያን ሊደርስ የቻለው ወይዘሪት ሔለን ሙላት ስለቸኝ ደከመኝ ሳትል በኮምፒዩተር ጽሁፍና ኤዲቲንግ አድርጋ ስለ አዘጋጀችልኝ የእግዚአብሔር አብ ቸርነት የወልድ እርዳታ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የድንግል ማርያም በረከት አይለያት አሜን።

ከመሪራስ አማን በላይ

2003

## ምዕራፍ ፩

### አዳም በእግዚአብሔር መልክ እንደምሳሌው ተፈጥሮ ሣለ ትእዛዝን ባለመጠበቁ ከገነት ወደ ምድረ ፋይድ ስለመውረዱና በዋሻ እለት ውስጥ ስለመኖሩ።

ዘመኖችና የዘመኖች መለያቸው ዓመት ሳይጀመርና ሳይቆጠር ወቅቱና የወቅቱ መታወቂያ የወር ስም ሳይሰጠውና ሳይታወቅ ጊዜውና የጊዜው መለኪያ ሌሊትና ቀኑ ሳይፈራረቅ ለቀኑም ስም ሳይወጣለትና ሳይሰጠው በመለኮቱ ምልአት አንድ አምላክ ብቻ የሆነ እግዚአብሔር ነበረ።

እግዚአብሔርም ከአንድነቱ መለኮት ምልአትና ባህርይ ሳይከፈል በሦስት አካላት ሳይቀዳደምና ሳይበላለጥ የነበረ ዛሬም የአለ ለዘለዓለም የሚኖር እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ማለት ቸሩ አባት ጌታ ማለት ነውና እርሱ የፍጥረት ሁሉ አባት ለፈጠረው ሁሉ ሕይወት እንዲኖረው የአደረገና ቸር ሆኖ የለገሰ፡ የፍጥረት ሁሉ ባለቤትና ጌታ የሆነ፡ ያልነበረውም እንዲኖር ፍጥረታቱን ሁሉ የጀመረና የፈጠረ፡ ለፈጠረው ሁሉ መኖሪያውን የአዘጋጀ፡ አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡ ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ፈጣሪና ጌታ የለም።

እግዚአብሔር ከመጀመሪያው ፍጥረቱ ላይ ርእዮተ ዓለማት የሆኑትን አየራትንና ሰማያትን የአለንባትንም ምድር እንዲሁ በውስጣቸው የአሉትን ሠራዊታቸውን ሁሉ ያለድካምና ያለ

መታከት በእግዚአብሔር ቃል ለእግዚአብሔር መንፈስ ከእግዚአብሔር ፈጠራቸው፡ የክብሩ መግለጫ ናቸውና።

እግዚአብሔርም በፈጠራቸው ፍጥረቶቹ ዘንድ ፈጣሪነቱን ለመግለጽ ክብሩንም ለማሣየት ብርሃን እንዲሆናቸው በፊታቸው ላይ ዓይንን ገለፀላቸው፡ ዓይን ለአካል ብልቶች ሁሉ ብርሃን ነውና።

እግዚአብሔርም ስሙን ለማሳወቅና የፍጥረቱ ሁሉ ባለቤትና የምስጋና ጌታ መሆኑን ታምኖበት እንዲመሰገን ሲል ገደብ የለሰው ነጻ አእምሮ ለፍጥረቱ ሁሉ ሰጥቶ በደማዊ ነፍሳቸው ላይ የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለባቸው።

በምድር ላይ ለሚንቀሳቀሱትና ለሚሳቡት ለሚሄዱትም በውኃ ላይ ለሚንሳፈፉትና ለሚራወጹት በአየር ላይም ለሚበሩት ፍጥረቶቹ ሁሉ እንደየድርሻቸው ሕያውነት የለሰው ልባዊ ነፍስን አደላቸው፡ በተሰጣቸው ልቡናም ያውቃሉና። የሕይወት እስትንፋስና ልባዊ ነፍስ ከተሰጣቸው ፍጥረቶቹ መካከል አንዱ የፍጥረት መደምደሚያ የሆነው በምድር ላይም ነግሶ እንዲሰለጥንባት የተፈጠረው የመጀመሪያው ሰው አድማኤል ነው።

እግዚአብሔር አዳምን ሲፈጥር "እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር፡ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዙ፡ እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረው፡ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። ዘፍ. 1፥26"

እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረ ቀን በእግዚአብሔር ምሳሌ አደረገው፡ ወንድና ሴት አድርጐ ፈጠራቸው፡ ባረካቸውም ስማቸውንም በፈጠረበት ቀን አዳም ብሎ ጠራቸው። ዘፍ. 5፥2"

እግዚአብሔር የመጀመሪያውን የሰውን ስም በሰየመበት ቃል እስከ አሁን ድረስ አዳም መልካም ነውና፡ በግእዙ ሕዝብ- አህዛብ የሚሰውን በአማርኛችን ቋንቋ አዳሙ-አዳሜ ይላል ይሄም የብዙዎች አባት አዳም ነውና።

ሰውም በእግዚአብሔር መልክ የእግዚአብሔር ምሳሌ ሆኖ በእግዚአብሔር ቃል ለእግዚአብሔር ክብር የእግዚአብሔርንም መልክ ተሰጥቶት ስለተፈጠረ በመጀመሪያው የሰው ልጆች ቋንቋ አድማኤል ተባለ።

አድማኤል ማለት የእግዚአብሔርን መልክ የያዘ ወይም የተቀባ መልከ መልካም ማለት ነው።

እግዚአብሔር አድማኤልን የፈጠረበት ምድር አፈር በሱባ ኤልዳ ይባላል፡ ትርጉሙ የእግዚአብሔር ፍጡር ማለት ነው፡ ኤል፡- መፍጠር ዳ፡- የረጅም ጊዜ።

እግዚአብሔር አዳምን ከኤልዳ ምድር አፈር አንስቶ ሲያበጀው ከእሳት አንድ እጅ ከአፈር ሁለት እጅ ከውኃ ሶስት እጅ ከ.ፋስ አራት እጅ አቀላቅሎና አዋህዶ የአዳምን አካል ሥጋ አበጀው።

እግዚአብሔር በእበጀው በሥጋው አካል ላይ በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት፣ ፈጠረበት ሰውም ሕያው ነፋስ ያለው ሆነ።

ሕያው ነፍስም በእግዚአብሔር መልክ ለእግዚአብሔር ምሳሌ ትሆን ዘንድ የአእምሮ ልባዊነትን አንድ እጅ ነባቢነትን /ቋንቋ/ ሁለት እጅ የዘለዓለም ሕያዊነትን ሦስት እጅ፣ የሚያንቀሳቅስና የሚያስተነፍስን ከምድራዊነት ወደሰማያዊነት የሚነጠቀውና ለዘለዓለም የሚኖረውን እስትንፋስን በማይፈርስና በማይበን በረቀቀ አካል መልክ ስሥጋ የውስጥ ሰውነት አድርጎ በመዋሐድ ፈጠራት /ፈጠረው/

አድማኤል በኤዶም ገነት የፈጠረውንና በምድር ላይ የአነገሰውን እግዚአብሔርን እያመሰገነ በነገሠባቸውና በሠለጠነባቸው በምድር ሠራዊት ላይ አለቃ ሆኖ እንደ እኛ አቆጣጠር 2,556,000 ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ አምሳ ስድስት ሺ ዓመታት ሕይወት ተቀምጧል።

አድማኤልም ሕያው ነፍስና ደማዊ ነፍስ ላለው ሁሉ በሱባ ቋንቋ ስም አወጣላቸው፣ በየስማቸውም ጠራቸው፣ ስማቸውም አድማኤል እንደሰየመላቸው ሆነ፣ ሱባ ማለት በአማርኛ ሰው ሲሆን በግእዙ ሰብእ ይለዋል።

እግዚአብሔር ለአዳም በሰማይ በታችና በምድር ስልጣን እንደሰጠውና የፈለገውን እንዲበላና እንዲጠጣ ነገር ግን ፍጡር መሆኑን እንዲያውቅና ፈጣሪውን እንዲያመሰግን የሕግ ሥርአት

ይሆነው ዘንድ ከገነት መሃል አንዲትን እንጨት እንዳይበላ አዘዘው። አትብላ ትእዛዝ፣ የበላህ እንደሆን ትሞታለህ፤ ህግ ነውና፤

"እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ነገር ግን መልካምንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና። ዘፍ. 2፥16"

"ይቤሎ እግዚአብሔር ለአቡነ አዳም ወንብኩከ መንግሥተ ዘበምድር ኢትህስስ መንግሥትየ ወኢትባእ ውስተ መንበረ ስብሐትየ አስመ ወሀብኩከ ዘታሁተ ሰማይ ወዘላዕለ ምድር ዘአጥረይኩ ለከ በከመ ፈተወ ልብከ ብላዕ ወስተይ ባሕቱ ኢትብልዓ ለይእቲ ዕፅ ወለእመ ተአጸውከ ትእዛዝየ ወእመ በላዕከ እምኔሃ ትመውት ዓቢየ ሞተ በምድር ወበሰማያት ወእምዝ አዘዝኩከ ኢትህልፍ"

እግዚአብሔር አዳምን በሰማይ በታች በአሉት ፍጥረት ላይ እንዳነገሰውና በኤደም እንዳስቀመጠው ግን አንዲት እንጨትን እንዳይበላ እንዳዘዘው እንዲህ ይላል።

"ገብር ሰብአ በአርያ ያኤምር፡ ኃበሥላሴሁ በአርያነሂ ወበአምሳሊነ ዘደቤ በእንተ አእምሮቱ ወበእንተ ፈሊጦቱ ሠናየ እምኩይ ወበእንተዝ ረሰዮ ንጉሠ ወእግዚአ ላእለ ኩሉ ፍጥረት በታህተ ሰማይ ወእምዝ አንበሮ ውስተ ገነት ኤዶም ወይቤሎ እምኩሉ እፅ ዘሀሉ ውስተ ገነት ብላእ ዘእንበለ ዕፅ ባሕቲታ፤

ዘከልአመሙሰ አኮ እምፍናቲቅየ አላ ያእውቆ አምላክናሁ" እንዳለ መጽሐፈ. ዜና አዳም የመጀመሪያው 1ኛ ትእዛዝ አትብላ ነው፤ 2ኛው በተሰጠው ነጻ አእምሮ የፈቀደውን ያደርግ ዘንድ አትብላ የተባለውን ትእዛዝ ረስቶ ከበላ በሞት ይቀጣል፤ ይህም የመጀመሪያ ህግ ነውና ከብዙ ሺህ አመታቶች በኋላ እንደዚህ ሆነ፤

አዳምና ሄዋን በገነት ኤደም መካከል እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በደስታና በተድላ ይኖሩ ነበር፡ መልካቸውም እንደ እንቁ ድንጋይ የአበራ ነበር፡ ውበታቸው ያማረ ነበረ፡ እግዚአብሔር በሰጣቸው ጥበብም ከብረው ነበር፡ ነገር ግን ከክብሩ ከተዋረደው ከዲያብሎስ ጋር በአባብ በኩል አሳብ ተሰዋውጠው የእግዚአብሔር ክብር መግለጫና ቅዱስ ስሙ የሚመሰገንበትን የውስጥ ሰውነታቸውን መቅደስ ባለመታዘዝና ትእዛዛትን ባለመፈጸም አረከሱ፡ ከሕይወት ይልቅ ሞትን ከክብር ይልቅ ውርደትን ከደስታ ይልቅ መከራን ከድሎት ይልቅ ጉስቁልናን መረጡ፡ በዘመናቸው የሚቅበዘበዙና የሚጨነቁ ሆኑ፡ ምክንያቱም በሰይጣን ምክር ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ወጥተዋልና።

"ወሶሉ አዳም ወሄዋን ይትአጸፉ ብርሃነ ዘያበርህ አምፀሐይ ወሰብ ርእየ ሰይጣን እበየ ክብርሙ ወፍሰሐሆሙ ቀንዓ ላእሌሆሙ ወተሠመረ ውስተ ሥጋ ከይሲ"

ነቢዩ ሕዝቅኤልም በዘመኑ በምድር ላይ ታውቆና ተከብሮ በነበረው በጢሮስ ገዢ አስመስሎ ስለአዳም ሕይወት ታሪክ በቅኔ ትንቢት ወይም በእንቆቅልሽ መሶ አምላክ እሆናለሁ ብሎ እፀ በለስን ስለመብላቱ፡ እንዲህ ሲል ተናግሮለታል፡-

"እኔ አምላክ ነኝ በእግዚአብሔር ወንበር በባህር መካከል ተቀምጫለሁ ብለሃል፡ ነገር ግን ልብህን እንደ እግዚአብሔር ልብ ብታደርግም አንተ ሰው ነህ እንጂ አምላክ አይደለህም።

እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ ፈጥሮ በመጨረሻው የፍጥረት መደምደሚያ ራስ ይሆን ዘንድ እንደ ተፈጠረና

የእግዚአብሔርን መልክ ጥበብና የውበቱ ምሳሌ ሆኖ የተፈጠረው አዳም እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበትን የውስጥ ሰውነቱን መቅደስ ስለማርከሱ በሕዝቅኤል አፍ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡

"የሰው ልጅ ሆይ በጢሮስ ንጉሥ /አዳም/ ላይ ሙሾ /ቅኔ/ አሞሽተህ እንዲህ በለው፡ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ጥበብን የተሞላህ ውበትህም የተፈጸመ መደምደሚያ /እርብ ቀን ስለተፈጠረ/ አንተ ነህ።

በእግዚአብሔር ገነት በዔድን /ኤዶም/ ነበርህ የከበረ ዕንቁስ ሁሉ ሰርድዮን፣ እንቆጳዝዮን፣ አልማዝ፣ ቢረሌ፣ መረግድ፣ ኢያስጲድ፣ ሰንፔር፣ በሉር፣ የሚያብረቀርቅ እንቁ ወርቅ ልብስህ ነበር፡ የከበሮህና የእንቢልታህ ሥራ በአንተ ዘንድ ነበረ፡ በተፈጠርህበት /እርብ/ ቀን ተዘጋጅተው ነበር፡ አንተ ልትጋርድ የተቀባህ ኪሩብ /መላአክ አድማኤል/ ነበርህ በተቀደሰው በእግዚአብሔር ተራራ /በአርያም ገነት/ ላይ አኖርሁህ፡ በእሳት ድንጋዮች መካከል ተመላለስህ፡ ከተፈጠርህበት ቀን ጀምረህ በደል እስኪገኝብህ ድረስ በመንገድህ ፍጹም ነበርህ፡ በንግድህ /ከሰይጣን ጋር በአደረገው ግንኙነት/ ብዛት ግፍ /ምክር/ በውስጥህ ተሞላ፡ ኃጢአትንም ሠራህ ስለዚህ እንደ ርኩስ ነገር ከእግዚአብሔር ተራራ /ከአርያም ኤዶም/ ጣልሁህ፡ የምትጋርድ ኪሩብ ሆይ /አድማኤል/ ከእሳት ድንጋዮች መካከል /ከመላእክት መካከል/ አጠፋሁህ፡

በውበትህ ምክንያት ልብህ ኮርቶአል ከክብርህ የተነሣ ጥበብህን አረከስህ፡ በምድር ላይ /ወደተፈጠረበት አፈር/ ጣልሁህ፡

ያዩህም ዘንድ በካህናት /ካቢያትና ኃጥርያት ቅዱሳን/ ፊት ሰጠሁህ፡ በበደልህ /ባለመታዘዝህ/ ብዛት በንግድህም /በሰይጣን ምክር በመሄዱ/ ኃጢአት መቅደስህን /የእግዚአብሔር መቅደስ የሆነው የውስጥ ሰውነታችን አካል ነውና/ አረከስህ፡ ስለዚህ እሳትን /መከራና ሥቃይን/ ከውስጥህ አውጥቻለሁ/ እርሱዋም በልታሃለች፡ በሚያዩህ ሁሉ ፊት /የአዳምን አለመታዘዝ በሚያውቁ ሁሉ/ በምድር ላይ አመድ አድርጌሀአለሁ /አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ/ በአህዛብም ውስጥ የሚያውቁህ ሁሉ /የአዳም ዘር ሁሉ/ ይደነቁብሃል፡ አንተም ለድንጋጤ /ለአዳም በደል ሁሉ አፈር ሆን፤ አዳም ባመጣው ሞት የማይደነግጥ የለምና/ ሆነሃል፤ እስከ ዘለዓለም /የሥጋ አካሉ አፈረ ነውና/ አትገኝም፡፡ ሕዝ.28፥12-20"

አዳምና ሔዋን አትብሉ የተባሉትን ትእዛዝ ባለመፈጸም ከእርሱ በበላችሁና በነካችሁትም ጊዜ ሞትን ትሞታላችሁ የተባሉትን ህግ በመጣስ ከገነት ወደ ምድረ ፋይድ ወረዱ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የህግ ቅጣትና ሞት በአዳምና በሔዋን ተጀመረ፡፡ አዳምና ሄዋን ከገነት ወጥተው ወደ ምድረ ፋይድ በደረሱና እንደ ወህኒ ቤት በአለት ዋሻ ውስጥ በተቀመጡ ጊዜ በጣም ደነገጡና ፈሩ፡ ምድርን አይተው አሸዋውንና ድንጋዮችን ተመልክተው "ወአዘዘ እግዚአብሔር ለአዳም ከመ ይሀድር ውስተ በዓተ ኰኵሕ ዘይእቲ በዓተ መዛግብት ታሁተ ገነት፡ አዳም ወሔዋን በወአተው እምገነት ኪዱ በእገሪሆሙ ወኢየአምሩ ዘይከይዱ፡ ወሶበ በጽሑ አፍአ እንቀጸ ገነት፡ ነጸርዋ ለምድር ዘፍሕት ቅድሜሆሙ ወእአብን ዐቢያን ወሆሣት ንዑሳን ፈርሁ ወርዕዱ ወወድቁ በገጸሙ እምፍርሀት..."

የአዳምንና የሔዋንን ሐዘንና በደልን እግዚአብሔር ተመልክቶ አዲስ የተስፋ ቃል ኪዳን በአደረገላቸው የተስፋውም ኪዳን በሔዋን ምክንያት ስመጣው በደል በሴት ልጅ በኩል ያ፡፡ወንድ ዘር ተፀንሶና ሥጋን ተዋህዶ የሰው ልጅ ሆኖ እንደሚወለድና በእንጨት ተሰቅሎ ሞትንም ሞቶ ሞትን ድል እንደሚያደርገውና የአዳምን ዘር ሁሉ ከሲኦል ወደገነት እንደሚያስገባለት ነገረው፡፡ እንዲሁ ከትንሣኤ በኋላ ሕያዋን የሆኑትን የሔዋንን ልጆች ብቻ እንደሚመርጣቸው ነገረው፡፡

የተስፋው ቃል ኪዳን ከመጀመሪያው ቀን ከእሁድ እስከ አርብ ምግሽ ቀን ድረስ ይሆናል፡ በእግዚአብሔር አምስት ቀን ተኩል ማለት ነውና፡፡

"ኦ አዳም አትቤዘወከ እምድህረ ሐሙስ እለት ወበመንፈቃ ሰመእልት እወርድ እምሰማየ ሰማያት ወእሀድር ውስተ ከርሰ ድንግል እምወሉተ ወለትከ ወእትወለድ ከመሕፃን" ሆንሽዋ /የሠራዊት ክቡር ጌታ/ በተባለው በመጽሐፈ ዜና አበው ደግሞ እንደዚህ ይላል፡ "ይቤ እግዚአብሔር ለአዳም አነ ሠራዕኩ ላእለ ዝንቱ ምድር እለታተ ወአመታተ ትሄሉ፡ አንተ ውስቴታ ወታንሶሱ እስከ ጊዜ ተፍጻሜተ እሙንቱ ዓመታት ወእለታት እፌኑ ቃልየ ዘፈጠረከ፡

ወተአጸውከ ወውእቱ ዘአውጽአከ እምገነት ወሶበ ወደቀ እንሥእከ ወውእቱ ካዕበ ዘያድህነከ በተፍጻሜተ እምስቱ ዕለት ወመንፈቅ ወሶበ ሰምአ ዘንተ ቃለ እም እግዚአብሔር ተናዘዘ ቦቱ፡ በነገረ እግዚአብሔር እስመ ውእቱ ያድህኖ፡ ኦላ አዳም ወሔዋን በከዩ በእንተ ፀአቶሙ እምገነቶሙ ቀዳማዊ፡

አዳም ይቤላ ለሔዋን ነጽሪ ዘንተ በዓተ ዘኮነት ለነ ቤተሞቅህ በዝንቱ ዓለም ወመከነ ዝብጠት አይቴ ዛቲ እምገነት አይቴ ዝንቱ ጸባብ እምውእቱ ርሂብ አይቴ ዝንቱ ኩኩህ እምውእቶን አዕፃዳት አይቴ ዝንቱ ጽልመት ዘውስተ ዝንቱ በዓት እምብርሃን ገነት አይቴ ተድበበ ዝንቱ በዓተ ኩኩህ፡ እምሕረተ

እግዚአብሔር ዘንተ ትጸልል ላዕሌነ አይቴ ምድር፡ ዝንቱ በዓት እምድረ ገነት ዛቲ፡ ምድር ዝርዕት በአእባን ወይእቲሰ ዝርዕት በዕፀ ፍሬያት ጥዑማት።

አዳምና ሔዋን ከገነት ወደዚህች ምድረ ፋዳ በወረዱ ጊዜ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደታቦት ድንጋዮች ወስደው አስቀመጡና በበላያቸው ላይ ቅጠል አልብሰው ደማቸውን አፈሰሱበትና ጌታ ሆይ በደላችን ይቅር በለን ብለው ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ።

"ወካዕበ ነሥኡ አዳም ወሔዋን አእባነ ወአንበርዎሙ በአምሳለ ታቦት ወነሥኡ አቈጽለ እምዕፀው አፍአ ገነት ወመዘመዙ በሙ ደሞሙ እምላዕለ ኵኩህ ወዘነጥበ ላዕሌሁ ነሥእዎ ምስለ መሬቱ ወአእረግዎ ላዕለ ታቦት ወከመ ቍርባን ለእግዚአብሔር፡

ወቆሙ አዳም ወሔዋን ታህተ ሓይከል ይበክዩ ወይሀሥሡ እም እግዚአብሔር እንዘ ይብሉ፡

እግዚአ ሥረይ ለነ አበሳነ ወኃጢአትነ ወነጽረነ በዓይነ ምህረትከ፡ - -

ወይእዜኒ ነጽር ላዕሌነ ደመነ ዘውሩግ ላዕለ አእባን ወተወከፍ እምኔነ በአምሳለ ስብሐታት ዘገነ ንገብሮሙ ለከ ቀዳሚ በውስተ ገነት፡ - - -

ወመጽአ ቃለ እግዚአብሔር ኃበ አዳም ወይቤሎ እ አዳም በከመ ከዓውከ ደመከ ከመዝ እነ እከዑ ደምየ

ሶበ እሠጋ እምዘርእከ ወበከመ ሞትከ እ አዳም ከመዝ እነ እመውት ወበከመ ሐነጽከ ምሥዋዐ ወበከማሁ እነ እሬሲ ሊተ ውስተ ምድር ምሥዋዐ ወበከመ አእረገ ደመከ ላዕሌሁ ከማሁ አዓርግ ደምየ ላዕለ ምሥዋዕ ውስተ ምድር ወከመ ኃሠሥከ ሥርየተ በዝንቱ ደም ለሥርየ ኃጢአት ወእደመስስ አበሳተ በቱ ወይእዜኒ - - - ናሁ ተወከፍኩ ቍርባነከ - - -

እግዚአብሔር ለአዳም ወርቅና እጣን ከርቤ እንደሰጠው ምስጢሩም፡- ወርቁ የመንግሥቱ፣ እጣኑ የመለኮት ባህርዩ፣ ከርቤው የሕመሙና የሞቱ ምሳሌ ሆነው ቀርበውለታል።

ይቤሎ እግዚአብሔር ለአዳም ኦ አዳም ኃሠሥከ እምኒየ ግብረ እምነት ከመ ትትናዘዝ ቦቱ ወናሁ ወሀብኩከ ለከ እሉንተ ሠለሥተ ትእምርታተ ከመትኩን ዘትትናዘዝ ቦሙ ወትእመን ብየ በኪዳንየ ለሊከ እስመ እነ እመጽእ ወአድሀነከ ወያመጽኡ ሊተ ነገሥተ ተርሴስ ወአፋር ወነገሥተ እንቈጵጵ በሥጋዌየ ወርቀ ወእጣነ ወከርቤ። ወርቅሰ ትእምርተ መንግሥትየ ወእጣን ትእምርተ መለኮትየ ወከርቤ ትእምእርተ ሕማምየ ወሞትየ።

ኦ አዳም ረሲ እሉንተ ኅቡከ ውስተ በአት ከመ ይኩን ወርቅ ዘያጸድል ላእሌከ በሌሊት ወእጣን ከመ ታጼኑ ዔናሁ ወከርቤ ይናዝዘከ እምኃዘንከ፡

ወሶበ ሰምአ አዳም ቃለ እምእግዜአብሔር ሰገዱ ቅድሜሁ ስብሀም ወአእኮትም በእንተ ዘገብረ ምስሌሆሙ እምሀረት፡

በአዳምና በሔዋን ላይ ሰይጣን ለሠራዊቱ ድንጋይ ከተራራ እንዲጥሉባቸውና እንዲሞቱ አዘዘ፡ ነገር ግን የእንከባለሉባቸው ቤባን የተባለ ድንጋይ እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን መጠጊያ አዳራሽ እንዲሆናቸው እንጂ እንዲገድላቸው አላደረገም፡ እንደቤት ሆኖላቸው በዚያም ኖሩ።

ሰይጣን ይቤሎሙ ለሠራዊቱ ንሥኡ ዘንተ ኰኵሓ ወውግሩ ላእሌሆሙ በዕሩይ ከመ ኢትሁር እምላእሌሆሙ ኅበጽንፈ ኳሕፅ ወሶበ ወገርክምዎ ላእሌሆሙ ጉዩ ወኢትቁሙ፡ ወገብሩ በከመ አዘዞሙ ወሶበ ትወርድ ኰኵሕ እምደብር፡ ላእለ አዳም ወሔዋን አዘዘ እግዚአብሔር፡ ለእብንቢጣን ከመ ትኩን ለአዳም ወሔዋን በአምሳለ ደብተራ ቤተጽርህ ወኢታህሥምሙ ወከነ ከመዝ በትእዛዘ እግዚአብሔር።

እየሱስ ክርስቶስ ስለ አዳም በአጋንንት ወንበዴዎች ስለመደብደቡና የእግዚአብሔር ካህን መልከ ጼዴቅ እንዳላዳነው ከእርሱ ቀጥሎ የሌዊ ዘር ሙሴም እንዳላዳነው ነገር ግን እራሱን

በተናቁት ሳምራውያን መስሎ እንዴት እንዲአዳነውና ምህረት እንዳደረገለት እንዲህ ሲል በምሳሌ አስተምሮናል፡-

"አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም /ስማያዊት/ ወደ ኢያሪኮ /ይህች ዓለም/ ወረዳ በወንበዴዎችም /ሰይጣናት/ እጅ ወደቀ፡ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት /ክብሩን/ ደበደቡትም፡ በሕይወትና /በነፍሱ/ በሞት /በሥጋው/ መካከልም ትተውት ሄዱ፡ ድንገትም አንድ ካህን /መልከጼዴቅ/ በዚያ መንገድ ወረደ አይቶትም ገለል ብሎ አለፈ፡ እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌዋዊ /ሙሴ/ ወደዚያ ስፍራ መጣና አይቶት ገለል ብሎ አለፈ። አንድ ሳምራዊ /ኢየሱስ/ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ፡ አይቶትም አዘነለት፡ ቀርቦም ዘይትና /ቅባአቅዱስ/ የወይን ጠጅ /ደሙ/ በቁስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው /የአዳም በደሎች/ በራሱ አህያም /ዓለም/ ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማደሪያ /እስከ እለተምጽአት/ ወሰደው ጠበቀውም፡ በማግሥቱም ሁለት ዲናር /ብሉይና ሐዲስ ኪዳን/ አውጥቶ ለባለቤቱ /መለኮት ባሕርዩ/ ሰጠና፡ ጠብቀው ከዚያም በላይ የምትከስረውን ሁሉ /ሰማእታት/ እኔ ስመለስ እከፍልህ አለሁ አለው። እንግዲህ ከነዚህ ከሦስቱ በወንበዴው እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል፡ እርሱም፡- ምሕረት ያደረገለት አለ /ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ምህረትን የሚያደርግ የለም/ ኢየሱስም፡- ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ አለው። ሉቃ.10፥30

አዳም በደል አስከሚገኝበትና በዲያብሎስ የጥፋት እርኩሰት እስከሚረከስ ድረስ የተፈጥሮ ባሕርዩ ከአሳት ድንጋዎች መካከል

ተለይቶ እንዲሚያንጸባርቅና እንደሚያበራ፣ እንቆባሕርይ ይመስል ነበር፣ ዳሩ ግን በዲያብሎስ የአመጻ ምክር ተታሎ እንደ እግዚአብሔር አምላክ እሆናለሁ ብሎ የተሰጠውን ትእዛዝና ህግ ባለመፈጸሙ እንደ እንቆባሕርይ የተፈጠረው አዳም እንደ አብነባሕርይ ተሰባሪ እንደ አፈር ፈራሽ ሆነ፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በጥበቡ እንደምሳሌው በመልኩ የፈጠረው ፈጣሪው የፍጡሩን አካል ተዋሕዶ ሰው ሆነ፡ ሰው በመሆኑ አዳምን እግዚአብሔር ወደ ጥንቱ ክብር መለሰው፡ የእግዚአብሔርን ልጅነትን እንደገና መልሶ ሰጠው፡፡ ለዚህ ነው በነቢያትና በሐዋርያት አፍ በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ ቃል እንደዚህ የተባለ፡-

"ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ፡ ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፡ ለዓይናችንም ድንቅ ናት፡፡ መዝ. 117፥22

እነሆ በጽዮን ድንጋይን ለመሰረት አስቀምጣለሁ፡ የተፈተነውን የከበረውን መሠረቱ የፀናውን የማእዘን ድንጋይ የሚያምን አያፍርም፡፡ ኢሳ. 28፥16

እነሆ የተመረጠና የከበረን የማእዘን ራስ ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ፡ በእርሱም የሚያምን አያፍርም ተብሎ ተጽፎአልና፡፡

እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው፡ ለማያምኑ ግን አናጢዎች የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ የእንቅፋትም

ድንጋይ የማሰናከያም አለት ሆነ፡ የማያምኑ ስለሆኑ በቃሉ ይሰናከሉበታልና፡ ለዚህ ደግሞ የተመደቡ ናቸው፡፡ 1 ጴጥ. 2፥6

እየሱስም እንዲህ አለ፦ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ፡ ይህም ከጌታ ዘንድ ሆነ /ከክርስቶስ/ ለዓይኖቻችንም ድንቅ ነው፡

የሚለውን ከቶ መጽሐፍ አላነበባችሁምን? ስለዚህ እላችሁአለሁ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ትወሰድአለች፡ ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች፡ በዚህም ድንጋይ /በክርስቶስ/ ላይ የሚወድቅ ይቀጠቀጣል፡ ድንጋዩ ግን የሚወድቅበትን ሁሉ ይፈጨዋል፡፡ ማቴ.21፥42

እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው /ከእርያም/ ተፈንቅሎ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየህ፡ የዚያን ጊዜም ብረቱና ሸክላው ናሱና ብሩ ወርቁም በአንድነት ተፈጩ፡ በመከርም ጊዜ /በእለተ ምፅአቱ ለክርስቶስ/ በአውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሆነ ነፋስም ወሰደው፡ ቦታውም /ገሀነም/ አልታወቀም፡ ምስሉንም /በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረው/ የመታ ድንጋይ /ክርስቶስ/ ታላቅ ተራራ ሆነ፡ ምድርንም ፈጽሞ ሞላ፡፡ ዳን. 2፥34" ታላቅ ተራራ ሆነ ማለት መንግሥትህ ትምጣልን እምንለው ሁሉ የክርስቶስ መንግሥት ተራራ በተባለው በእርያም ሰማይ ነውና፡፡

የክርስቶስን መንግሥት በተስፋ ለምንጠባበቅና ክብሩን ለመውረስ የተዘጋጀን ትእዛዛቱንም የፈጸምን ሊቃውንት ቅዱሳንና

ልዑላን ክርስቲያኖች ሁሉ እምነታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ይሁን፡ ምህረቱና ጸጋው ከእኛ ጋር ነውና የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር አይለያችሁ፡ አሜን።

እግዚአብሔር ስአዳም በተስፋው ዘር በኩል ከዲያብሉስ እጅ የአዳም ዘር ሁሉ ነጻ እንደሚያወጣቸው በነቢይ አፍ እንደዚህ አለ፡

"እኔ ምድርን ሠርቼአለሁ ሰውንም በእርስዋ ላይ ፈጥሬአለሁ፡ እኔ በእጄ /በክርስቶስ/ ሰማያትን ዘርግቼአለሁ፡ ሠራዊታቸውንም ሁሉ አዝዣለሁ፡ እኔ በጽድቅ /ኢየሱስን/ አስነስቼዋለሁ፡ መንገዱን /ቅዱስ መንጌል/ ሁሉ አቀናለሁ፡ እርሱ ከተማዬን /መንግሥተ ሰማያትን/ ይሠራል፡ በዋጋውም ወይም በደሞዝ ሳይሆን ምርኮኞቼን /ነፍሳትን/ ያወጣል፡ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ኢሳ. 45፥12

በመዝሙር እንዲህ ይላል፡- ከጨለማና ከሞት ጥላ አወጣቸው እስራታቸውንም ሰበረ ለሰው ልጆች ስለ አደረገው ታምራት ስለምህረቱም እግዚአብሔርን አመስግኑ፡ የናሱን ደጆች ሰብሮአልና፡ የብረቱንም መወርወሪያ ቆርጦአልና፡ መዝ. 106፥14

ወደላይ ዓረግህ ምርኮንም ማረክህ፡ ስጦታንም /የሕይወት ጸጋን/ ለሰዎች ሰጠህ፡ ደግሞም ለአመፀኞች በዚያ /በሲኦል/ ያድሩ ዘንድ፡ መዝ. 67፥18"

# ምዕራፍ ፪

# እግዚአብሔር የአቤልን መስዋእት ስለመቀበሉና በቃኤል እጅ አቤል ስለመገደሉ ሄኖክ ስለ መመረጡና መጻሕፍትን ለንደጻፈ

ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን ከዚች ምድር ላይ እንዳይኖሩ ገድሎና ስማቸውን አጥፍቶ ከሠራዊቱ ጋር እንዲኖርባትና ከሠራዊቱ ጋር ብቻውን እንዲነግሥባት ፈለገ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ስለሆነ አዳምን ከእግዚአብሔር ጋር በምክንያት አለያይቶ ሲያጠፋው የተነሣውን ዲያብሎስን ረግሞ ከፊታቸው እንዲርቅ በእሱ ፈንታ የሚያዝኑለትና የሚጠብቁትን የሚረዱትንም የመላእክት አለቆችን ላከለት፡ በመጽሐፈ ዜና አበው ዘስሙ ዣንሸዋ የእግዚአብሔር ሠራዊት በተባለው በግእዝ እንዲህ ይላልና፡

"ወዲያብሎስ የኃሥሥ ከመ ይቅትሎሙ ለአዳም ወሔዋን ወይደምስስ ስሞሙ እምላእለ ምድር ወትተርፍ ምድር ሎቱ ወለሠራዊቱ ለባሕቲቶሙ፡

ወእግዚአብሔርሰ መሐሪ ነጸሮ ለሰይጣን ከመ ውእቱ ይፈቅድ ይቅትል አዳምሃ፡ በምክንያቱ ብዙህ ወርእዮ ለአዳም እስመ ውእቱ የዋህ ወጽአ ቃል ዓቢይ እምኀበ እግዚአብሔር ኀበ ሰይጣን ወረገሞ ወኵሎ ውእቱ ወሠራዊቱ፡

ወተርፉ አዳም ወሔዋን ቅሙማኒሆሙ ላእለ አሐዱ ርዕሰ ደብር ወርእዮ ታህተ እምኔሆሙ ዓለመ ዓቢይ ወእልቦ እምኔሆሙ አሐዱ እምሠራዊተ ዲያብሎስ እምዘነጸርዎሙ ወበከዩ አዳም ወሔዋን ቅድመ እግዚአብሔር ወሐሠሡ እምኔሁ ሥርየተ ወመጽአ ቃል እምሰማይ ኀበአዳም ወይቤሎ ሎቱ አእምር ወለቡ እምዝንቱ ሠይጣን እስመ ውእቱ የሐሥሥ ይኂጥከሙ ኪያከ ወዘርአከ ዘይመጽእ እምድህሬከ ወበከየ አዳም ቅድመ እግዚአብሔር እምላኩ ወሠአለ ወሐሠሠ

እምኔሁ ከመ የሀቦ ግብረ መስቀል እምገነት ከመ፤ ን ኀቤሁ ትእምርተ ድህነ ይትናዘዝ ቦቱ፡

ወነጸረ እግዚአብሔር ሀዘኖ ለአዳም ወፈነወ መልአኮ ሚካኤልሃ ዘያበጽሖ ወዘይመርሆ እስከ ባህረ ውቅያኖስ ወእም ባህረ ውቅያኖስ እስከፈለገ ግዮን ከመ ይንሣእ እምህየ አብትራተ መስቀል ዘወርቅ፡

በትእዛዘ እግዚአብሔር ወረደ ሚካኤል መልአክ ወነስአ አብትረ መስቀል ዘወርቅ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ወአብጽሆሙ ምድረ ዮቅ በቅድመ እግዚአብሔር ወእምድህረ ዝንቱ አዘዞ እግዚአብሔር ለመልአክ ገብርኤል ከመይረድ ኀበገነት ወይንሣእ እምኔሁ እጣነ ዘጥእም ጼናሁ ከመየሀቦ ለአዳም ወወረደ መልአክ እግዚአብሔር ገብርኤል ውስተ ገነት፡

ወነሥአ እጣነ ከመየሀቦ ለአዳም ወፈጸመ ትእዛዘ እግዚአብሔር፡

ወአዘዞ እግዚአብሔር ለመልአክ ሩፋኤል ከማሆሙ ከመይረድ ኀበገነት ወይንሣእ ከርቤ ከመየሀቦ ለአዳም ወወ/ደ መልአክ እግዚአብሔር ወፈጸመ ትእዛዘ እግዚአብሔር፡

ወአብትራተ መስቀል ዘወርቅ ዘውስቴቱ አእናቁ እምባህረ ውቅያኖስ ወእምነ ምድረ ዮቅ ወእጣንሰ ውእቱ እምጽንፈ ገነት ምስራቅ ወከርቤኒ እምጽንፈ ገነት ምእራብ፡

ወሶበ ነጸረ አዳም ለአብትራተ መስቀል ዘወርቅ ወለእጣን ወለከርቤ ወተፈስሐ ወበከየ እስመ ውእቱ ኃየለ ከመ ወርቅ ትእምርተ መንግሥት ዘወጽአ እምኔሁ ወእጣን ትእምርተ ክህነት ዘመልከ ጼዴቅ ዘተከለ እምኔሁ ወከርቤ ትእምርተ ንስሐ ኃዘን ዘውስቴቱ፡

ወአዘዞሙ እግዚአብሔር ለሱርያኤል ወለሰላትያኤል ከመ ይጹሩ አዳምሃ ወሔዋንሃ ወአውረድዎሙ እምላእለ ርዕሰ ደብር ልዑል ወአምጽእዎሙ ኀበ በአተ ምድረ ፋይድ ዘተፈጥሩ ባቲ"

ከብዙ ዓመታቶችና ዘመኖች በኋላ እንደዚህ ሆነ፡ አዳምና ሔዋን ምንም የወርቅና የእጣን የከርቤም ምስጢር ቢሰጣቸው ፍዳ ወደአሰበት ወደተፈጠሩበት ወደ ኤልዳ ምድር በወረዱ ጊዜ

የእንስሳንና የአራዊትንም ባሕርይ ተጋሩ፡ ጠባያቸውም ሆነ፡ ሆኖም "እግዚአብሔር ባረካቸው፡ እንዲህም አላቸው፡- ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም የባሕርን አሦችና የሰማይን ወፎች በምድርም የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው፡ ዘፍ.1፥28" በተባሉት መሰረት አዳም ሚስቱን አወቀ፡ ፀነሰችም ቃየንንም ወለደች፡ ደግሞ ወንድሙን አቤልን ወለደች፡ አቤል በግ ጠባቂ ነበር፡ ቃየንም ምድርን ያርስ ነበር።

ከእለታት አንድ ቀን ቃየን ከሚያገኘው ከምድር አዝርእት ፍሬ ለእግዚአብሔር መስዋእት አቀረበ፡ እግዚአብሔር ግን አስተሳሰቡንና የልቡን ክፋት ተመልክቶ ቃየን የአቀረበውን መስዋእት አልተቀበለውም፡ ስለዚህ ቃየን እግዚአብሔርን አማረረ።

እንዲሁ አቤል ደግሞ ከቃየን ይልቅ እንስሳትን ይወድና ይጠብቅ ያረባም ስለነበር ከእንስሳዎቹ መካከል ይወደው የነበረውን የበግ ጠቦት ለእግዚአብሔር ስም ባርኮ መስዋእት አድርጐ አቀረበ፡

እግዚአብሔር የአቤልን መልካም ልብ ተመልክቶ የሚወደውንም ለእግዚአብሔር ብሎ ስላቀረበ የአቤልን መስዋእት ተመለከተ፡

እግዚአብሔር የአቤልን የበግ መሥዋእትን እንደተቀበለና እንደተመለከተለት ቃየን አይቶ በወንድሙ ላይ ቀና የክፋ ጥፋትም ሊያደርግበት አሰበ፡ በልቡ ውስጥ ኃጢአትን አስተናገደና ተናደደ፡

ቃየን በምንጭ አጠገብ ተቀምጦ ወንድሙን ለመጉዳት ሲያስብ ሳለ ሁለት አሞራዎች ወደምንጩ ውኃን ሊጠጡ ሲወርዱ

አየ፡ እንደኛው ቀድሞ ገባና ጠጥቶ ወጣ፡ ሁለተኛው በተራው ውኃን ሲጠጣ ወደምንጩ ሲገባ ከላይ የአለው አሞራ ድንጋይን ወደ ምንጩ አንከባሉ ሲጠጣ የገባውን ሲገድለው አየ፡

ቃየንም የሞተውን አሞራ ሄዶ አየና እንዲሁ ወንድሙን እንደሚገድለውና ሞትም እንደለ አወቀ፡

የጥፋት ግድያን ተማረ፡ ከዚያም ወንድሙ አቤልን ከአለበት አመጣውና መጀመሪያ ወደምንጩ ገብቶ ውኃ ጠጣ፡ በተራው አቤል ሊጠጣ ወደምንጩ ወረደና ተጉንበሶ ሲጠጣ ቃየን በአቤል ላይ ድንጋይ አነሣና ገደለው፡

በግእዝ በመጽሐፈ ዜና አበው እንደዚህ ሲልም ይገኛል፡ "ቃየልሰ ቀታሊ ነሥአ ዕብነ ዓቢየ ወዘበጦ ለእኁሁ ቦቱ ዲበ ርእሱ እስከ አውጽአ ናላሁ ወእሁሁ ይትለበጥ ውስተ ደሙ ቅድሜሁ ወኢነሥሐ ኅሊለ ዘገብረ ወምድርሰ ዘወድቀ ላዕሌሃ ደመ አቤል ጻድቅ አጽለቅለቀት ወረሰየት ደሞ ከመ ተሐጦ ለቃየል ወጸ፡ሐ ደሙ ለአቤል በምስጢር ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይትበቀል ሎቱ እምዘቀተሉ።"

የአቤል ደም በግፍ ወንድሙ ስለገደለው ከምድር ወደሰማይ ለእግዚአብሔር ጮኸ፡

እግዚአብሔር ቃየንን አለው፡ ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? እርሱም አለ አላውቅም የወንድሜ ጠባቂ እኔ ነኝን?

እግዚአብሔርም አለው ወንድምክን አቤል ገዳዩ አንተ ጠባቂው እንዳልሆንክ አውቃለሁ ምን አደረገህ? የወንድምህ የደሙ ድምጽ ከምድር ወደ እኔ ይጮሃል፡ አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ

ነህ፡ እንግዲህ ወንድሙን የገደለና አሳልፎ የሰጠ የካደም እግዚአብሔርን እንደገደለ ይቆጠራል፡ የሰውን ደም ያፈሰሰን ሁሉ እኔ እበቀለዋለሁ፡ ስምህም ወንድምክን በመግደልህ ቃኤል እንጂ ቃየን ተብሉ አይጠራ "ቃ ገዳይ ቃኤል ፈጣሪን ገዳይ ተብሉ ይተረጉማል"

አሁንም በግእዝ እንዲህ ይላል "ወመጽአ ቃሉ እግዚአብሔር እምሰማይ ኀበ ቃየል ወይቤሉ አ ቃኤል አይቴ ውእቱ እኁከ አቤል? ወይቤሉ ቃየል እፎ አ እግዚእ አነኑ አቃቢሁ ለአቤል ወይቤሉ እግዚአብሔር ለቃየል ርግምት ምድር ዘአስተየት ደሞ ለአቤል እኁዘ ወእንተኩን ርዑደ ወቅጉቁጠ ወይሉን ዝንቱ ትእምርት ለከ ወለኩሉ ዘመስለከ ወዘረከበከ ይቅትልከ"

አዳም ወንዶችንና ሴቶችን ከወለደና የአሥራ ሁለት ዘር ትውልድ የልጅ ልጅ ከአየ በኋላ አዳምና ሔዋን ከገነት ወደ ምድረ ፋይድ ከወረዱ ጀምሮ የኖረበት የእድሜው ዘመን ዘጠኝ መቶ ሠላሣ ሲሆነው አረፈ።

ልጆቹም ከኢልዳ ምድር ማዶ በአለ ዋሻ ውስጥ ወስደው ከወርቅና ከእጣን ከከርቤው ጋር መልከጼዴቅ እስከሚነሣ በክብር አኖሩት።

የእግዚአብሔር ካህን መልከጼዴቅ እስከሚመጣና እስከሚረከበው ድረስ እንዲጠበቅ አድርገው ዋሻውን በተጠረበ አለት ሳንቃ አሽጉት፡ ስሙንም ኮሬብ አሉት።

"ወነጸረ አዳም ከመቀርበ ተፍጻሜቱ ጸውአ ለውሉዱ ሴት ወቀርበ ኀቤሁ ውስተ በእተ መዛግብት ወይቤሉ አ ወልድየ ሴት አብጽሀ ሊተ ውሉድከ ኀቤየ ወውሉደ ውሉድከ ከመ እባርከ ሳእሲሆሙ እምቅድመ እሙት ወሰበ ሰምአ ሴት

ዘንተ ቃለ እምአዳም ወእስተጋብአ ውሉዶ ወውሉደ ውሉዱ ወእምጽአሙ ኀበ አቡሁ አዳም፡

ወይቤሎሙ አዳም ለውለደ ሴት ኩሉ ቡሩካነ ወብዙኃነ በቅድመ እግዚአብሔር ወይእዜኒ አ ወልድየ ሴት ኩን ቅውመ ላእለ ውሉዱከ ረእዮሙ ወእቀቦሙ በፍርሃተ እግዚአብሔር ወምርሆሙ ውስተ ፍኖተ ሐር ወአገዝኦሙ ከመ ይጸምኡ ለእግዚአብሔር፡

ወይቤሎሙ ለውሉደሴት እቀብዎ ለዝንቱ ወርቅ ወእጣን ወከርቤ ዘወሀበነ እግዚአብሔር ለነ ትእምርተ እስመ በመዋዕል ዘይመጽእ ዓይህ ያስጥም ኩሎ ፍጥረቱ ወዘይበውኡ ውስተ ታቦት ይንስኡ ምስሌሆሙ ወርቀ ወእጣን ወከርቤ ወሥጋ አጽምየ፡

ወይእዜኒ አ ወልድየ ሴት ናሁ ከሰትኩ ለከሙ ምስጢራተ ህቡአት ዘከሠቶሙ እግዚአብሔር ሲተ ይሑን ኢታቤ ትእዛዘየ ለነፍስከ ወወሉዱከ ወሶበ ፈጸመ አዳም ትእዛዞ ተፈትሐ መለያልይሁ ወተብጠለ እደዊሁ ወእገሪሁ ወደፈነ አእይንቲሁ ወመጠወ ነፍሶ፡

እንደዚህም ሆነ፡ አዳም ከሞተና ብዙ ዓመትታቶች ከአለፉ በኋላ የአዳም ዘሮች መብዛት በጀመሩና ቁጥራቸው አንድ መቶ ሺህ በሆናቸው ጊዜ ከአምስተኛው ሰማይ ከኢረር ክልል ውስጥ ከሚገኘው ከሜምሮስ ዓለም ከበብ የሚኖሩ ሮሃንያ በኢዮር ክልል ውስጥ ወደምትገኘው ወደዚህች ምድር ዓለም ኔፊሊምንና ንኤፍሊን ግያንንም ለማየት ወረዱ፡ በዚህን ጊዜ ከንኤፍሊና ከኔፊሊም ከግያን ልጆች ይልቅ የሰው ሴቶች ልጆች ውበትና ደም ግባት ያላቸው ሁነው የተዋቡና የሚያስደስቱ መልከመልካም ሁነው አዩአቸው፡ የሰው ልጆችም ሮሃንያ መናፍስትን አይተው ከሌላ ዓለም ሰማይ ስለመጡ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው አሉ፡፡

ዘንተ ቃለ እምአዳም ወእስተጋብአ ውሉደ ወውሉደ ውሉዱ ወእምጽአሙ ኀበ አቡሁ አዳም፡

ወይቤሎሙ አዳም ለውለደ ሴት ኩኑ ቡሩካነ ወብዙኃነ በቅድመ እግዚአብሔር ወይእዜኒ አ ወልድየ ሴት ኩን ቅውመ ላእለ ውሉዱከ ረእዮሙ ወአቀቦሙ በፍርሃተ እግዚአብሔር ወምርሆሙ ውስተ ፍኖተ ሐር ወአዝዞሙ ከመ ይጻምኡ ለእግዚአብሔር፡

ወይቤሎሙ ለውሉደሴት አቀብዎ ለዝንቱ ወርቅ ወእጣን ወከርቤ ዘወሀበነ እግዚአብሔር ለነ ትእምርተ እስመ በመዋዕል ዘይመጽእ ዓይህ ያስጥም ኩሉ ፍጥረቱ ወዘይበውኡ ውስተ ታቦት ይንስኡ ምስሌሆሙ ወርቀ ወእጣነ ወከርቤ ወሥጋ አጽምየ፡

ወይእዜኒ አ ወልድየ ሴት ናሁ ከሰትኩ ለከሙ ምስጢራተ ህቡአት ዘከሠቶሙ እግዚአብሔር ሲተ ይሁን አቃቤ ትእዛዝየ ለነፍስከ ወወሉዱከ ወሶበ ፈጸመ አዳም ትእዛዘ ተፈትሐ መለያልይሁ ወተብጠለ እደዊሁ ወእገሪሁ ወደፈነ አእይንቲሁ ወመጠወ ነፍሶ፡

እንደዚህም ሆነ፡ አዳም ከሞተና ብዙ ዓመትታቶች ከአለፉ በኋላ የአዳም ዘሮች መብዛት በጀመሩና ቁጥራቸው አንድ መቶ ሺህ በሆናቸው ጊዜ ከአምስተኛው ሰማይ ከኤረር ክልል ውስጥ ከሚገኘው ከሜምሮስ ዓለም ከበብ የሚኖሩ ሮሃንያ በኢዮር ክልል ውስጥ ወደምትገኘው ወደዚህች ምድር ዓለም ኔፊሊምንና ንኤፍሊን ግያንንም ለማየት ወረዱ፡ በዚህን ጊዜ ከንኤፍሊና ከኔፊሊም ከግያን ልጆች ይልቅ የሰው ሴቶች ልጆች ውበትና ደም ግባት ያላቸው ሁነው የተዋቡና የሚያስደስቱ መልከመልካም ሁነው አዩአቸው፡ የሰው ልጆችም ሮሃንያ መናፍስትን አይተው ከሌላ ዓለም ሰማይ ስለመጡ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው አሉ፡፡

እግዚአብሔርም ሮሃንያን በዚህ ዓለም ለመኖር፣ና ከሰው ልጆች ጋር ለመቀላቀል እንደተመኙ አውቆ ከቃኤል ልጆች ጋር እንዲቀላቀሉ ፈቀደ።

የሰው ልጆትም በመናፍስቶች ፍቅርና ስሜት ረኩ፣ ተደሰቱ እንደ አምላክ አመለኩአቸው፣ በዚህን ጊዜ ሮሐንያ መናፍስት በእነሱ እንደረኩ ስለአዩ የሰው ሴቶች ልጆችን መልከ መልካሞችን እየመረጡ በደማቸው ውስጥ አደሩ፣ ህሲናቸውንም ተቆጣጥረው ገዙት፣

የቃኤል ልጆችም ከመናፍስት የተለዩ መልከ ቀና ደም ግባት ያላቸውን ወንዶችንና ሴቶች ልጆችን ወለዱላቸው፣ ስማቸውንም ረዓይት አሉአቸው።

የረዓይቶች ቁመት ከሰው ልጆች ቁመት ይልቅ የረዘመ ነበረ፣ ከነዚህም አንዳንዶቹ ከአሥር እስከ አርባ ክንድ ይሆናሉ፣ በዘመናቸው እስከሚጠፉ ኃያላን አዳኞች ሆኑ፣ ለስማቸው መታሰቢያ ይሆናቸው ዘንድ ከተራራና ከኮረብታ ላይ ድንጋይን ፈንቅለው ወስደው እንደሃውልት መትከል ጀመሩ።

አንዳንዶች ደግሞ በግዮን ወንዝ ዳርቻ ባለሦስት የማእዘን ምስጢር ህንጻ አነፁ፣ እነሱ ካለፉ በኋላም የተነሱ የሰው ልጆች ማምለኪያና መሠዊያ ለበድናቸውም መቀበሪያ አደረጉት፣

ሌሎችም እነሱን በማየት የድንጋይ ሐውልት ለራሳቸው አቆሙ፣ መንደርም ቆረቆሩ፣

በመጽሐፈ ዜና አበው እንደዚህ ሲል በግእዙ ይገኛል፡ - - - - እሄውም ከሴላ ዓለም መጣሁ የሚለው ሰይጣን በመልአክ ተመስሎ ለሴት ከታየውና በአማረ ቃል ህሊናውን ሲቆጣጠረውና ልጆቹንም ሲገዛ ፈልጎ፡ እንዲህ አለው ይላል፡

"ይቤሎ አ ሴት ለምንት ትነብር ውስተ ዝንቱ ደብር እስመ ውእቱ ደብር እፁብ ወምሉእ እምእእባን ወሆፃ ወእፀው ዘአልቦ ፍሬ ሰናይ ወገዳም ዘአልቦቱ አብያት ወኢሀገር ወኢማህደር ሠናይ። አላ ሁሩር ወድኅም ወኃዘን ወይቤሎ ንህነ ውስተ መካናት ሠናያት ወዓለም ካልዕ እምዝንቱ ዓለም አላ ዓለመሠናይ ወሥርአታቲነ ሥርአታተ ሠናይት ወብእሲታትነ አልቦ ሠናይ ዘይሤኒ እምኔሆን፡

ወሶበ ሰማእከኒ ዘእቤለከ አነ አስተዋስበከ እምአዋልድየ ወዝንቱ በነቤነ አልቦቱ ኃጢአት ወኢፍትወት እንስሳዊት ወንህነ በውስተ ዓለምነ አልብነ እግዚአ አላሉልነ አጋእዝት ወኩልነ ብርሃናውያን ወሰማያውያን ወጽኑአን ወክቡራን ኩሉሄ ያንበሰብል ብርሃን በሕእለ ገጽነ"

ከሜምርስ ዓለም ወደዚህ ዓለም ስለወረዱት መናፍስት ደግሞ እንደዚህ ይላል፡ ይህም የሆነው በያሬድ ዘመን ነው፡

"ወይቤልዎሙ እምጽኡ ለነ የዓ መብልአ ኀበ ዝንቱ ዓይንማይ ከመ ንብላእ ንህነ ወአቢያኢነ ወሶበ ነጸርዎሙ ውሉደ ቃኤል፡ አንክሩ እምኔሆሙ ወይቤሉ፡ እስመ እሉንቱ ሠናያን ገጽ ወኢነጸርን እምሳሊሆሙ ግሙራ ተንሥኡ ወመጽኡ ምስሌሆሙ ኀበ ዓይንማይ ከመ ይነጽሩ አብያጺሆሙ ወረከቡ ሰናየ ወተጻውኡ በበይናቲሆሙ ከመ ይትጋብኡ ወይነጽርዎሙ ለእሉንቱ ሠናያ ነገድ ወተጋብኡ ኀቤሆሙ ዕደው ወአንስት ወይቤሉሙ አረጋዊ ንህነ ፈላሲያን በውስተ ምድርከሙ እምጽኡ ኀቤከሙ ሠናየ መብልአ ወመስቴ ወአንስት ወናእርፍ ኀቤከሙ ወሶበ ሰምኡ እሉንተ ነገረ አረጋዊ ኮነ ኩሉ አሐደ አሐደ እምውሉደ ቃኤል ያምጽኡ ብእሲተ ወጠካልአ ያምጽኡ ወለቶ፡

ወበጽሓ ኀበሆሙ አንስት ብዙኃት ወኮነ አሐቲ አሐቲ እምኔሆሙ ወሶበ ፈቀዱ ወዘፈተው ነሥኡ አህደሩ ምስለ አዋልደ ቃኤል፡ ወተጎወሉ ምስለ ውሉደ

ቃኤል ማህበራት ርኩሳት ወበዘንቱ ግብር ዘኮኑ ውሉደ ያሬድ ይወርዱ እምደብር ቅዱስ በእንቲአሁ ወንህነሰ በፈቃድነ ንከስት ለከሙ ውእቱ ዝንቱ ሰብ ወረደ ቃኤል ኀበ ምድር ጽቡር ጸሊም ወበዘሁ ዘርኡ፡

ወኮና አዋልደ ቃኤል ይቀንዓ ላእለ ውሉደ ሴት ከመ እራዊት መዓጥያን ወከመዝ ውሉደ ሴትሂ ላእለ አዋልደ ቃኤል ውእቶሙሰ ረኩሱ ምስሌሆን ወእምድህረ ድቀቶሙ ውስተ ርኩሰት ተመይጡ ውስተ ፍኖት ዘወረዱ እምኔሃ ወፈቀዱ ይዕርጉ ኀበ ደብር ወኢተከህሎሙ እስመ አእባን ደብር ቅዱስ ኮኑ እሳተ ዘታንበለብል ቅድሜሆሙ፡

እንደዚህም ሆነ፡ የያሬድ ልጅ ሄኖክ አስተዋይና ብልህ ከመሆኑ የተነሣ ከአባቶቹ የሰማውን ምክርና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ያከብርና ይፈጽም ነበር፡ ከጥፋት እርኩሰት ከመራቁም ከመጥላቱም የተነሣ የሴትን ልጆች ሁሉ ሰብስቦ እግዚአብሔር የአዘዘውን እንዲፈጽሙ የማይወደውንም እንዲተዉና እንዲጠሉ ይመክራቸው ያስተምራቸው ነበር፡ ነገር ግን ወደጥፋት አገር በኃጢአት ጕዳና ይመላለሱ ነበር፡

ሄኖክ አስተሳሰቡና አመለካከቱ እግዚአብሔር የአዘዘውንና የፈቀደው ብቻ ስለሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ፍጹም ሆኖ ስለተገኘ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች መካከል ለይቶ መረጠው፡ የሚያደርገውን ሁሉ እንዲያመለክተው እግዚአብሔር መላኩን ላከለት፡

ሄኖክም ከእግዚአብሔር መልአክ በሚሰጠው መመሪያና እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋ የአባቶቹን የሕይወት ዘመን ስለሚመጣው የጥፋት ዘመን በአሥራ ሁለት የወር በሮች በምስራቅ በኩል ስለሚወጣው ፀሐይ ምስጢር ምስጢሩም

ሉተገለጸላቸው ለእሥራ ሁለቱ ደቀመዛሙርቶቹ ሥልጣነ ክህነትን በሰማይና በምድር ላይ ይሰጣቸው ዘንድ የሕይወት ቃሉንም ያበራላቸው ዘንድ ስላሰው በሥጋ ተገልጦ ስለሚመጣው ስለክርስቶስ ተናገረ።

ስለእርሱ ብቻም አይደለም በሰማያትና በምድር ውስጥ ስለአሉት እርሱ እግዚአብሔር ስለፈጠራቸው ፍጥረታት በቤሐርና በየብስ በአየር የሰለጠኑትን በራሪዎችና ተንሣፋፊዎችን የሚሳቡትንና የሚንቀሳቀሱትን የሚዘሉትንም የሚበረግጉትንም አሣዎችንና አእዋፋትን እንስሳትንና እራዊትን እፀዋትንና በእፀዋት ላይ የአሉትን ድቃቅን ፍጥረታትን፣ የእንቁ ድንጋዮችንና በድንጋዩ ውስጥ የሚገኙትን እንቁዎች የአላቸውን የተፈጥሮ ባህርይ የሰው ልጆች ይመረምሩአቸውና ከተሰጣቸው ጸጋ ጋር ይጋሩ ዘንድ ስለአሰው የጥበብ ምስጢር ለልጆ ልጆቻቸው ያስተላልፉ ዘንድ ከእግዚአብሔር መልአክ ከኡራኤል የተረዳውንና የተማረውን የጥበብ እውቀት አስተውሎ በመጽሐፍ ጻፈው። ስለዚህም ጥበብ በእውቀት ከበረች በማስተዋልም ጸናች። ከእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጠና የተወደደ ሄኖክም ስለሚመጣው ፍጻሜ ቀን ሁሉ ለሰው ልጆች መመሪያ ሥርዓት ይሆናቸው ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዛትንና ህጐችን በመጽሐፉ ጽፎ ለልጁ ለማቱሳላ አስረከቦታል፣ ማቱሳላም ለኖህ የአስረከበውና የአስተላለፈለት መጽሐፍቶች፦

1ኛ/ መጽሐፈ አዳም፣ ይኸውም ዜና አዳም የተባለው
2ኛ/ መጽሐፈ ዣንሸዋ አውደ ፀሐይ የተባለው ስለሰማያትና
በውስጣቸው ስለአሉት ዓለማትና ከዋክብት ብዛት የሚዘረዝር፣
3ኛ/ መጽሐፈ ዜና አበው 4ኛ/ መጽሐፈ ተስፋ ዘሱባኤ
5ኛ/ መጽሐፈ ጥበብ ዘኢዮቤል 6ኛ/ በራእይ የአየው ትንቢተ ሄኖክ
7ኛ/ እንዲሁም መጽሐፈ ሄኖክ ናቸው።

በእግዚአብሔር መልአክ በኡርኤል /ኡራኤል/ ሄኖኤል የተባለው ሄኖክ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ፈጽሞና አስተምሮ ከእግዚአብሔር ጋር መንገዱን አድርጓልና፣ ወደ እግዚአብሔር በአካለ ሥጋ ከሰዎች ተለይቶ ተወሰደ እንጂ እንደአባቶቹ ነፍሥና ሥጋው አልተለያዩም፣ እግዚአብሔር ከሰው ልጆች መካከል መርጦታልና፣ በሕይወተሥጋ ይኖር ዘንድ ሞትን አላየም፣ በሥጋው አልሞተም።

በግእዙ እንዲህ ይላል፡- ከመጽሐፈ ዜና አበው

"ወሄኖክ አቀበ ትእዛዘ እግዚአብሔር ወትእዛዘ ያሬድ አቡሁ ወኮነ ይትቀነይ ቅድመ እግዚአብሔር ውስተ በዓተ ምድር ወዝንቱ ሄኖክ ቦቱ መንክራት ብዙኃት ወቦቱ ኄዐበ ጸሐፈ መጻሕፍተ ወኮነ መጻሕፍቲሁ ምስጢራተ ዓለም ወኢይትከሃሉ ለተነግሮ እው ለተዘክሮ ውስተ ዝንቱ ዓለም፣

ወሶበ ፈጸመ ሄኖክ ትእዛዘ እግዚአብሔር ወእግዚአብሔርሰ ወሰዶ ለሄኖክ እምላእለ ዝንቱ ዓለም ኀበ ምድረ ሕይወት ማህደረ ጻድቃን ወሄራን፣ - - -

- - - እምአዳም እስከ ዛቲ እለት አሐዱ ይኤዝዞ ለአሐዱ እምአረጋውያን በጊዜ አረፍቶሙ እምሥጋ ወይሜህሩ በበይናቲሆሙ"

ከአዳም እስከጥፋት ውኃ ድረስ አንዱ አባት ለአንዱ ልጁ ከአረጋውያን መካከል ለይቶ የአዝዘዋል፣ ነፍስና ሥጋቸው

በምትለያይበት ሰዓት እርስ በእርሳቸው ይማማሩና ይናዘዙ ነበር። ለዚህ ነው ሰው ሊሞት ሲል ለሚወደው ልጁ ሐብቱን እንደተናዘዘለት ከሥጋው ነፍሱ የሚለይ፣ እንዲሁ ኑዛዜ ከአባቶች ዘንድ ስለተወረሰ ዛሬም ተከብሮና ተጠብቆ ይቐል፣ የኑዛዜ ቃል ለአንደበት በር ቁልፍና ማሰሪያ ስለሆነ በእሱ ይዘጋል እንጂ አይከፈትም።

# ምዕራፍ ፫

## ኖህና ልጆቹ ከጥፋት ውኃ ስለመዳናቸው በእግዚአብሔር መልአክ እየተረዳ ስለአጸዋትና ስለ አእባን ምስጢር ስለመጻፉ

የላሜህ ልጅ ኖህ በምድር በአሉት በሰው ልጆች መካከል እንደ ቅድመ አያቱ ሄኖክ እግዚአብሔርን የሚፈራና የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚፈጽም ፍጹም ጻድቅ ሰው ነበር።

በኖህ አድሜ ዘመን እንደዚህ ሆነ፡ የሰው ልጆችና ሮሃንያን ተቀላቅለው ተጋብተውና ተዋልደው ስለነበር፡ ምድርን በግፍና በክፋት ሥራቸው አርክሰዋት ነበር፡

በድሮ ዘመን ረዓይት ሲባሉ አንዳአንዶች ደግሞ ግያን ኔፊሊም ንኤፍ ሌም ይባላሉ፡ እነዚህ ረአይቶች በምድር ላይ በበዙና ስማቸው ታውቆ ኃያላን በሆኑ ግዜ በአርማሮስ ንጉሥ እየተመሩ የተፈጥሮን ባህርይ ለመቀየር የተሰያዩ ከንቱ አማልክቶችን ለማብዛት ይፈላሰፉና ያስተምሩም ጀመር።

አንዳአንዶችም በአዛዝኤል መንፈስ ተሰክፈው እየተጨነቁ አእምሮአቸውን እየረሱ እርስ በእርሳቸው አጸያፊ ግብረ ሥጋ ይፈጽሙ ነበር።

ሌሎች ወገኖች ደግሞ በጋድራኤል እየታዘዙ አባቶቻቸውን ለስማቸው መዘከሪያ በግዮንና በአርዲስ ወንዝ ዳርቻ ባለሦስት ማዕዘን ምስጢር ሕንጻዎችንና ሐውልቶችን አቁመው ስለነበር በሐውልቱና በግንቡ ስር የሰው ልጆችን ለበዓል እያረዱ ደማቸውን

ይረጩና በደማቸው ይታጠቡ ነበር። ለበጐ ነገር የተፈጠረችው ምድር በግፍና በክፋት ተሞላች፤ ስለዚህ በመከራና በጭካኔ በግፍም የተገደሉት የሰው ልጆች በደልና ሥቃይ ከመብዛቱ የተነሣ ደማዊ ነፍሳቸውና ከሥጋቸው ተለይቶ የወጣው ሕያው ነፍሳቸው ሁሉ ከምድር ወደ እግዚአብሔር ይጮህ ጀመር፤ እግዚአብሔርም ሰማ።

እግዚአብሔርም ምድርን አየ፤ እነሆም ሥጋ የለበሰ ሁሉ የሰው ልጆች በምድር ላይ ደም በማፍሰስና በረከሰ ዝሙት ምድር ተበላሽታና ረክሳ ነበር።

የሰው ልጆች የተሰጣቸው የተፈጥሮ ባህርይ ጸታቸውን ትተው እርስ በእርሳቸው በማይገባ ግብረ ሥጋ በመርከሳቸው ጸታቸውንም ባለማክበራቸው የሰው አሳቡና ምኞቱ ሁሉ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ ወደጥፋት እርኩሰት ልባቸው በመሄዱ እግዚአብሔር አያቸው።

እግዚለብሔርም አለ፡- በእግዚአብሔር መልክ እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የፈጠርኩት ሰው ክፉውንና መልካሙን ለይቶ እንዲመርጥበት በሰጠሁት አእምሮ መልካሙን ትቶ የጥፋትን ሥራ አፍቅሮ በመፈጸሙ የኃጢአትንም ደሞዝ እንዲከፈለው ስለፈለገ ዋጋውን እከፍለዋለሁ፤ የጥፋቱን ብድራት ሁሉ ለእርሱ እመልስለታለሁ፤ በልቡ ክፋትና ተንኮል ተሞልቷልና ከምድር አጠፋው አለሁ፤ ከሰው መጥፎ ሥራ የተነሣ ምድር ረክሳለች፤ በግፍ ደምም ተሞልታለች፤ ሰውን ፈጥሮ ነጻ አእምሮ በመስጠቱና የፈቀደውን እንዲያደርግና እንዲመረጥ መብት በመስጠቱ ተጸጸተ።

ነገር ግን ኖህ ከቤተሰቦቹ ጋር እግዚአብሔርን የሚፈራ ለአባቶቹ የተሰጣቸውን ትእዛዝ የሚፈጽም በትውልዱ ጻድቅና ፍጹም ሰው እንደሆነ እግዚአብሔር አየ፤ አካሄዱም ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ነበር፡ እግዚአብሔርም ከመላእክት አለቆች መካከል አንዱን ኪሩብ ሱርያኤልን ወደኖህ ያስተምረው ዘንድ ላከው፤

መልአኩ ሱርያኤልም ወደኖህ ሄደና እግዚአብሔር ለሰው ልጆችና ከረዓይቶች ግፍና በደል ከፋትም የተነሣ ምድር እረከሳለች፡ ከኃጢአታቸውም ብዛት ተበላሽታለች፡ እነሆ በምድር ያለውን ሁሉ በጥፋት ውኃ አጠፋቸውአለሁ፡ ከምድርም ፊት ፈጽሜ አጠርጋቸው አለሁ፡ በዲን እሳት እንደገለባ አቃጥላቸው አለሁ፡ ነፋስ ፍሬን ከእብቁ እንደሚለይ እንዲሁ አንተንና ቤተሰቦችህን ከእነርሱ መካከል ለይቼ አድንህ አለሁ፡ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አግኝተሃልና የክፎችንም ሥራ ፈጽመህ ጠልተህ ከጠፊዎች ጋር አልተባበርክምና እግዚአብሔር ከዚህ ትውልድ አንተን መረጠህ።

ስለዚህ ከጥፋት ውኃ ታመልጥ ዘንድ ጕፈራም ከሆነው ከአንቃና ከጥቁር እንጨት መርከብን /ታቦትን/ ለአንተና ለቤተሰብህ ከአንተም ጋር ከጥፋት ውኃ ለዘር ለሚቀሩ ሥራ የመርከቢቱን ውስጥና ውጭዋን ኖህያንና ሩይሬን በሮሃ ድንጋይ ወቅጠህ ከአቦካኸው በኋላ ከቅጥራን ሙጫ ጋር እየለወስክ ለቅልቃት ምረጋትም።

በመልአኩ ሱርያኤል ከንድ የመርከቢቱ ርዝመት ሦስት መቶ ከንድ ወርድዋ አምሳ ከንድ የከፍታዋ ቁመት ሠላሣ ከንድ ይሁን፡ የመርከቢቱን በር በጐንዋ ታደርጋለህ በጐንና በጐን አሥራ ሁለት መስኮቶች ታበጃለህ፡ አንደኛ ሁለተኛ ሦስተኛ ደርብ /ፎቅ/ ታደርጋለህ፡

እግዚአብሔርም አለሁ፦ እኔ እነሆ ከሰማይ በታች በአለህባት ምድር ላይ የሕይወት ነፍስ ያለውን ሥጋ ሁሉ ለማጥፋት የጥፋት ውኃን አመጣለሁ፡ በምድር ያለው ሁሉ ይጠፋል፡ ነገር ግን ቃል ኪዳኔን ከአንተ ጋር ለዘለዓለም አቆማለሁ፡ ወደ መርከቢቱም አንተና ልጆችህ ሚስትህንና የልጆችህ ሚስቶች ይዘህ ትገባለህ፡ ከአንተ ጋር በሕይወት ይኖሩና ለዘርም ይቀሩ ዘንድ ሥጋ ካለው እንስሳና አራዊት ከየወገኑ ወፍና አሞራ እንደወገኑ ሁለት ሁለት ሰባትም አድርገህ ወደመርከቢቱ ታስገባለህ ብሉ እግዚአብሔር የአዘዘውን ሁሉ የእግዚአብሔር መልአክ ሱርያል ነገረው፡ ኖህም እግዚአብሔር የአዘዘውን ሁሉ አደረገ፡

"ይቤሎ እግዚአብሔር ለኖህ ግበር ለከ ታቦተ እምዕፅ ዘይነቅዝ ከመ ይኩን ለከ መድኃኒተ ወለሰብአ ቤትከ ምስሌከ ወሰበ ገበርከ ይኩን ኑኃ አሐዱ እንቀጽ ኀበ ላእል ወትኩን ሠለስቱ አጽራህ ወሰሰ አሐቲ እምአጽራህ ቆመ ሠላሣ እመተ ወኑኃ ሠለስተ ምዕተ እመተ ወስፋኃ ሃምሳ እመተ መልእክ መቅባዕ ዓዘቃተ ኖህያን ወሩደሬን በናዕክ እምውስየ ወአምአፍአ ወግበር ውስተ ታቦት መዛግብተ ለሥርናይ ከመ ትብላእ አንተ ወዘምስሌከ"

ኖህ የእግዚአብሔር መልአክ ሱርያኤል በአሳየውና በአስተማረው የጥበብ ሥራ እየተረዳ መርከቢቱን ሰርቶ ሲጨርስ እድሜው የስድስት መቶ ዓመት ሰው ነበር።

በዚህን ጊዜ አያቱ ማቱሳላ ሲሞት በቀረበ ጊዜ ከአባቶቹ የተረከበውን የአዳምንና የሔዋንን አጽም ወርቅንና እጣኑን ከርቤውንም የአዳምን ሕይወት ታሪክ የያዘው ዜና አዳምን የልጆቹንም የሄኖክንም መጽሐፍት ሁሉ በጥፋት ውኃ እንዳይጠፉ ይዞአቸው ይገባ ዘንድ አስረከበው፡ ወደፊት ለሚነሣው እግዚአብሔር ካህን ለመልከ ጼዴቅ ይሰጡትና ይጠብቀው ዘንድ እንደዚህ አለው፡

ለላሜህ ልጅ ለኖህ እኔ እንደአባቶቼ ከአረፍኩ በኋላ የጥፋት ውኃ እንደሚመጣና በምድር የአለው ፍጥረት ሁሉ እንደሚጠፋ ነገር ግን ለዘር ትተርፉ ዘንድ አንተና ልጆችህ ትድናላችሁ።

የምሰጥህን የአዳምን አጽምና ከአጽሙ ጋር የአሉትን የእግዚአብሔርን ስጦታዎችንና የሄኖክ ትንቢት መጽሐፍቶችን በክብር አቆይተህ ለምትባርከው ለሴም ልጅህ ስጠው እርሱም ለሚባርከው ልጁ እንዲሁ ይስጠው፡ የእግዚአብሔር ካህን የሆነ መልከ ጼዴቅ ሲነሣ ለእርሱ የልጅ ልጅህ ወስዶ የአስረከበው።

የእግዚአብሔር ካህን መልከ ጼዴቅ እናቱ ከምትወደው ከካም ዘር የሚወጣ ሲሆን በእናቱ በኩል ከሴም ልጅ ከአርፋክስድ ልጅ ከቃይን የልጅ ልጅ ከሰሊማያ ይወለዳል። እናቱ ሰሊማያ አባቱ ቂና ይባላሉ፡ ነገር ግን በክህነቱ በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሉ ለዘለዓለም የእግዚአብሔር ካህን ይባላል፡ ለእርሱ የእግዚአብሔር ምስጢር ተሰጥቶአልና።

"ወይቤሎ ማቱሳላ ለኖህ ኦ ወልድየ ዘይ ቀንይ ለእግዚአብሔር ቅዱ ሥጋ አቡነ አዳም ይኩን ልብሱ እምእዝተ ወይቀ፥ት ውስተ ሐቋሁ ወይን. ሱቱ ሠርጕ ወይጸሊ ለእግዚአብሔር እምላክ ከመ ይዕቀብ ሥጋ አቡነ አዳም እስመ ውእቱ ሥጋ ዓቢይ ቅድመ እግዚአብሔር ወዘይከውን ቅውመ ውእቱ ካህነ እግዚአብሔር ልዑል በንጹህ ልብ ወበሰናይ መዝሙር ይትቀነይ ቅድመ እግዚአብሔር፡

ዝ ውእቱ መልከ ጼዴቅ ካህነ እግዚአብሔር እምላክ ውሉደ ውሉዱ ለካም፣ ካም ወለደ ለኩሽ፥ ኩሽ ወለደ ለሳባ፥ ሳባ ወለደ ለንባ፥ ንባ ወለደ ለአጋና፥ አጋና ወለደ ለኢታን፥ ኢታን ወለደ ለናምሩድ፥ ናምሩድ ወለደ ለቱና፥ ቱና ወለደ ለመልከ ጼዴቅ ወእሙ ወለተ ሚልኪ ለሊማያ እስመ ውእቱ ካህኑ ለእግዚአብሔር ልዑል ይንሥኡ ምስሌሆሙ ሥጋ አቡነ አዳም ይሰድዎ ወያንብርዎ በላእለ ደብረ ራማ ዛቲ ይዕቲ ማእከለ ምድር ወይኩን መልከ ጼዴቅ ካህኑ ለእግዚአብሔር በውስተ ይእቲ ደብረራማ እስከ ለዓለም እስመ ይእቲ ቅድስት ሃገር"

እግዚአብሔር በምድር ላይ የጥፋትን ውኃ ከአወረደና የሕይወት የእለውን ሁሉ ደምስሶ አጠፋ ሁሉም ሞቱ ነገር ግን ኖህና በመርከቢቱ ውስጥ የነበሩት ብቻ ከጥፋት ውኃ ዳኑ ብቻቸውን ቀሩ።

የጥፋት ውኃ ከአለፈ በኋላ እግዚአብሔር ኖህን አለው፡ ሚስትህንና ልጆችህን የልጆችህንም ሚስቶች ይዘህ ከመርከብ ውጣ፡ ከአንተ ጋር ያሉትን እንስሳትንና አራዊትን ወፎችንና አሞራዎችን የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ አውጣቸው፡ በምድር ላይ ይርመስመሱ ይዋለዱ በመሬት ላይ ይብዙ አለው።

ኖህም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ፡ የህዳር መባቻ እለት ኖህ በአሉባር ተራራ ለእግዚአብሔር የመስዋእት መሠዊያን

ድንጋይ ተከለ፡ ስሙንም ዮጽ ብሎ ጠራው፡ ዮጸ ማለት የጠራና የሚፈተን ወርቅ ማለት ነው፡ የተራራውንም ስም አሉባር አለው፡ ትርጉሙ የጉር አዱኛ ታየ ማለት ነው፡ ከዚያም ከንጹህ እንስሳና ከወፍ ከእህልም መርጦ ለእግዚአብሔር መስዋእት አቀረበ።

እግዚአብሔር ኖህ የአቀረበውን መስዋእት ተመልክቶ ተቀበለና ዳግመኛ ምድርን በእርስዋ ያሉትን ፍጥረቱን በጥፋት ውኃ አልመታም፤ አልቀስፍም ግን ምድር በዘመንዋ ብርድና ሙቀት በጋና ክረምት ቀንና ሌሊት ከመፈራረቅ አያቋርጡም አለ።

"ወኖህሰ ውስተ ታቦት ቦአ ወነሥአ እምአእዋፍ ንጹሐን ወወጠነ በከመ አዘዞ እግዚአብሔር ሎቱ ወአዕረገ ቁርባናተ ላዕለ መሥዋዕ ቅድመ እግዚአብሔር እምላዕለ ኪዳን ዘተካየዳ ቦቱ እግዚአብሔር ለኖህ ወአስተርአዮ ሎቱ ቀስተ ደመና በውስተ አየር ወአዔነወ እግዚአብሔር ጼና ቁርባን ኖህ ወተከየደ ምስሌሁ ኪዳን ከመ ኢያመጽእ ዓይህ ካልእ ላዕለ ምድር እምድህረዝ እስከ ለዓለም ወዝንቱ ውእቱ ኪዳን ዘተካየደ እግዚአብሔር እስመ ምስለ ኖህ - -

እግዚአብሔር ይቤሎ ለኖህ አነ እሬሲ ቀስተ ኪዳንየ እምውስተ ደመና ወሶበ አስተርአየ የአምሩ ሰብእ፡ ከመ በአማን አስተርአየ ወሶበ ኮነ እምኔሃ ተምዕአ ያስተርኢ ቀስተ ደመና ወይትሀደግ ትምዕእ ወመቅሰፍት ዘኮንኩ እፈቅድ አምጽኡ ላዕለ ሰብእ።

እግዚአብሔር ተወከፈ ቁርባነ ኖህ ወባረከ ላዕሌሁ ወላዕለ ውሉዱ ወይቤሎሙ ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልኡ ውስተ ገጸ ምድር ወአዘዛ ለምድር እግዚአብሔር ከመ ታውጽእ ሣዕረ በከመ ልማድ ዘትካት ለአራዊት ወለእንስሳ ወለአእዋፍ ወለኩሉ ዘይትሀወስ ላዕለ ምድር ወኖህሰ ሰገደ ቅድመ እግዚአብሔር ውእቱ ወደቂቁ ወአንስቲያሆሙ ወሰብሆ ለእግዚአብሔር በእንተ መድኃኒት እጸዋት ወምስጢረ አእባን"

ኖህ ከእግዚአብሔር መልአክ ኑርያኤል የሰማውን የተማረውን የእግዚአብሔርን ትእዛዛትና ቃል ኪዳኑን ሁሉ ለልጆቹ፣ ልጆቹ ለልጆቻቸው እንዲያስተምሩና ቃሉን እንዲጠብቁት የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እንዲፈጽሙ አዘዛቸው።

የአበውን ሕይወት ታሪክ የያዘ ዜና አበውና መጽሐፈ ሄኖክ ትንቢተ ሄኖክ የሚባሉትን መጽሐፍቶች ለልጆቹ ኖህ አስረከቡዋቸዋል። እንዲሁ በኖህ የተዘጋጁና የተጻፉ ስለጥፋት ውኃ ስለ እንስሳትና ስለ አራዊት ባህርይ ስለሰማያትና በውስጣቸው ስለአሉት ዓለሞችና ከዋክብት ስለሰማይ ወፎችና ስለባህር አሣዎች በምድር ስለሚሳቡ እንደየወገናቸው ተፈጥሮ ባህርይ ስለ እጸዋት ምግብነትና መድኃኒትነት፣ ስለድንጋዮችና ስለጠሩት እንቁዎች ምስጢር ስለንጹህነትና ስለ እርኩስነት ስለፈዋሽነትና ስለመርዝነት የሚገልጹትን ሁሉ ከኖህ በፊት ያልታወቁትን የተፈጥሮ ባህርይ ምስጢሮች ከመልአኩ እየተረዳ በግልጽ ዘርዝሮ ጽፎአቸዋል። ይህም መጽሐፍ መጽሐፈ አበው ወመጽሐፈ ኖህ ይባላል።

ለእንስሣና ለአራዊት ለአእዋፍና ለንስሮች ለአጸዋትና ለድንጋዮች ለተፈጥሮ ባህርያቸው የተሰጣቸውን ጸጋንና ኃይልን እንዲጋሩና ጠባያቸው እንዲሆን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ፈቅዶላቸዋል፣ ለዚህ ነው በእፀዋት ላይ ያለው የተፈጥሮ ባህርይ በሰው አካል ውስጥ አድሮ ለመልካም ወይም ለመጥፎ የሚሆን፣ እንዲሁ በድንጋዮች ላይ የአለው የተፈጥሮ ባህርይ በሰው ሰውነት ላይ ተሰራጭቶና ተዋህዶ እንደተሰጠው ጸጋና ኃይል ለሰው ልጅ

የሚጋራ ጠባይ ይሆናል፡ ነገር ግን የሰው ልጆች ከመልካሙ ተግባር ይልቅ መጥፎውን ሥራ በመምረጥ ከደግነት ይልቅ የጥበብን ሐብት በመጥላት የኃጢአትን ሥራ እርኩሰትን በመቀበል እርስ በራሱ ሲፋጅ ሲናናቅ፣ ሲጠፋፋ፡ ሲጋደል ከሥጋይ ጋር ኖሯል፡ አሁንም እየሆነ ነው። የሰው ልጅ በሕይወቱ ታሪክ ላይ በክብሩ ፈንታ ውርደትን መረጠ በሕይወት ፈንታ ሞትን፡ በጤንነት ፈንታ ህመምን፡ በሐብት ፈንታ ድህነትን፣ በደስታ ፈንታ ሐዘንን፣ በነጻነት ፈንታ ባርነትን፣ ፈልጎ በራሱ ላይ መከራ እያበዛ ሄደ፡ ከሰባዊነት ጠባዩ ወደ አውሬነት እየተለወጠና በስራው ጥፋት እየጠፋ ነው።

ነገር ግን ሳይጠፋ ከሚያጠፋ ሳይበደል ከሚበድል ገና በሕይወት ሳለ ሳይሞት ከሞተ በደለኛ ሰው ከሆነ ትርቁና ከእናንተ ታርቁት ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ትጠብቁና በህጉም ትጸኑ ዘንድ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ቅዱሳኑን ትመስሉ ዘንድ ከመጽሐፈ ዜና አበው አስፈላጊውን የጥንት ታሪክ ጽፌላችሁ አለሁ፡ እግዚአብሔር በቅዱሳኑ አፍ እንደተመሰገነ እንዲሁ በእኛም ለዘለዓለም ይመስገን።

# ምዕራፍ ፬

## መልከጼዴቅ ከአብርሃም ወርቅና እጣን ከርቤም ስለመቀበሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለተከበሩት ድንጋዮች ስለአላቸው ምስጢር

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ነጻ አእምሮ ሰጥቶ በምድር ላይ በአለው ሁሉ እንዲሰለጥኑበትና ከተፈጥሮው ከተሰጠው ጸጋ ጋር እንዲጋሩት ለመልካም ፈቀደላቸው።

ነገር ግን የሰው ልጆች ከመልካም ይልቅ ጥፋትን ከንቱነትን በመምረጥ እንዲሰለጥኑበት የተሰጣቸውን ሁሉ አእምሮአቸውን በማቆሸሽ ያመልኩበትና ይሰግዱለት ጀመር።

እግዚአብሔር ከአዘዛቸውና ከፈቀደላቸው ትእዛዝና ህግ እየወጡ በራሳቸው ከንቱ አሳብና ምኞት ወደቁ፡ ከወደቁበት ስህተት እስከ አሁን ብዙዎች አልወጡም፡ ህሊናቸው ደንዝዞ አእምሮአቸው ጨልሞአልና፡ ምክንያቱም የብርሃን ልጆች ሳይሆን የጨለማ ልጆች ሆነዋልና በቀን ብርሃን የሚሄድ እንጂ በሌሊት ጨለማ የሚጓዝ ቢኖር አወዳደቁ የከፋ ነው።

ግእዝን ለምታውቁትና ለምትተረጉሙት በአጭሩ ልግለጽላችሁ፡

"በመዋእሊሁ ለመልከ ጼዴቅ ካህኑ ለእግዚአብሔር ልዑል ዘስሙ ኢትኤል ዘበትርጓሜሁ ጸጋ እግዚአብሔር ዘሀነጸ ሀገረ ኢትዮጵያ ወሰመያ በስሙ ወኩሉሙ ነገሥት ዘነግሡ ላዕለ ይእቲ ሀገር ይሰመዩ ኢትዮጵያውያን በከመ ስመ ሀገሮሙ፡

ወካዕበ ዘነገሡ ሳእሌሃ ከመ ትኩን ስሙረ ብሔር ወሀገሩ በአእባነ ወርቅ ለይእቲ ሀገር ኢትዮጵያ ወበእንተ አእባነ ወርቅ ይቤሉ እስመ ለአድባረ ዛቲ ሀገር አእባኒሃ ኩሎሙ ወርቅ ዘስሙ ዮጵ እንተ ትሰመይ በከመ ስመ ንጉሥ ኢትዮጵ+ ኢትዮጵ ብሂል ጸጋ ወርቅ፡፡ ወእምድህረ ዝንቱ ውሉደ ሱባአ በዓለም ወጠኑ ጣእታተ አእባን ወኮኑ ቀዳሚሆሙ ክሲጦን ወሔሉዶን፡ ወበዝሁ ውሉደ ሱባአ ላእለ ምድር ወበዝሀ እከየ ግብሮሙ እስመ ውእቶሙ ኢኮኑ ሎሙ ህገ ወሥርአት፡ ወኢመምሀራን ዘመሐርዎሙ ወኢአሐዱ ዘይኴንን በበይናቲሆሙ ወበእንተ ዝንቱ ጠፍኡ ወርህቁ እምፍኖተ እግዚአብሔር፡፡"

የሴም ዘር የሆነው አብርሃም ለእግዚአብሔር አገልጋይ ካህን ለሆነው ለካም ዘር ለመልከ ጼዴቅ ከአባቶቹ የተረከበውን ወርቅና እጣን ከርቤ ከአዳም አጽም ጋር ሰግዶ አስረከበው፡ እንዲሁም ከአለው ሁሉ አሥራትን አውጥሮ ሰጠው፡ መልከ ጼዴቅም አብርሃምን ባረከው፡ እንደዚህ ሲል፡-"አብርሃም ሰማያትንና ምድርን ለፈጠረና ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው፡ ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው አለው፡፡

"ወመጽአ መልከ ጼዴቅ ካህነ እግዚብሔር ልዑል ወተቀበሎ ለአብርሃም በፍሥሐ ወአፍጠነ አብርሃም ሰበ ነጸሮ ለመልከ ጼዴቅ ወሰገደ ሎቱ ወመልከ ጼዴቅ ባረከ ላእለ አብርሃም በረከተ ሠናያተ ወአብርሃም ወሀቦ ለመልከ ጼዴቅ ወርቀ ወእጣነ ወከርቤ ምስለ አጽመ አዳም ወአሥራተ እምኩሉ ዘሀሎ ምስሌሁ ወእምድህረ ዝንቱ አብርሃም ተቄረበ እምነ መልከ ጼዴቅ እምስጢራተ ቅድሳት ዘመልከ ጼዴቅ ቀደሰ በእደዊሁ እስመ ውእቱ ካህነ አቢይ እኮ በእደ ብእሲ አላ ትብእሉ እምእግዚአብሔር እምላክ፡፡

ወእምድህረ ተቄረበ አብርሃም እመልከ ጼዴቅ ይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ኢትፍራህ አቢየ ፍርሀተ በቅድሜየ ወበመልከ ጼዴቅ ካህንየ ዓቢይ ባረከ ላእሌከ ወረሰይከ ህቡረ ምስሌሁ በምስጢራት ቅድሳት አነ እሬስየከ ህቡረ

መንበሩ በዚያ ሰማያት ወሀቦ ይቤሎ እግዚአብሔር ለአብርሃም ባርኮ አነ አባርከከ ወአብዝኆ አስተባዝኆ ዘርአከ ላዕለ ገጸ ምድር"

ወተርፈ መልከ ጼዴቅ ህዳረ ውስቴታ ለደብረ ቅድስተ ሀገረ ኢየሩሳሌም ወነገሥት ይመጽኡ ኀቤሁ ወይትባረኩ እምኔሁ እስከ እለተ ፍልሰቱ ወተፍጸሜተ ህይወቱ ውስተ ዝንቱ ዓለም።

አብርሃም በመልከ ጼዴቅ ከተባረከና ከአባቶቹ የተሰጠውን አደራ ከአለው ሐብት ሁሉ አውጥቶ አሥራቱን ከከፈለ በኋላ በሰላም ወደ ኬብሮን ተመለሰ።

እንደዚህም ሆነ፡ የእግዚአብሔር ካህን መልከ ጼዴቅና ሦስቱ ልጆቹ ሃ.ኑ ወደሚባለው ሥፍራ ደርሰው ሰማያትንና ምድርን ለሚገዛ ለኤልሻዳይ የእህል መስዋእት አቅርበው የእግዚአብሔርን ስም ጠርተው በዜማ ከቀደሱት በኋላ የእጣ ክፍላቸውን አገር ለይተው ያውቁ ዘንድ እንደዚህ አደረጉ።

የእግዚአብሔር ካህን መልከጼዴቅ ከአብርሃም የተቀበለውን እንቁአርያ ወርቅና ህብስት የሚይዘውን መሶበወርቅ የወይን ውኃ የሚይዘውን የሕያኤልና የእንቁሐይ ጽዋ ከሦስት መድበው በእጣ ተካፈሉ፡ የእንቆአርያ ወርቅን ለኢትኤል በሕያኤልና በእንቁሐይ የተሰራው የወርቅ ጽዋን ለሃሙኤል፡ የመሶብ ወርቁን ለአቤሜሌክ ስለደረሳቸው ድርሻቸውን ወሰዱ።

አባታቸው የእግዚአብሔር ካህን መልከጼዴቅ የአዳምን አጽምና ከእግዚአብሔር መልእክ ለአዳም የተሰጠውን ወርቅና እጣን ከርቤ የሰላሙ ንጉሥ እስከሚነግሥ ድረስ በክህነት እጅ ይቆይ ዘንድ ያለእጣ ወስዶ በክብር አስቀመጠው፡ እርሱም ከራማ ተራራና

ከኮሬብ ዋሻ መካከል በሚገኘው ሸሰቆ ውስጥ ሄዶ ተቀመጠ፡ አንዳአንድ ግዜም በራማ ተራራ ለእግዚአብሔር መሥዋእት ይቀርብ ነበር፡፡

የክህነቱ ስም ኢትኤል የተባለው ኢትዮጵ በኮሬብ በአለው አለት ላይ ለእግዚአብሔር የእህል መሥዋእት የሚያቀርቡበት ትልቅ ድንጋይ አስፈለፈለ፡ ስሙንም በሚስቱ ስም እንቁዮጵ ብሎ ሰየመው፡፡

ኢትዮጵ ግዮን በተባለው በአንኤል ወንዝ ዳርቻ ስሙ ፔካ የተባለ የድንጋይ መንበር አስቀምጦአል፡ የልጅ ልጆቹ በሚነግሱበት ሥርአት ላይ በድንጋዩ ላይ ሆነው ቅባአ መንግሥት እንዲቀቡበትና የፀሐይ ብርሃን እንዲሞቁበት ለማሳሰቢያ አስቀምጧል፡ ስሙንም የእግዚአብሔር ድንጋይ ለማለት አባንኤል ብሎታል፡፡

ቤቤባንያ ጥሀተብርሃን እብነራእይ ጥሀተ ሰማይ የሚባል ባለአራት ማእዘን ድንጋይ አለ፡ መልኩ ቀይ ደም መስሎ ዘይት የፈሰሰበት ይመስላል፡፡

“ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ወጥቶ ወደ ካራን ሄደ፡ በዚያም ስፍራ ድንጋይ አንሣና ከራሱ በታች ተንተርሶ ተኛ፡ ሕልምም አለመ፡ እነሆም መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ ራሱም ወደሰማይ ደርሶ እነሆም የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር፡ እነሆም እግዚአብሔር በላይ ቆሞበት ነበር፡ እንዲህም አለ፡ የአባትህ የአብርሃም አምላክ የይስሃቅም አምላክ፡ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፡

ይህቺን አንተ የተኛህባትን ምድር ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁ - - -

እነሆም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፣ በምትሄድበት መንገድ ሁሉ እጠብቅህ አለሁ፣ ወደዚህም ምድር እመልስህ አለሁ፣ የነገርሁህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና ያዕቆብ ከእንቅልፍ ተነስቶ በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው፣ እኔ አላወኩም ነበር አለ፣ ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራ፣ ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፣ ይህም የሰማይ ደጅ ቤባንያ ነው።

ያዕቆብ ማልዶ ተነሣ፣ ተንተርሶት የነበረውን ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመው፣ በላዩም ዘይት አፈሰሰበት፣ ያዕቆብም ያንን ስፍራ ቤቴል /ቤትኤል/ ብሎ ጠራው፣ አስቀድሞ ግን የዚያች ስፍራ ሎዛ ነበር። ዘፍ.28፥10

ያዕቆብ ድንጋይን /ቤቤባንያን/ ወስዶ ሐውልት አቆመ፣ ያዕቆብም ልጆቹን ድንጋይ ሰብስቡ አላቸው፣ እነርሱም ድንጋይ ሰብስበው ከመሩ፣ በድንጋዩ ክምር ላይ በሉ፣ ላባም ይጋር ሠሀዱታ ብሎ ጠራት፣ ያዕቆብም ገለአድ አላት። ላባም ይህች ምድር በእኔና በአንተ መካከል ዛሬ ምስክር ናት አለ። ዘፍ. 31፥45

እንደዚህም ሆነ፣ ሙሴ በመንገድ ላይ ባደረበት ስፍራ እግዚአብሔር ተገናኘው፣ ሊገድለውም ፈለገ፣ ሲፓራም ሚስቱ ባልጩት /ሕብነ እዝህ/ ወሰደች፣ የልጅዋንም ሸለፈት ገረዘች፣ ወደሙሴ እግርም ጣለችው፡- አንተ ለእኔ የደም ሙሽራ ነህ አለች፣ ከእርሱም ፈቀቅ አለ፣ የዚያን ጊዜ ስለግርዛቱ አንተ የደም ሙሽራ

ነህ አለች፡፡ ዘጸ.4፥24 ምክንያቱም ሙሴ በግብጻዊነቱ አልተገረዘም ነበርና፡፡

እግዚአብሔርም ሙሴን በህዝቡ ፊት እለፍ ከእስራኤል ሽማግሌዎችን ከአንተ ጋር ውሰድ፡ ወንዙንም የመታህባትን በትር በእጅህ ይዘሃት ሂድ፡ እነሆ እኔ በዚያ በኮሬብ በዓለት ላይ በፊትህ እቆማለሁ፡ ዓለቱንም ትመታለህ ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከእርሱ ውኃ ይወጣል አለው፡ ሙሴም በሽማግሌዎች ፊት እንዲህ አደረገ፡ ዘጸ.17፥5

"ሙሴም እንደታዘዘ በትሩን ከእግዚአብሔር ፊት ወሰደ፡ ሙሴና አሮንም ጉባኤውን በድንጋዩ ፊት ሰብስበው፡- እናንተ ዓመፀኞች እንግዲህ ስሙ በውኑ ከዚህ ድንጋይ ውኃን እናወጣላችኋለን? አላቸው፡ ሙሴም እጁን ዘርግቶ ድንጋዩን ሁለት ጊዜ በብትሩ መታው፡ ብዙም ውኃ ወጣ፡ ማህበሩም ከብቶቻቸውም ጠጡ፡፡ ዘኁ:20፥10

የድንጋዩንም መሠዊያ ብታደርግልኝ ብረት በነካው ድንጋይ አትሥራው፡ በመሣሪያ ብትነካው ታረክሰውአለህና፡ ዘጸ.20፥25

እግዚአብሔር ብቻውን መራው ከእርሱም ጋር ሌላ አምላክ አልነበረም፡ በምድር ከፍታ ላይ አወጣው፡ የእርሻውን ፍሬ በላ፡ ከዓለትም ድንጋይ በሚገኝ ማር ከጭንጫውም ድንጋይ በሚገኝ ዘይት አጠበው፡፡ ዘዳ.32፥12

በአባቱ ስም በኦሪ መጽሐፍተ ኦሪት እንዲባሉ የአደረገና ከሙሴ አማት ከዮቶር አብ የወሰዱትን የአባቶችን ዜና

የሚገልጹትን መጻሕፍት የጻፈ እንዲሁም እግዚአብሔር የአዘዘውን ሁሉ ከሙሴ አፍ በመስማትና በማየት ይጽፍ የነበረውን የአሪን ልጅ እግዚአብሔር ሙሴን እንደዚህ ሲል መረጠው።

"እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡ እይ ከይሁዳ ነገድ የሚሆን የሆር የልጅ ልጅ የኡሪት ልጅ ባስልኤልን በስሙ ጠርቼው አለሁ፣ በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብም በማስተዋልም በእውቀትም የእግዚአብሔርን /ወልድ/ መንፈስ ሞላሁበት፣ የጥበብንም ሥራ አስተውል ዘንድ በወርቅና በብር በናስም ይሠራ ዘንድ ለፈርጥ የሚሆነውን የእንቁ ድንጋይ ይቀርጽ ዘንድ እንጨቱንም ይጠርብ ዘንድ ሥራውንም ሁሉ ይሠራ ዘንድ ጥበብን አኖርሁ። ዘጸ. 31፥1

እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው። ዘጸ. 31፥18

ሙሴም ተመለሰ ሁለቱንም የምስክር ጽላቶች በእጁ ይዞ ከተራራው ወረደ፣ ጽላቶቹም በዚህና በዚያ በሁለት ወገን ተጽፎባቸው ነበር፣ ጽላቶቹም የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ፣ ጽሕፈቱም በጽላቶቹ ላይ የተቀረጸባቸው የእግዚአብሔር ጽሕፈት ነበር።

እንዲህም ሆነ፣ ወደሰፈሩ ሲቀርብ ጥጃውንም ዘፈኑንም አየ፣ የሙሴም ቁጣ ተቃጠለ፣ ጽላቶቹንም ከእጁ ጥሎ ከተራራው በታች ሰበራቸው፣ የሠሩትንም ጥጃ ወስዶ በእሳት አቀለጠው፣

እንደትብያም እስከሚሆን ድረስ ፈጨው፡ በውኃውም ላይ በተነው፡ ለእስራኤል ልጆች አጠጣው። ዘጸ. 32፥15

እግዚአብሔር ሙሴን አለው፡- ሁለት የድንጋይ ጽላቶች እንደፊተኞች አድርገህ ጥረብ፡ በሰበርሃቸው በፊተኞች ጽላቶች የነበሩትን ቃሎች እጽፍባቸዋለሁ፡ ነገም የተዘጋጀህ ሁን፡ በማለዳም ወደሲና ተራራ ወጥተህ በዚያ በተራራው ራስ ላይ በፊቴ ቁም አለው።

ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ፡ ወደሲና ተራራመ ወጣ፡ ሁለቱንም የድንጋይ ጽላቶች በእጁ ወሰደ፡ እግዚአብሔርም በደመናው ውስጥ ወረደ፡ በዚያም ከእርሱ ጋር ቆመ፡ የእግዚአብሔርንም ስም አወጀ።

እግዚአብሔርም ሙሴን በእነዚህ ቃሎች መጠን ከአንተና ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን አድርጌአለሁና፡ እነዚህን ቃሎች ጻፍ አለው፡ በዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ። እንጀራም አልበላም ውኃም አልጠጣም በጽላቶቹም አሥሩን የቃል ኪዳን ቃሎች ጻፈ። ዘጸ. 34፥1-29

ኢያሱም ለህዝቡ፡- እነሆ የተናገረንን የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ ሰምቶአልና ይህ ድንጋይ ይመሰክርብናል፡ እንግዲህ አምላካችሁን እንዳትክዱ ይህ ምስክር ይሆንባችኋል አላቸው። መ/ኢያሱ 24፥27

ይህም በመካከላችሁ ምልክት ይሆናል፡ ልጆቻችሁም በሚመጣው ዘመን የእነዚህ ድንጋዮች ነገር ምንድነው? ብለው

ሲጠይቁአችሁ እናንተ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦት ፊት የዮርዳኖስ ውኃ ስለተቋረጠ ነው፤ ዮርዳኖስን በተሻገረ ጊዜ የዮርዳኖስ ውኃ ተቋረጠ፤ እነዚህም ድንጋዮች ለእስራኤል ልጆች ለዘለዓለም መታሰቢያ ይሆናሉ ትሉአቸዋላችሁ። መ/ኢያሱ 4፥6

ሳሙኤልም አንድ ድንጋይ ወስዶ በምጽጳና በሼን መካከል አኖረው፤ ስሙንም እስከ አሁን ድረስ እግዚአብሔር ረድቶናል ሲል አቤንኤዘር ብሎ ጠራው። ሳሙ.ቀ. 7፥12

ዳዊት እጁን ወደኮሮጆው አግብቶ አንድ ድንጋይ ወሰደ፤ ወነጨፈውም ፍልስጥኤማዊውንም ግንባሩን መታ፤ ድንጋዩም በግንባሩ ተቀረቀረ፤ እርሱም በምድር ላይ በፊቱ ተደፋ።

ዳዊትም ጐልያድን በወንጭፍና በድንጋይ አሸነፈው፤ ፍልስጥኤማዊውንም መትቶ ገደለ፤ በዳዊትም እጅ ሰይፍ አልነበረም፤ ዳዊትም ሮጦ በጐልያድ ላይ ቆመ፤ ሰይፉንም ይዞ ከሰገባው መዘዘው፤ ገደለውም ራሱንም ቀረጠው። ሳሙ.ቀ/ 17፥49

እግዚአብሔር ዓለቴ፥ አምባዬ፥ መድኃኒቴ፥ አምላኬ፥ በእርሱም የምተማመንበት ረዳቴ መታመኛዬና የደህንነቴ ቀንድ መጠጊያዬም ነው። ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ። መዝ. 1፥72

ልቤ ተስፋ በቆረጠ ጊዜ ከምድር ዳርቻ ወደ አንተ እጮሀለሁ፤ በድንጋይ ላይ ከፍ ከፍ አደረግኸኝ። መዝ.60፥2

ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፡ ለዓይናችንም ድንቅ ናት። መዝ. 117፥22

ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ በጽዮን ድንጋይን ለመሰረት አስቀምጣለሁ፡ የተፈተነውን የከበረውን መሠረቱ የጸናውን የማእዘን ድንጋይን የሚያምንም አያፍርም። ኢሳ. 28፥16

አንቺ የተቸገርሽ በአውሎ ነፋስም የተናወጥሽ ያልተጽናናሽም እነሆ ድንጋዮችሽን ሸላልሜ እገነባለሁ፡ በሰንፔርም እመሰርትሽ አለሁ፡ የግንብሽንም ጉልላት በቀይ እንቁ በሮችሽንም በሚያብረቀርቅ እንቁ ዳርቻሽንም ሁሉ በከበሩ ድንጋዮች እሠራአለሁ። ኢሳ. 54፥11

እኔም እንደጉልበቴ ሁሉ ለአምላኬ ቤት ለወርቁ ዕቃ ናሱን ለብረቱም ዕቃ ብረቱን ለእንጨቱም ዕቃ እንጨቱን ደግሞም መረግድንና በፈርጥ የሚገባ ድንጋይን የሚለጠፍ ድንጋይን ልዩ ልዩ መልክ የአለውንም ድንጋይ የከበረውንም ድንጋይ ከየዓይነቱ ብዙም እብነበረድ አዘጋጅቼአለሁ። ዜና መ/ቀ. 29፥2

ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰው ይመስላል። ማቴ.7፥24

መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ፡ ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠው አለሁ፡ ነጭ ድንጋይንም እሰጠው አለሁ፡ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር

አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል። የዮሐ.ራ. 2፥17

መጽሐፈ ጥበበ ዕንቆ አእባን ብዬ የሰየምኩትን መጽሐፍ ጽፌና አሳትሜ የአቀረብኩት ለእናንተ ለኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያን እንደዓይናችሁ ብሌን ለምትጠብቋት እንደ ህይወታችሁ አንድርጋችሁ ለምታስቡዋት ለእውነተኛ ልጆችዋ እንጂ ለዲቃላዎችና ለእንጀራ ልጆችዋ እንደነሱም የታሪኩዋን አይን ለሚያጠፉና ለሚሸነቁሩዋት አይደለም። ስለዚህ መጽሐፉ አንድ ግዜ ታትሞ ከእናንተ ከደረሰ በኂላ ድንገት ስለሚቆይም- በክብር ገዝታችሁ ለሚፈላሰፉ ልጆቻችሁ ወይም አገሩንና ሕዝቡን ለሚወድ ትውልድ አስቀምጡት ግን ለአፍ ወዳጅ ለልብ ጠላት አትስጡት፡ ስለዚህ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ሲል አስተምሮናል።

"በእግራቸው እንዳይረግጡት ተመልሰውም እንዳይነክሱአችሁ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፡ ዕንቁቻችሁንም በዕሪያዎች ፊት አትጣሉ። ማቴ. 7፥6"

"እርሱ ግን ወደ እነርሱ ተመልክቶ እንግዲህ ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፡ ተብሎ የተጻፈው ይህ ምንድር ነው? በዚያም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ ይቀጠቀጣል፡ የሚወድቅበትን ሁሉ ግን ይፈጨዋል አለ። ሉቃ. 20፥17

# ምዕራፍ ፰

## ጥበበሰንቶ ወእእባን
## የድንጋዮችና የእንቁ ጥበብ

የልቤ ሰው ወዳጄ ሆይ በእግዚአብሔር እንጂ በራስህ ሳትመካ የጥበብን በር አስቀድመህ አንኳኳ፣ ይከፈትልሃል ትገባለህ፤

አስተውለህ መርምር ታውቃለህ፤
ጠንክረህ ፈልግ ታገኘው አለህ፤
ስውር የሆነው የጥበብ ምስጢር ይገለጽልሃል ታየውአለህ፡ ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ነው፡ የእግዚአብሔርን ስም በክብር ሳታነሣና ሳታመሰግን አንዳች ነገር አትጀምር፡ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን ማወቅና መፍራት ነው፣ እርሱም የእግዚአብሔርን ትእዛዛት መፈጸም ነው፡ በእግዚአብሔር እንደታመንክና እግዚአብሔርን እንደወደድክ ፍቃዱንም እንደፈጸምክ በዚህ ፍጹም እምነትና መልካም ስራ ሁሉ ይገለጻል። ስለዚህ እግዚአብሔር ደግሞ የወደደውን ይመርጠዋል፡ ጸጋውንም ይሰጠዋል፡ ለተጋ አእምሮውን ያበራል፡ የሰጠውን አእምሮ ከቀን ወደቀን በመንፈሱ ያነጻዋል ያድሰዋልም፡ የእግዚአብሔር ቸርነትና ፈቃድ ለዘለዓለም በሕይወታችን ላይ ነግሷል፡ ክብሮአልም፡ እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ሰውን በመልኩ እንደምሳሌው ወደ ፈጠረ፡ ፈጥሮም በፈጠረው ፍጥረት ላይ የተሰጣቸውን የተፈጥሮ ባህርይ እንዲጋራቸውና እንዲሰለጥንባቸው ነጻ አእምሮ ሰጥቶ ፈቀደለት፣ ሰጠውም፡ አልከለከለውም ነገር ግን ገደብ እንዲኖረው አደረገ፡ ምክንያቱም ፈጽሞ እንዳይጠፋ በገደቡ ጠበቀው እንጂ

አንተም የእግዚአብሔር ሰው የሰው ፊቱ ነህና ታስተውል ትመረምር ዘንድ ተፈቅዶልሃል፡ ተሰጥቶሃልም፡ ነገር ግን እንዳትጠፋ ተጠንቀቅ። ከእግዚአብሔር መንገድ እንዳትወጣ ፈቀቅም እንዳትል፤ ትምክህት ወደአለበት ወደ ከንቱ ፍልስፍና እንዳታዘነብል፤ እግዚአብሔር ሲፈትንህ በፊትህ መልካምን ሕይወትና የጥፋት ቅጣትን አስቀምጦብሃልና በተሰጠህ አእምሮ ለይተህ መምረጥ የአንተ ነው።

እግዚአብሔር የሚወደውን መልካም ነገር ለመምረጥ ያብቃህ፡ ያብቃሽ፡ የእግዚአብሔር ጸጋና እርዳታ አይለያችሁ፡ ምንግዜም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፡ ፍቅሩንና ሰላሙን ይስጠን፡ ሕዝባችንን በአንድነት ያቁምልን፡ አገራችን ኢትዮጵያን ይጠብቅልን፡ አሜን።

**ከመሪራስ አማን በላይ ታስተውሉ ዘንድ የተጻፈ።**

"ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እነሆ በጽዮን ድንጋይን ለመሰረት አስቀምጣለሁ፡ የተፈተነውን የከበረውን መሠረቱ /ተዋህዶ ሃይማኖት/ የጸናውን የማዕዘን ድንጋይ የሚያምንም አያፍርም። ኢሳ. 28፥16

ድል ለነሣው ከተሰወረ መና /መሥዋዕትን/ እሰጠውአለሁ፡ ነጭ ድንጋይንም /ታቦት/ እሰጠው አለሁ፡ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል። የዮሐ.ራ. 2፥17

1ኛ/ ዕንቋዕ ዕንቋዕ አሰይ አሰይ፣ እንቁ እንኩ አልማዝ የከበረ ድንጋይ ከድንጋዮች መካከል የነጠረ መልኩ እንደ መጽሔት እንደመስዊት የጠራ የተፈጥሮው ባሕርይ የሚያንጸባርቅና የሚያስደስት ነው፡ ስሙም እንቆዮጳዝዮን ብሂል እንቆባህርይ ይባላል። እብነ ሰንፔር የከበረ ድንጋይ ማለት ነው፤

2ኛ/ አበነ፣ ደነገየ ጠነከረ ድንጋይ ሆነ ካለው አባኔ ጥንክርና እብን ጠንካራ የሆነ እብነ ኩክህ ነው።

"እኔም እልሀአለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያንን እሠራለሁ፡ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም፡ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻዎች እሰጥሀአለሁ፡ በምድርም የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሠረ ይሆናል፡ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል። ማቴ. 16፥18

ደቀመዛሙርቱን በድንጋይ ስለመሰሉ "መምህር ሆይ ደቀ መዛሙርትህን ገሥጻቸው አሉት፡ መልሶም፡- እላችኋለሁ፡ እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮኻሉ አላቸው። ሉቃ. 19፥40"

1. **ኣዉፋ - ኣ** ፡- የመጀመሪያው አርአያና አምሳል የሆነው **ነጭ** ድንጋይ ነው፡ በሮሃ ድንጋይ ጠርበህና አለስልሰህ የእግዚአብሔርን ስምና እግዚአብሔር የሚወደውን ትእዛዛቱን ጻፍበትና በምትጸልይበት ቦታ በክብር አስቀምጠው፡ እግዚአብሔር ስእለትህን ይፈጽምልሃል።

ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠወ እለሁ፡ ነጭ ድንጋይ፤ እሰጠው እለሁ፡ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል። የዮሐ.ራ.2፥17

ጳ የተባለው ድን ይ መልኩ የተነደፈ ጥጥ ወይም የተከመረ በረዶ ይመስላል፡ ንጣቱ በጣም የደመቀ ነው፡ እርሱን እስጠርበህ ጽላት አድርገህ የእግዚአብሔርን ስም ብትቀርጽበትና አስሩን ትእዛዛት ብትጽፍበት በክብርም ብታስቀምጠው ከምትፈራው ነገር ይጠብቅሃል፡ ስእለትክንም ይፈጽምልሃል፡ የእግዚብሔር በረከት ድንጋዩ በአለበት ይኖራል።

2. **ሸኝ** :- የኖረና የሚኖር የሰው አምሳል የሆነ ድንጋይ ነው፡

ይህ ድንጋይ እንደ ሙዳይ ወይም እንደ አገልግል መስሎ ክብ ነው፡ ዙሪያውን በቀይ በአረንጓዴ ቀለም የተከበበና የተሸለመ ነው፡ በየጊዜው ሲያዩት ለዓይን እንግዳ ነው፡ ይታደሳል፡ በዚህ ድንጋይ ላይ የእግዚአብሔርን ስም ከላይ የአገሩን ስም በታች በምታስቀምጥበት ቀርጸህ ጽፈህ ሐውልት ሰርተህ ስትጨርስ መደምደሚያ አድርገው፡ እንደዚህ አድርገህ የአስቀመጥከው እንደሆነ ከተማህ ደማቃ ሰላም የበዛበት ሰው የማይቸገርበት ጠሙን የማያድርበት ይሆናል፡ ለሰው ሁሉ ፍቅርንና ሰላምን እድሜንና ጤናን ሐብትንና በረከትን የሚያድል ነው። ለዚህ ድንጋይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠውን ጸጋ የሰው ልጆች እንዲጋሩትና እንዲጠቀሙበት እግዚአብሔር አስቀድሞ ሳይሆን ፈቅዶአል፡ በዚህ የእግዚአብሔር ምስጢር አለ፡ የእግዚአብሔር

ጥበቡን ለአስተዋለና ለተመራመረ ግን ምስጢሩ ግልጽ እንዲሆን እግዚአብሔር ፈቅዶአል፡ በዚህ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ታውቆ ከበረ፡፡

3. **እየን - ኳእ** ፡- ድንቅ ድንጋይ ነው፡ በግእዙ እጉለ ቤተመስቀል ይባላል፡ ግማደ መስቀል የሆኑ አራት ቀዳዳዎች አሉት፡ በቀዳዳዎች ውስጥ የቢጫ ወርቅ ሐብል አስገብተህ ብትይዘው የአየህ ሁሉ ያከብርሃል፡ በነጭ ወርቅ ሐብል አስገብተህ ተንተርሰህ የተኛህ እንደሆን ኖህተ ገነት ተከፍቶ ታያለህ፡ የእግዚአብሔር ክብር በሩቅ ያሳይሃል፡ ሰው ነፍስና ስጋው ሲለያይ ከአለት ውስጥ ከወጣ ፀበል ጋር አሳድረህ በበድኑ አፍንጫ ፀበሉን በቀዳዳው አሳልፈህ ክተትበትና ከወገቡ ላይ እሰርለት፡ አይፈርስም፡ አስደናቂ የሆነ ክቡር ድንጋይ ነው፡፡

በዚህ የድንጋዮች ጥበብ ይከብራል፡ ጥበብ ለአእባን የሚለውን ቃል ሰሚ የሆነ የአስተውል፡ አይቶም ይመልከት፡ እግዚአብሔር ለፈጠረው ሁሉ እንደ እጣ ክፍሉ ጸጋውን ሰጥቶታልና፡ የሰው ልጆችም የሌላውን እድል ለመጋራት ነጻ አእምሮ ተሰጥቶአቸዋል፡ መምረጥ የራሳቸው ነው፡፡

4. **ቶእ** ፡- ተስፋን የሚፈጽም የእግዚአብሔርን ቸርነት የሚያሳይ እብነ መለኮት ይባላል፡ መልኩ ቀያቴ ነጭ ነው፡ ብዙ ግዜ ከምድር ውስጥ ነው የሚገኘው ይህ ድንጋይ ባለበት የሚመነጭ ውኃ የፈሳ ይሆናል፡ ከምንጩ ድንጋዩ ራቅ ያለ ከሆነ ውኃው ሳብ ያለ ይሆናል፡ በእጅህ ብትነካው ያቃጥልሃል፡ በጉጠት

አውጥተህ እንደዝብታ ጥረበው፡ ይጠረባል፡ ለታቦት ብታደርገው በዚያ የእግዚአብሔር በረከትና ረድኤት ይታያል፡ ልብስ አታልብሰው፡ በእንጨት ላይም አታስቀምጠው፡ ያቃጥለዋል፡ ነገር ግን በድንጋይ ጠረጴዛ በድንጋይ መንበር ላይ አስቀምጠው፡ እሱ ባለበት ሁሉ የአለው እቃ ይሞቃል፡ ክቡር የሆነ እብነ መስኮት የተባለ ነውና አክብረህ ያዘው፡ በእርሱም ብዙ የድንጋይ ጥበብ አለ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በአለበት ሁሉ የጥበብ ምስጢር አለና የድንጋዮችና የዕንቁ ጥበብ እስተውሎ ለተመራመረ ተመልክቶም ለአየና ላወቀ ብልህ ሰው የጥበብ ምስጢር ተገለጠ፡ ስለእርሱ ማስተዋል ጥበብም ከበረች ከፍ ከፍም አለች፡፡

5. **ኧማን -ኧኤ** የተማነ ድንጋይ አማንኤል

"ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ፡ ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች /ጥበብ/ ለዓይናችንም ድንቅ ናት፡፡ መዝ. 117፥22

ከእኛ ጋር ሰው የሆነውን አምላክ ምሳሌው ሆኖ የተነገረለት የማእዘን መደምደሚያ ድንጋይ ነውና፡ ለታቦት የሚሆን የታመነ ድንጋይ ነው፡፡ ሰው ጠርቦ የተወው ይመስላል፡ አልፋ ኦሜጋ ብለህ ጻፍበትና በክብር አኑረው፡፡

6. **ኣኤ - ስቤኔዘር** ፡ ሳሙኤል ያቆመው ድንጋይ ነው፡ ቁመቱ ሁለት ክንድ ይሆናል፡ አራት ማዕዘን አለው፡ በደጋ አገር ከስታ መካከል ታገኘው አለህ፡ ነጭ ቦረንቅ ይመስላል፡ እንባህን አገርህን አዙረህ ብትተክለው ጠላት ከወሰንክበት ቦታ አያልፍም፡ አውሬም

እንዲሁ፡ ሳሙኤል እግዚአብሔር ረዳኝ ሲል አቤንኤዘር ብሎ በምጽጳና በሴን አቆመው።

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ እነሆ በጽዮን ድንጋይን ስመሰረት እስቀምጣለሁ፡ የተፈተነውን የከበረውን መሠረቱ የጸናውን የማእዘንን ድንጋይ የሚያምን አያፍርም" ተብሎ ለክርስቶስ የተመሰለው ይህ ነውና።

7. **ኰደኸ - ኰደኸ** መእዛ ያለው ድንጋይና እስፌሊጦስ ሙሜ የእለው ለቀለም ቅጥራን የእለው ድንጋይ ነው፡ ኰደኸና እስፌሊጦስ የተባሉትን የድንጋይ አፈርና ሙሜዎች በአንድ ላይ ወቅጠህ ለጥቁር ቀለም ቀንድ አሳርረህ ጨምርበት፡ ለቀይ ቀለም የደጋ ቀይ አፈር። ለቢጫና ለአረንጓዴ እንቁላል ቢጫ አፈርና አረንጓዴ አፈር የወይን ጠጅ ዋርዴ አፈር ኩል እኩል በእኩል አዘጋጅተህ አቡካውና በጥብጠህ አጥለውና እስከሚደርቅ አቆየውና እንደገና በፈላ ውኃ ለውሰህ ከምድጃ በታች ቅበረውና በሶስት ወሩ አውጥተህ እየበጠበጥክ ጻፍበት፡ በዚህ መልክ የቀለም ዓይነቶችን ማዘጋጀት ትችልአለህ። እንዲሁ የመረጥከውን የቀለም መልክ ዓይነት ካዘጋጀህ በኋላ ለሐውልት ወይም ለህንጻ ከተዘጋጀ ከድንጋይ ዱቄት ጋር አቡክተህ ሥራው፡ ለምሳሌ ከሸክላ አፈር ጋር አቀላቅለህ ብትለውሰውና የሸክላ እቃ ብትሰራ መልኩ አንተ እንደመረጥከው ቀለም ይሆንልሃል። በዚህ ዓይነት ብዙ የእጅ ሥራዎችን መፍጠርና ማሳመር ትችልአለህ። እስተውለህ መፈላሰፍ መርምረህ ማወቅ

የአንተ ግዴታ ነውና ተማምነህ አድርግ ይሆንልሃል፣ የእግዚአብሔር ፍቃድ ከእምነትህ ጋር ነውና።

8. **ዓጼ** :- ጥሩ ድምጥ የአሰው ድንጋይ ነው፣ ኢል ፪ ብሎ ጠርቶ አሳብገና ምኞትን ተናግሮ በድንጋይ ቢወቅሩት የተመኙትን የሚፈጽም የአማረ የደወል ድንጋይ ነው።

የተጣሉትን ሰዎች ስማቸውን አንስተህ ደውልና ታረቁ በሳቸው፣ ይታረቃሉ፣ በመካከላቸው ቂም ይጠፋል፣ ዳግመኛ አይጣሉም። ይህ ድንጋይ መልኩ የምናየውን ቡላ መስሎ እንደውጋግራ ረጅም ነው፣ ድምፁ አንድ ግዜ ስትመታው ተደጋግሞ ይሰማል፣ ስታዳምጠው ልብን የሚነካና የሚያረካ ድምጽ አሰው፣ በእሳት አግለህ ደወል ስትሰራው ጥሩ የደወል ብረት ይሆንልሃል። ነገር ግን ለስእለት ለምኞት ለማስታረቅ አይሆንም፣ ምክንያቱም በእሳት ሲፈተን ከእግዚአብሔር የተሰጠው ጸጋና ኃይል ርቀዋል። እንዳለ በእሳት ሳታግል ተጠቀምበት፣ በዚህ የድንጋዮች ጥበብ ክብሮ ይታወቅልሃል። ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር ነውና በአምላካችን በእግዚአብሔር ተማምነህ አድርግ፣ ይሆንልሃል፣ አእምሮህን ከቀን ወደቀን ያበራልሃል፣ የሰማኸውን ታስተውላለህ፣ ያየኸውንም ትመለከታለህ።

9. **ቶፚ** :- ከውኃ ላይ ሲጥሉት የሚንሳፈፍና ክፍት የሆነ ቀዳዳ የአለው ኩርንችት ድንጋይ ነው፡ በሜዳ በምድረ በዳ ድንጋይ በበዛበት ቦታ ታገኘው አለህ፡ ሰብረህ ስባሪውን በድኩላ ወይም በነብር ጅማት አንጠልጥለህ ብትይዘው አትደክምም፡ የሚደርስብህ የለም፡ እንዲሁ የሰመሬታ ንብስ የአሩጥ ቀንበጥ አበባ ጋር ወቅጠህ በድንጋዩ ቀዳዳ ውስጥ አስገብተህ ከውኃ ላይ አድርገህ አሳድረህ ጠጣ፡ እግርህንም ታሽበት፡ የነብር ጅማት የአሩጥ ጥጥ በአንድ ላይ ገምደህ በእግርህ አሰርና ሩጥ ብዙ ጊዜ ፈጣን ሩዋጭ ትሆናለህ። መጨረሻ ከእግርህ አውጥተህ በዋሻ ውስጥ አንጠልጥለው፡ ሰምርዋጽ ይሆንልሃል፡ ለሌላም ተመሳሳይ ነገር ይሆናልና ተፈላሰፍበት፡ የድንጋዮችና የዕንቁ ጥበብ ምስጢር ይፋ ግልጥ ለአንተ ይሆንልሃል፡ የጥበብን በር እንኳኳ ይከፈትልሃል፡ ምስጢሩዋንም ተግተህ ፈልግ ተገልጾ ታየውአለህ።

10. **ኣፚ** :- መሠረቱ የጸና ድንጋይ ኢያስጲድ፡

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እነሆ በጽዮን ድንጋይን ለመሰረት አስቀምጣለሁ፡ የተፈተነውን የከበረውን መሠረቱ የፀናውን የማእዘንን ድንጋይ የሚያምን አያፍርም፡ ኢሳ.28፥16" የተነገረለት ለኣኢ ድንጋይ ነውና፡ እርሱም ላላመኑት እንቅፋትና መሰናከል ላመኑትና ትእዛዛቱን ለተቀበሉት።

ለሕይወታቸው መሰረት ለሆነው ለእየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሁኖ የተነገረ ኢያስጲድ ድንጋይ ነውና። ይህ ኢያስጲድ ድንጋይ መንበር ወይም ገበታ የመሰለ ሰማያዊ ዋርዳና ደማቃ መልክ ያለው ነው፡ ሰማያዊ እብነበረድ ባለበት አለትና ተራራ ላይ ታገኘው አለህ፡ ለመቅደስ መንበር ለጽላት ገበታ ይሆናል፡ የቤተመቅደስ መሰረት ስትጥል በበላዩ የእግዚአብሔርን ስም ጽፈህ ቅበረው፡ የተጀመረው በቶሎ ያልቃል፡ የእግዚአብሔር ቸርነት ይታይበታል፡ ቅዱሳን የሆኑ መናፍስት አይርቁትም፡ ይጠብቁታል፡ ጠላት ቢመጣም አይደፍረውም፡ በአካባቢው ንብ ይሰፍርበታል፡ በዚህ የድንጋዮች ጥበብ ይከብራል፡ አንተም እንዲሁ እግዚአብሔርን በማመን ጥበብንም በማወቅ ክበር፡ እድሜህ የሰላም ዘመን ይሆንልሃልና።

11. **ሊሊ** ከሀዘን ከመከራ የሚያድንና የሚያስረሣ ሲያዩትና ሲነኩት የሚያስደስት መንፈስን የሚያረካ ከመሆኑ ሌላ፤ ሊሊ - **ሊያስሚር**፡ በጣም የጠራ ነጭ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ ይህ ነጭ ጠንካራ ድንጋይ በውስጡ የተለያዩ ቀለሞች የአሉት አልማዝ ይገኙበታል ለፈርጥ አድርገህ ብታስቀርፀው መልኩ እያደረ ያአምራል፡ ይጠራል እንጂ እድፍ ሌላ ቀለም አያርፍበትም፡ አስተዋይ በሆነ አንጥረኛ እንዲሰራው አድርግ እንጂ እንደሌሎች የሚጣበቅ አይደለም፡ እርሱን በአንገትህ በእጅህ ብታስረው በእድሜህ ዘመን ሐዘን መከራ ችግር አይደርስብህም፡ ሁልጊዜ ደስተኛ ሆነህ ትኖራለህ እንጂ

የሚያሳዝንህ የሚያስከፋህ አይኖርም፣ መስተፍስሒ ልብ ነው፡ ምንግቤም ልብን ያስደስታልና፡፡

12. **ኡድ- ኡ** ፡- የሚያምርና መአዛ የአለው ድንጋይ ነው፣ መልኩ ቀይና አረንጓዴ ነው፣ አልመህ ደቁሰህ ሰውነቱ ለሚቀረና መፕፎ ሽታ ላለበት፣ በውሃ በጥብጠህ በባዶ ሆዱ ይጠጣው፡ እንዲሁ ጠረኑ ለሚለወጥ ነገር ሁሉ ነስንስበት፣ የሆድ ህመም የደም ብዛት ለአለበት ሁሉ ስጠው ይፈውሳል፡ ኡድ ድንጋይ ባለበት ከርቤና የድንጋይ ሙጫ ምልቶአል ከነሱ መሃል ታገኘው አለህ፡ ለሽቶ ዘይት ስትቀምም አብረህ ጨምረው፡ መአዛውን ያሳምርልሃል፡ የድንጋዮችና የዕንቁ ጥበብ በዚህ ተወዳጅና ተፈላጊ ይሆናል፡ አንተም ተፈላሰፍ አዋቂ ፈላስፋ ትባላለህና፡ ትውልድን አስተማሪና መካሪ ትሆናለህ፡ እግዚአብሔር የአዘዘውን ለመፈጸም ችላ አትበል፡፡

በመኃልየ መኃልየ ሰሎሞን እንደዚህ አለ፡- "ቀኑ እስኪነፍስ ጥላውም እስኪያልፍ ድረስ ወደከርቤው ተራራ ወደ እጣኑም ኮረብታ እሄዳለሁ፡ ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው፡ ነውርም የለብሽም፡፡ መኃ.መኃልይ 4፥6"

13. **ቶሎ** ፡- ነጠብጣብ የአለውና በልዩ ቀለም የተሸላለመ ድንጋይ መልኩ እንደነብር ቆዳ ወይም እንደጃርት ሾህ መስሉ በሰው እጅ የተጌጠ የመሰለ ጽሁፍ አለው፡ ጽሁፉን ለአስተዋለና ለተመራመረው በእርሱ ብዙ ምስጢር አለ፡ ቤተ መቅደስን

ወይም ቤተመንግሥትን ስትሠራና ህንጻውን ስትመሰርት የእግዚአብሔርን ስምና ስምህን የአባት የእናትህን ስም የአገሩን ስም በድንጋዩ ላይ በቋንቋህ በራስህ ፊደል አስቀርፀህ ከቀይ ሰንፔር ጋር ከመካከሉ ላይ በክብር ቅበረው፡ ስምህ በክብር ሲጠራ ይኖራል፡፡ የአንተን ስም የሚነቅፍ አምላክህን የማያምን ቢኖር ፈጽሞ ይጠፋል፡ ዘሩም ይነግላል እንጂ አንተ በመሰረትከው ከተማ አይኖርም፡፡

በነቢይ እንደዚህ ይላል "አንቺ የተቸገርሽ በአውሎ ነፋስም የተናወጥሽ ያልተጽናናሽም እነሆ ድንጋዮችሽን ሸላልሜ እገነባለሁ፡ በሰንፔርም እመሠርትሽአለሁ፡ የማንብሽንም ጉልላት በቀይ ዕንቁ በሮችሽንም በሚያብረቀርቅ ዕንቁ ዳርቻሽንም ሁሉ በከበሩ ድንጋዮች እሠራለሁ፡ ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል፡፡ ኢሳ. 54፥11"

14. **ሉዊዐ፡ ኢልዖዩ - ላኤ** - ኃይል የሚሰጥና የሚያበረታ ድንጋይ ነው፡፡ መልኩ ነጣ ያለና ልዝብ ነው፡ ሲያዩት የተጠረበ ገበታ ይመስላል፡ እብነ በረድ መስሎ እንጨት ሳንቃ ይመስላል፡ ይህን ድንጋይ ጠርበህ በንጽህና የፈለከውንና የተመኘኸውን ቃል ጻፍበት፡ ይፈጸማል፡ ለቃሉ ተቃራኒ የሆነ ነገር ከመጣ የሚቀስፍ የሚያጠፋ የሚያቃጥል ረሃብ ችግር የሚያመጣ ይሆናል፡ ከመጻፍህ በፊት ተጠንቅቀህ አድርግ እንጂ የማትወጣውን አትጻፍበት "ታሪክ ፡ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር

በሲና ተራራ የተናገረውን በፈጸመ ጊዜ በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ሰጠው፡ ነገር ግን እንደዚህ ሆነ፡ ወደ ሰፈሩ ሲቀርብ እስራኤል የወርቅ አምላክ ጥጃ አበጅተው ሲያመልኩ ሙሴ አየ፡ ጽላቶቹን ከእጁ ጥሎ ሰባበራቸው፡ እንዲሁ በሌላ ቀን ሙሴ እንደፊተኞች አድርጎ ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጠረበ፡ እግዚአብሔርም የእግዚአብሔርን ስም አወጀ።"

15. **ኊኌ - ሑዋ - ሕዩዐ** ፡- በመንፈስ ሰመነጠቅ ተንተርሶ መተኛት ወይም በበላዩ ላይ ስሙን በአራት ማእዘን ጽፎ የሐውልት መሰረት ማድረግና ማነፅ ስሙ ለመታሰቢያ ይሆናል እንጂ አይጠፋም። በመቃብሩም እንዲሁ ማድረግ ነው።

"የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል፡ መዝ.111፥6"

የተባለለት በዚህ ድንጋይ ስማቸው ለተመዘገበ ነውና እርሱም የክርስቶስ ምሳሌ ድንጋይ ነው። "ኊየል፡ ኊዋ" ብለህ ጽፈህ በመቀመጫህ የአደረከው እንደሆነ ትከብርበት አለህ። "ኊዋ ኊየል" ብለህ ጽፈህ ተንተርሰህ ከተኛህ መጭውን በራእይ ታየው አለህ፡ መክሰተ ራእይ ነው፡ መልኩ ቢጫ ሰማያዊ ወይም የሎሚ ወይም የብርቱካን መልክ ይመስላል። ትንሽም ትልቅም አለው፡ ነጭ አፈር ባለበት ይገኛል፡ እንዲሁ ላዩ ጥቁር ወይም ቀያቴ ቡላ አፈር ሁኖ ወደ መሬት ውስጥ ቢጫ አረንጓዴ የሆነ አፈር ባለበት ታገኘው አለህ፡ ለሁሉም መልካም ነው፡ በመኖሪያህ በመሰለህ ቅርጽ አስጠርበህ ስምህን ጽፈህ አስቀምጠው፡ በበላዩ

የእግዚአብሔርን ስም፣ "ኤልሻዳይ፣ ኤልኦሄ ኤልማሰ" ብለህ ጻፍበትና በክብር አስቀምጠው፣ ትከብርበታለህ።

16. **ሉደ - ሌውታ** ፡- ስውርና የማይታይ ድንጋይ ነው፡ ነገር ግን ወፍ በበላዩ ጉጆ ሰርታ እንቁላል ትጥልበታለች፡ በዚህን ጊዜ ወፍዋ ስትበር ይታያል፣ ስታርፍበት ይሰወራል።

ሌውታ የሚባል እንደ ድንጋይ ሙጫ መሰሉ ከዋሻና ከአለት ድንጋይ ላይ ተለጥፎ ታገኘው አለህ፡ የጠራ ኩል ውኃ ይመስላል፣ ተጠንቅቀህ ቀርፋው ከእጅህ ;መሰጠህ አይታይህም፡ ይህን ድንጋይ እንደራስ ወርቅ እንደ አክሊል ከነጭ ወርቅ ጋር አሰርተህ ከአራት ላይ በውስጥ በኩል አጣብቀህ ሰብጠው፡ የተሰወረን በዓይነልቡና ለመመልከት ከራስህ ላይ አድርገህ አስተውለህ ተመልከት፡ የሥጋህ ዓይን ያላየውን እንደ ውኃ ሙላት ነፋስን በሥጋ ያለን ደዌን፡ የማይታየውን ህዋሳት፡ ጥቃቅን ፍጥረታት ሁሉ ትመለከታለህ፡ ብዙ ጊዜ አታድርገው፡ እንዳትሰወር ተጠንቅቀህ አድርግ፡ በዚህ ጥበብ አለ።

17. **ኦሎ - ኦሉደ** ፡- ፈሳሽ ውኃ በአለበት የሚገኝና የደፈረሰን ውኃ የሚያጠራ ድንጋይ ነው፡ እርሱን በገበታ ላይ አድርገህ ውኃ በበላዩ እያደረክ ሲጠራልህ ጠጣው፡ ከውስጥ የአለውን ደዌ ሁሉ ጠርጎ ያስወጣልሃል፡ እርሱ ድንጋይ በአለበት የሚፈልቅ ውኃ ፈዋሽ ፀበል ይባላል፡ መልኩ ሰማያዊ ነጭ መስሉ አሞሌ ጨው ወይም ወርቃወርቁ ድንጋይ ይመስላል፡

ትልቅም ትንሽም አለ፡ ኦሉይ ድንጋይ መሆኑን ለማወቅ በውኃ ውስጥ አሳድረውና ውኃውን ቅመሰው እንዲሁ ሌላ ውሃ ቅመስ፡ የሁለቱ ልዩነት ከሌለው አይደለም፡ ልዩነት ጣም ከአለው እርሱ ነው። በዚህ ብዙ አይነት ፍልስፍና መፍጠር ትችላለህ፡ ለመድኃኒት መቀመሚያ ይሆናል፡ ምግብም እንዳይበላሽ በቶሎው ጠረኑ እንዳይለውጥ ያደርጋል።

የድንጋዮች ጥበብ እንደዚህ የላቀ ነው፡ አንተም ከአስተዋልክና ምስጢራቸውን ከተመራመርክ በልብህም የተሰጣቸውን ጸጋ ከአስተናገድክ፡ የኃይላቸው የክብራቸው ተካፋይ ትሆናለህ፡ እግዚአብሔር እንድንጋራቸው ፈቅዶልናል።

18. **ሎቶ[illegible] - ኗ** - ተንቀሳቃሽ የሆነ በአንድ ላይ ተከማችቶ የሚገኝ የድንጋይ ክምር ነው፡ በትነኸው ብትሄድም እንደገና ተመልሶ ይገናኛል። በአንድ ላይ የሚከመረው ከአሥር እስከ መቶ ቁጥሩ ሊሆን ይችላል፡ ከተሰበሰቡት ከተከማቹበት ላይ ብትቆፍር የተጫረ ወይም ጽሁፍ የአለው የመሰለ ድንጋይ ታገኛለህ፡ ሳትሰብር አምጥተህ በአደባባይ ላይ ቀብረህ የተለያዩ ቀለም ያላቸውን ድንጋዮች ዘበላዩ ላይ ከምረህ ሐውልት አቁምበት፡ ሐውልቱን የአየ ሁሉ በአእምሮው ይቀረጻል። በአካባቢው ለመኖር ይፈልጋል፡ መንደር ወይም ከተማ ለመቆርቆር ሕዝብ ለመሳብ የሚሆን ድንጋይ ነው፡ ሳባ የሚባለው ድንጋይም እንዲሁ ምህሳበ ሰብእ ነው፡ ልዩነታቸው

ሳባ ድንጋዮችን እንደማግኔት አጣብቆ ይዟቸዋል፡ ሉዋው ግን ማጣበቅ ሳይሆን መሳብና መሰብሰብ መከመር ብቻ ነው።

19. **ጓጓ** ፦ መጥፎ ሽታ የአለው ድንጋይ ነው፡ ምግብ በልተው ቢያሸቱት ያስቷውካል፡ ሳይበሉ ቢያሸቱት እራብና ጥም አያሲዝም፡ ይዘውት ቢሄዱ ምግብ አያስፈልግም ድካም አይሰማም፤ ክፉ ነገር አይጠጋም፡ ጠላትም አያስነካም፡ በመጥፎ ጠረኑ ወይም ሽታው ታውቀው አለህ፡ በዚህ የድንጋዮች ጥበብ አለና፡ ተፈላሰፍበት ለሌላም ጉዳይ ይሆናልና አስተውለህ መርምረው።

እግዚአብሔር አስቀድሞ የሰው ልጆች በምድር በአሉ ሁሉ እንዲገዙአቸውና በጥበብም እንዲሰለጥኑባቸው የተፈጥሮ ባህርያቸውንም እንዲጋሩአቸውና እንዲጠቀሙባቸው ወስኖአል፡ ለዚህም ነጻ የሆነ አእምሮ እንዲመረምሩበት ሰጥቶአቸዋል፡ ነገር ግን ከከፉታቸው የተነሣ አእምሮአቸው በጥፋት እንዲደነዝዝ ልባቸው ከመደንደኑ የተነሣ የእግዚአብሔርን ጥበብ እንዲአረክስና እንዲንቅ በፈንታው ድንቁርና ከንቱነት እንዲበዛ የሚያደርገውን ክፉ መንፈስን ወደዱ፡ በመውደዳቸው ለልጅ ልጆቻቸው የከፋ ሞትን አዘጋጁላቸው፡ ከዚህ ለመውጣት እግዚአብሔርን መጠየቅ ነው፡ የጥበብን መንገድ ያሳዩናል፡ ጉዞውም የቀና ቀጥ የአለ ነውና።

20. **ቆ - ቆሚጋ** ፦ መጨረሻ መደምደሚያ ድንጋይ ነው፡

ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ጥበብን የተሞ ውበትህም የተፈጸመ መደምደሚያዩ አንተ ነህ፡ ሕዝ.28፤12 የፍጥረት መደምደሚያ የአዳም ምሳሌ የሆነው ይህ ከቡ ድንጋይ በእግዚአብሔር ገነት ሲኖር አዳም ወደ ምድረ ፋይድ ሲወርድ አብሮ የወረደ ለምስክርነት ይሆን ዘንድ በዚህ ዓለ ላይ የአለ የድንጋዮች ሁሉ የበላይ መደምደሚያ ነው፡፡ እርሱም አራት ማእዘን ያለው ሆኖ ቁመቱ ከከንድ በላይ ይሆናል፡፡ ይህ ድንጋይ ቤተመቅደስ ስትሰራ መደምደሚያ አድርገው፡ እሱ ባለበት ጸሎትህ ይሰምራልና፡፡

21. **ሺቆ** ፦ በውቅያኖስ ውስጥ በአሉ ደሴቶችና በዲብ ውስጥ በአሉ በእሳት ድፍድፍ ወይም ልምድድ በአለበት የሚገኝና እንደሌሎች ድንጋዮች የማይግልና የማይቀልጥ ድንጋይ ነው። ይህ ድንጋይ ከሌሎች ዓለሞች ከዋከብት ከሚያደርጉት ግጭት የተነሣ ተከፍሎ ተበታትኖ ወደዚህ ዓለም ምድር የወረደ ጠንካራ ድንጋይ ነው፡፡ ከበድን ጋር ብታስቀምጠው በድኑ አይፈርስም፡ ሌሎችን እቃዎች እንደዚሁ አያረጁም፡፡

22. **ቶኤዉ: አኤናምን** ፦ የማይሰበርና የማይፈለጥ ጥቁር ድንጋይ ዓይነቱ ብዙም ቢሆን መልኩ የዋልካ ሞክላ ይመስላል፡፡ ሞክላ ማለት በእርሻ ጊዜ ድንጋይ ያክል ሆኖ ሳይፈርስ የሚፈነቀል የመሬት አፈር ነው፡፡ ትንሽም ትልቅም አለው፡ አኤናምን

የተባለውን ድንጋይ ለታመመ ሰው በእሳት ውስጥ አግ፣ በጉጠት አውጥተህ ከውኃ ውስጥ ጨምረው፡ ውኃው. አጠጣው ይፈወሳል፡ ህመሙም ምን እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ለአባጭም እያጋልክ ተኩስበት ያፈነዳለታል፡፡

ተላላፊ በሽታ ወደ ግቢህ እንዳይገባ በግቢህ ደጃፍ/በር/ ስር ቅበረው፡ ወይም በቤትህ በርእፍ ይሁን፡ ለቅጽርህ መሰረት ስትጀምር አብረህ አንጸው፡ በቤትህ በግቢህ የሚኖሩ ሁሉ ሙሉ ጤነኛ ይሆናሉ፡፡

23. **ቶጆ**፡- ሰፊ ጠፍጣፋ ድንጋይ ነው፡ እንደ እንጀራ ተደራርቦ ታገኘው አለህ፡ እርሱን ወቅጠህ በውኃ ከዱን ጋር ለውሰህ በመሰለህ ቅርፅ ጠፍጥፈው በበላዩ ዘይት አፍስበት እንዲሁ ሌላ ጠፍጥፍና አቃጥለው፡ ሳንቃ መስሎ ታገኘውአለህ፡፡

24. **ኣቂ** ፡- የከበረ እንቁ ድንጋይ መልኩ እንደውኃ የጠራ ሆኖ የኩል ድንጋይ ይመስላል፡ በበሐር ውስጥ በምድር ልብ ውስጥ ታገኘው አለህ፡ ለሴቶችና ልጆች ይሆናል፡ ከጣጉል ቅርፍት መካከልም ታገኘው አለህ፡፡

25. **ሽ[illegible]ደ** ፡- ምንጊዜም መልኩ የማይቀየርና የማይፈረከስ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ መልኩ ነጸብራቅ የለሰው ሆኖ እንደኩል የጠራ ነው፡ መስታዋትም ይመስላል፡ በፀሐይ እንዲያንጸባርቅ አድርገህ በእለቱ አንጻር አስቀምጠው ነፀብራቁ የዋሻውን እለት ያቀልጠዋል፡፡

26. **ቆ[redacted]** ፦ መደምደም ውቅሮ መደምደሚያ ድንጋይ ነው፡ መልኩ ጥቁር ሆኖ ያልዘለቀ ቀዳዳ የአለበትና ከባድ ድንጋይ ነው፡ ይህን ድንጋይ የድንጋይ ቤት ሰርተህ ስትጨርስ መዝጊያና መደምደሚያ አድርገው፡ ከበታች የአሉትን ሁሉ እንዳይናዱ ይጠብቃቸዋል፡ ከጊዜ ብዛት ይጣበቃሉ፡፡

27. **ሽ[redacted]** ፦ ማረፊያ ፡ ይህ ድንጋይ ቋጥኝ ያክል ሆኖ ከአፋፍ ከገደል ጫፍ ተን ተንጠልጥሎ ታገኘው አለህ፡ ሰው በብልሃት የአስቀመጠው ይመስላል፡ በአደባባይ በበር አስቀምጠው በሃገሩ ችግር አይመጣም፡ ጦርነትም አይነሣም፡፡

28. **ሽ[redacted]** ፦ በውኃ ተንሳፋፊ ይሆንና ቆይቶ ይሰጥማል፡ ቀላል ወይም ከባድ አይደለም፡ ብዙ ግዜ ወፎች ሲቆረቁሩት በአፋቸው ሲነፉት ታያለህ፡ እንስሳዎችም ይልሱታል፡ ይህን ድንጋይ መካን የሆነ ሰው ታቅፎት ቢያድር መካንነቱ ይቀራል፡፡

29. **[redacted]ገር** ፦ የድንጋይ ክምር ኮረብታ የሆነ ነው፡ በቀድሞ ዘመን ወደጦር ሲሄዱ የንጉሥ ሠራዊት አንዳንድ ድንጋይ ይጥላሉ፡ ሲመለሱ ለብቻው እንዲሁ ያደርጋሉ፡ የሞተውን ቁጥር በዚህ ያውቁታልና፡ ስሙ ውግር ክምር ድንጋይ ይባላል፡፡

30. **ኤ[redacted]**፡- መፍለቅለቂ፡ ስትቀርበው የሚጠፋ ስትርቀው የሚፈልቅ ድንጋይ ነው፡ ቡልጭት ወይም ወርቃወርቂ ድንጋይ ባለበት ታገኘው አለህ፡ ቤትን ስታንጽ ስትሠራ ኤው የተባለውን ድንጋይ አቀላቅለህ ሥራ ቤትህ ያማረና ጠንካራ ይሆንልሃል፡ ለቤተመቅደስም እንዲሁ አድርግ፡፡

31. **ሽ[redacted]ሴ** ፡- ወይም ሽሞሴ የተባለ ነጭ ድንጋይ የጨው ባህር ወይም የጨው አረንቋ ባለበት የሚገኝ የጨው አሞሌ መስሎ ታገኘው አለህ፡ የጨው ድንጋይ መስሎ ባለመሰበሩ ታውቀው አለህ፡ እርሱን አምጥተህ በሚመር ምንጭ ውኃ ላይ ብትቀብረው ውኃው ይጣፍጣል፡ መራራነቱን ያጠፋዋል፡ ከምትበላው ከምትጠጣው እቃ ውስጥ ክተተው፡ የተመረዘ ቢሆን ያጠራዋል፡ ይህ ድንጋይ ባለበት መርዝ የሆኑ ነገሮች ይሻራሉ፡ እባብ እንኳ ድንጋዩ ባለበት አይቀርብም፡ እንዲሁም መርዝ ያላቸው ሁሉ አይቀርቡም፡ በዚህ ሌላ ጥበብ አለ፡፡

32. **ሽ[redacted]** ፡- መያዝ አውቃር በድንጋይ የተሠራ ቤት፡

**ሽ[redacted]** ፡ የሚያያዝ የሚጣበቅ አንድ የሚሆን ነው፡

ከእሳተ ገሞራ ውስጥ የተረጨና እንደ እብቅ ሆኖ የተከመረ ወይም የሚከመር ቆይቶ ወደ አለት የሚቀየር ነው፡፡ ይህ የእሳተ ገሞራ እብቅ የሆነ አሸዋ እንደ አለት ከመሆኑ በፊት እንደቤት ቢሰሩት እነደሐውልት ቢያደርጉት

ከትንሽ ጊዜ በኋላ የድንጋይ ቤት ይሆናል። እንስሳም ይሁን ሰው የቀመበት የእሳተ ገሞራው እብቅ ኮቴው እንደ አሻራ ሆኖ ይቀራል፡ ለዚህ ነው እሳተ ገሞራ በተነሣበት አካባቢ የነበሩ አራዊቶችና እንስሳቶች ኮቴያቸው በአንዳንድ አለት ላይ ተቀርጾ ይታያል። ሶማንኛውም በመሰለህ ዓይነት በትኩሱ አቡዋራ ወይም እብቅ የሆነውን ሰብስበህ የድንጋይ ቤት እንዲሆን ብታደርገው ይሆንልሃል። መፈላሰፉና ለታሪክ መታሰቢያ አድርጉ ማለፉ የአንተ ነው፡ እስከ አሁን ድረስ "ፈረስ እረግጥ" እየተባለ የሚነገርበት አለት በዲማ ጊ/በታላይ መ/ዓ/ በሌሎችም አገሮች ይገኛል።

33\. [redacted] :- የውኃ እናት ልምድድና የሚስለከለክ ድንጋይ መልኩ ክብረሰማይ መስሉ እንደመስታዋት የጠራና ኩል የሆነ ነው፡ ከእሳት ውስጥ ቢገባ አይቀልጥ፡ አይግምም እሳቱን ያጠፋዋል፡ ለእሳት ፀር ነው።

34\. [redacted]ቪ :- ፍላጐትን የሚፈጽም ድንጋይ መከስትም ነው፡ መልኩ ወይባ የተነከረ ልብስ ወይም እሳት አብሪ ይመስላል፡ ትንሽም ትልቅም አለው፡ እንደመስቀል አስቀርፀህ በአንገትህ ብትይዘው የምትፈልገውን ሁሉ ታገኘለህ፡ ለአንተ የሚሰወር የለም፡ ሁሉ ይከሰትልሃል፡ ዘንዶ በሚኖርበት ቦታ ታገኘው አለህ።

35. **[illegible]ራ[illegible]ሬ** ፡- ብዙ ዓይነት ቀለም የአለው የእንቁ ድንጋይ ነው፡ ይህ ድንጋይ ከጥላ ውስጥ ሲያደርጉት የሚጠቁር ከብርሃን ላይ ሲያደርጉት የሚፈልቅ እንደ እስስትም በየጊዜው መልኩን የሚቀይርና የተለያዩ ዓይነቶች ቀለሞች የሚታዩበት ነው፡ በቤትህ ውስጥ ብታኖረው የሚጉብኝህ ይበዛል፡ አብሮህ የሚኖር ግን የለም፡ በቤተ መዘክር ውስጥ ቢቀመጥ መልካም ነው፡ የሚጉብኘው ይበዛል፡፡

36. **ኣ[illegible]** ፡- አንፀባራቂ ድንጋይ ነው፡ እንቁ ይመስላል፡ ነገር ግን አይደለም፡ እንደ ክርስቶ ያለ ነው፡ ስትሰብረው ይሰበራል፡ በእሳት አቅልጠህ እንደጠርሙስ ብትሰራ ይሰራል፡ ከዚህ ድንጋይ የተሰራ እቃ ወይም መስዋት የጠራ ይሆናል፡ ከዋሻ ውስጥ ይገኛል፡፡

37. **[illegible]** ፡- ድምጹ ሲወቅሩት እስከ ሩቅ አገር የሚሰማ ነው፡ ከሁለት ከፍለህ ከተራራቀ አገር ለያይተህ ብታስቀምጠውና የተከፈለውን አንዱን ሲመቱት ከሁለተኛው ተጠግተህ ብታዳምጥ ስንት ግዜ እንደመቱት ድምፁን ትሰማለህ፡ በዚህ የድንጋዮች ጥበብ እንዳለ ታውቃለህ፡ የመሰለህን ነገር ተፈላሰፍበት፡፡

በዋውየ ድንጋይ የተሠራ ከበሮም ይሁን የሙዚቃ መሳሪያ ድምጹ ልብን ይስባል፡ ለዛ ያለው ስሜትን የሚቀሰቅስ ትዝታን

በልብ ላይ ቀርጾ የሚተው ድምጽ አለው፡ ድምጹን አስተውለው ሲሰሙት ቅርብ እያለ ከሩቅ የሚሰማ ከሩቅ ያለው ቅርብ ቦታ ያለ ይመስላል፡ አፊ ያሬድ የተባለች ወፍ ለድምጹዋ ማማር እንዲያግዛት ትወቅረውና ሽርፋ ትውጠው አለች፡ አንተም እንዲሁ ብታደርግ ድምጽህ ከቀን ወደቀን ያምራል።

38. **ዋፆ** - የሚንቀሣቀስ ድንጋይ በምድረ በዳ ተሰብስቦና ተከማችቶ ታገኘው አለህ፡ በትነኸው ብትሄድ በሌላ ቀን ብትመለስ እንደገና ተሰብስቦ ተከማችቶ ታገኘው አለህ፡ ከተከማቹት መሃል የተድበለበለና ከባድ የሆነ ድንጋይ ታገኛለህ፡ እሱን አምጥተህ ከገበያ መሃል ቀብረህ በበላዩ ሐውልት ብትሰራ የሕዝብ መናሓሪያና መገናኛ ትልቅ ገበያ ይሆናል።

39. **ቆጩሎ** ፡- አውሉ ነፋስ የሚነሣበት ዋሻ ውስጥ የሚገኝ ጥቁር ድንጋይ አለ፡ ከድንጋዩ ውስጥ የእሳት ፍህም የመሰለ አለ፡ እርሱን ከወርቅና ከብር ጋር ብታስቀምጠው እንደውኃ ያቀልጣቸዋል፡ እርሱ ባለበት ዋሻ ውስጥ ልምድድ የሆነና ውኃ የመሰለ መ/ታገኛለህ።

40. **ዮራኔ - ዮራ** ፡- ኃይል ያለውና ፍንዳታ የሚፈጥር ቢጫ ድንጋይ ነው። ከኃይለኛ ቢጫ እንቁ ጨረር ጋር አገናይተህ ወደዋሻ ብታፈልቀው ዋሻውን ገደሉን ይንደዋል፡ ያቀልጠዋል፡ እንዳልነበረ ያደርገዋል። እርሱ ባለበት አረንጓዴ፡ ቢጫ አፈር

አለ፡ ከእርሱ ጋር የብረት ድንጋይ ብታደርግ ያጠራዋል ወይም ያቀልጠዋል።

41. **ዮጵያ - ፄጺ** ፡- ቢጫ ወርቅ፡ ለገጸበረከት የሚቀርብ የወርቅ ድንጋይ ነው፡ እርሱ ባለበት ክብር ይበዛል፡ ሁሉም ይመኙዋልና፡ እንዳይወስዱብህ ጠብቀው፡ በዮጵያ ወርቅ እየተጣበቀ የሚሠራ እንቁ ያማረና ውበት ያለው ይሆናል።

42. **ያክንት** ፡- መልኩ ቀይ ደም የመሰለ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ በነጭ ወርቅ ለብጠህ ብትይዘው የአየህ ሁሉ ይወድኃል፡ ከምትሰራው ከቅርፅ ሥራ ጋር እየቀያየጥክ ብትሠራው የአማረ ይሆንልሃል። በጽላት ገበታ ላይ በራስ ወርቅ ላይ ለፈርጥ ጌጥ እያደረክ፡ ስራው ለፈለከው ጌጥ ሁሉ የሚሆን እንቁ ነው፡ ከድንጋይ ውስጥ ይገኛል።

43. **ያስታደኒ** ፡- መልኩ ነጫጭ ጥቁር ሆኖ ቀጥ ያለ መስመሮች የአሉትና የተሳለ ወይም የተሞረደ ብረት የመሰለ ነው፡ ለሰይፍ ለጐራዴ ለተወርዋሪ ቀስትና ጦር አቅልጠህ ብትሰራው ተመሳሳይ የለውም፡ ለእጅህ የቀለለ ሆኖ በቀላሉ የሚወረወር የብረት ድንጋይ ነው፡ በገደል በተራራ ስር እንደቆመ ሳንቃና ግንድ መስሎ ታገኘው አለህ፡ በዚህ የድንጋዮች ጥበብ የላቀ ነው።

44. **ሎያ** ፡- የሻከረ ድምፅ ያለው ድንጋይ ነው፡ መልኩ አረንጓዴና ቡላ ሆኖ ጠፍጣፋ ነው፡ ድፍን ሆኖ ስንጥቅ የመሰለ አለው በሃገርህ ቸነፈር ቢሆን ጦርነት ቢሆን አንበጣ ቢመጣ እስከ ሰባት ቀን ሌሊት ተነስተህ ጥፋትን ወደጠላቴ መልሰው እንዳጉም አብነው እንደአቡዋራ አብነው እያልክ በደረቅ እንጨት እየመታህ ስቀለው በሰባተኛው ቀን የመታህበትን አቃጥለህ ለነፋስ ስጠው፡ የአልከው ሁሉ ይፈጸማል፡፡

እንዲሁ በመንፈቀ ሌሊት ከተራራ ላይ ወጥተህ "ሰማያትንና ምድርን የፈጠርክ ቸርነትህ የበዛ ምህረትህን የምታሳይ እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፡ ይህን የመጣውን መቅሰፍት አንሳልን፡ በፈንታውም እድሜን አርዝመህ ጤንነትን ስጠን፡ ጠብንም አርቀህ ፍቅርንና ሰላምን ስጠን፡ የጸጋህን በረከት አሁን ስጠን፡ ምድርህን ባርክ ሕዝብህንም አድን" እያልክ በወይራ ዘንግ ሰባት ጊዜ ምታው፡፡

45. **ኢዮቤል**፡- አቤል የተገደለበት ድንጋይ ነው፡፡ መልኩ ድቡልቡል ሆኖ ቡና ወይም የወይን ጠጅ ይመስላል፡ እልፎ እልፎ ደም የተንጠበጠበበት ይመስላል፡ ይህን ድንጋይ ወስደህ ፍርድ በሚፈረድበት አደባባይ ቅበረውና በግድያ የተጠረጠረውን ሰው በተቀበረበት አቁመህ ብትጠይቀው ገድሎ ከሆነ እውነቱን ይናገራል፡ ካልገደለ አልገደልኩም ይላል፡ ይህ ድንጋይ በአለበት ሁሉ ወንጀለኛ የሆነ ሁሉ ይናገራል፡፡

46. ስፀ ፦ መስታዋት መስሎ ጠንካራ ያልሆነ ወርቃ ወርቁ ድንጋይ ነው፣ በእሳት አቅልጠህ ስመጠጫ ዋንጫ አድርገህ ብትሰራው ይሆንልሃል፣ ወርቅማ የሆነ አፈር ወይም አረንጓዴ የሆነ መሬት አለ፣ ከእርሱ ጋር ቀላቅለህ ብታቦካውና እንደሸክላ ብትሰራው ተወዳጅ እቃ ይሆንልሃል።

47. ሏዮ ፦ እንደሙጫ መስሎ አጣብቆ የሚይዝ ድንጋይ ነው፣ በጼቃ ከተባለ ከኖራ ድንጋይ ጋር ወቅጠህ እያቦካህ ህንጻ ስታንፅ አብረህ ስራው እንድ ያደርግልሃል፣ ለሐውልትም እንዲሁ አድርግ፣ ከጊዜ ብዛት የድንጋይ ኃውልት ይሆንልሃል።

48. ናና ፦ ሰው የመሰለ ድንጋይ ወይም የሰው ራስ የመሰለ ድንጋይ ነው፣ ይህ ድንጋይ ከአዳም ነገድ በፊት የነበሩና የዝንጀሮ መልክ የነበራቸው የማያን ራስ ቅል ነው፣ ለምቀኛ በደጃፍህ ቅበረው መልካም ነው።

49. ናኒ ፦ የእሳት ፍንጣሪ የመሰለ ድንጋይ ነው፣ መልኩ ቢጫም ቀይም መስሎ እንደቅልምሽ የመሰለ ነው፣ በማጣበቂያ አምስቶቹን እንደመስቀል አድርገህ እሰረው ይጠብቅሃል።

50. ናዘደ ፣ እረፍት የሚሰጥ ድንጋይ ነው፣ መልኩ ጥቁር ሆኖ ከድንጋዮች መሐል ዘይት የፈሰሰበት ይመስላል፣ እሱ መሆኑን ለማወቅ ለታመመ ሰውና እንስሳ አንተርሰው ይድናል፣ ወይም ይሞታል።

51. **ላናብሊስ** - ናብሊስ ደወል የሚሆን ድንጋይ እንደመስታዋት ሰተት ያለ ነው፡ መልኩ ነጭ በረዶ ይመስላል፡ ጸር ለበዛበት በጆሮው አጠገብ የመቱበት እንደሆነ ወዲያውኑ ይሞቃል፡ ምጥ ለያዛት ሴት እንዲሁ ምታው፡ በሰላም ትወልዳለች፡ ምጥ የያዛት ወፍ በአፍዋ ትቆረቁረው አለች፡ ወዲያውኑ እንቁላልዋን ትጥላለች፡ በቤተ መቅደስ ደጃፍ ስቀለውና ለፈለከው ጉዳይ ምታው፡፡

52. **ሎዮን** ፡- ለምርዋዕ የሚሆን ቀላል ድንጋይ፡ የድኩላ ቁረን ወይም ቅልጦሽ ይመስላል፡ እርሱን በወገብህ እሰረው ፈጣን ሩዋጭ ትሆናለህ፡ ይህ ድንጋይ ባለበት ሙጫ መስሎ የተከመረ አፈር ይገኛል፡፡

53. **ሶኔ** ፡- ስሜት እንዲኖር የሚያደርግ ድንጋይ ነው፡ መልኩ ነጭ ሆኖ ድቡልቡል የሰው ራስ ቅል ይመስላል፡ በድን በማይፈርስበት በነጫጭ ቦረቅ ውስጥ ይገኛልና አምጥተህ ለሚረሳ ስሜት ለሌለው ሰው በውኃ ውስጥ አሳድረህ ውኃውን አጠጣው፡፡

54. **ናፑሬን** ፡- ውኃን የሚያፈላ ድንጋይ ነው፡ እንዲሁም ለአረንጓዴ፡ ለነጭ፡ ለቀይ፡ ለጥቁር፡ ለቢጫ ለፈለከው ዓይነት ቀለም ለማድረግ ከቀይ ከጥቁር አፈር ጋር ውቀጠውና አቡካው ጥሩ ቅጥራን የቀለም ዓይነቶች ይሆንልሃል፡፡

55. **ናጌ፡ ሸሳስነ ናጌ** ፡ የሚባል ክርችፍችፍ የሆነ ድንጋይ አለ፡ ሰማእሰረ ሰብ በወገብህ ያዘው፡ በእርሱ የዘሆን ጥርስ ለጌጥ ስታበጅ በእርሱ ተጠቀም፡ እንዳልከው ይሆናል፡ በፈረፈር፡ በጭንጫ ቦታ ታገኘው አለህ፡ መልኩ ክርችችፍ ሆኖ የመንጋጋ ጥርስ ይመስላል፡ ለአንጥረኛ ሰው ጥሩ ነው።

56. **ኦር** ፡ የሚያበራ ድንጋይ ነው፡ መልኩ አረንጓዴ ቢጫ ነው፡ ከእለት መሃል ወይም ከዋሻ ውስጥ ታገኘው አለህ፡ ቀን ከፀሐይ ላይ አውለውና ማታ ስታየው ፍህም መስሎ ታየውአለህ፡ ከአንተ አታርቀው።

57. **ኖሀያ** ፡ እንደኩበት የቀለለ እንደሩይሬ ድንጋይ ጠንካራ ያልሆነ ስትወቅጠው ይደቃል፡ በበሐር ላይ ብትጥለው አይሰጥምም፡ ከቅጥራን ጋር አቡክተህ መርከብህን ለቅልቀው፡ አይሰጥምም፡ ሣጥንህንም ብትመርገው ብል አይበላውም፡ አይነቅዝም፡ በአዋሽ ሸለቆ እስከተርሴስ ባህር ድረስ ባለው ታገኘው አለህ፡ ይህ ድንጋዩ ባለበት ኡየን የተባለውም ይገኛል።

58. **ናኔ** ፡- ራእይ የሚያሳይ ድንጋይ ነው፡ የሰው ቅርጽ ታይበታለህ፡ ወይም መከዳ መስሎ ዘይት የፈሰሰበት ይመስላል፡ በእሉ ላይ ተቀምጠህ ወይም ቆመህ ወደ እግዚአብሔር ጸልይና ተንተርሰህ ተኛ፡ የአሰብከውን ያሳይሀል፡

ራቅ አድርገህ በክብር አስቀምጠው ወይም በቤተመቅደስ ውስጥ አትረው።

59. **ኒያስ** ፦ ከሩቅ ያሰን ድምፅ የሚስብ ድንጋይ ነው፣ ይህ ድንጋይ የአለበት ዋሻ ድምጽን ደጋግሞ ያሰማል /የገደል ማሚቶን/ ከዋሻው አለት እንደበት ተሰጥሮ ታገኘውአለህ ለደንቆሮ ሰው ሰብረህ አስርለት።

60. **ኒል** ፦ ሰማያዊ የወይን ጠጅ የመሰለ የእንቁ ድንጋይ ነው፣ ይህን አስደንጋጭና ቀልብ የሚስብ እንቁ ያለቢጫ ወርቅ አትሰረው ይጠፋል።

61. **ኔን** ፦ እጥንት የመሰለ ነጭ ድንጋይ ነው፣ ወቅጠህ በውኃ ለውሰህ አስንብተህ እንደገና አቡካውና እንደሸክላ በፈለከው መልክ ስራና በእሳት ተኩሰው፣ የአማረ እቃ ይሆንልሃል።

62. **ዕንቁዮቁ** ፡ የዕንቁዎች ማጣበቂያ ቢጫ ወርቅ ዮቋ ይባላል፣ ኢትዮጵ የተባለ የመልከጼዴቅ ልጅ ግዮን የሚፈስበትን ምድር በስሙ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ ብሎ በበስሙ ለመታሰቢያ የሰየመና በዮቋ ወርቅ የከበረ ንጉሥ ነው።

ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ማለት ምስጢሩ የኢትዮጵያ ጠበብቶች ወርቅና እጣን ከርቤ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ በእጆቻቸው ስለማቅረባቸው ነው፣ ይህም ትንቢት ተፈጽሞ አሁንም ኢትዮጵያውያን ለእግዚአብሔር

የሚያቀርቡትን ስእለትና ስጦታን ይመስክታል፣ ለእግዚአብሔር ስጦታን ሲማቅረብ እጆቻቸው ታጥፈው አያውቁምና።

63. **ፈ** ፡ ልብ የመሰለ የወርቅ ድንጋይ ነው፣ ይህ ድንጋይ የልብ ቅርጽ የመሰለ ድቡልቡል የሆነ ነው፣ ከውስጥ እንዲሁ የተድበሰበሰ የልብ ቅርፅ የያዘ ወርቅ ይገኝበታል፣ ሳታኖፐር በእሳት ሳትፈትን በክብር አስቀምጠው፣ የአስከብርሃል፣ ይህን የልብ ቅርፅ የመሰለ ወርቅ ይዘህ ቤተመንግሥት ብትገባ ዝቢያ ብትውል የልብህ ምኞት ሁሉ ይፈጸማል፣ የአልከው ሁሉ ይሆናል፣ የአየህ ሁሉ ይወድሃል።

64. **ዓፈር** ፡ የአፋር እንቁ ድንጋይ የከበረና ተወዳጅነት የአለው ነው፣ አፈር ወይም ኦፈር የተባለው የአፍሪካውያን ጥቁር ወርቅ ወይም ንጹህ የብር ድንጋይ ይገኝበታል፣ መልኩ በጣም የጠራ ሆኖ ሰማያዊ ነጭና አረንጓዴ ዓይነት ነጭ ነው፣ ነጸብራቁ እንደኮከብ ሆኖ አምስት ቀስት ያለው ኮከብ ይመስላል፣ ለፈርጥ ጌጥ ቢያደርጉት መልካም ነው፣ ልብን የሚያረካና የሚያስደስት እንቁ ነው፣ የሰው ገላ ከአፋር አፈር ሰው ሆኖአልና።

65. **እፈ** ፡- የተያያዙ ሦስት ድብልብል ድንጋዮች አንዱን ከቤት ሁለተኛውን ልጅህ ወይም ሚስትህ ሦስተኛውን አንተ ስፍታችሁ ብትይዙ በአንደኛው የደረሰው ደስታም ይሆን መከራ ለሁለተኛው ሰው ይሰማዋል ያውቀዋል፣ በዚህ የድንጋይ ጥበብ

አለና ተፈላሰፍ፡ እንደመንቶች አንድ አይነት አስተሳሰብ አንድ አይነት ጠባይ እንዲሆኑ የሚያደርግ ከእግዚአብሔር ስጦታ ተሰጥቶአቸዋልና አስተውለህ አጥናቸው።

66. **ፋርያ** ፡- እሳተ ገሞራን የሚያስነሣ ልምድድ የሆነ የእሳት ድንጋይ ነው፡ በምድር ልብ ውስጥ ለውስጥ የሚሳብ ነው፡ እሳተ ገሞራ እንዳይነሣ ለማድረግ ሉዋኦ የተባለውን ድንጋይ ስታገኝ ወስደህ ብታስቀምጠው እንዳይፈነዳ ያደርገዋል።

67. **ሰፋር** ፡- ወይም ስመ አፋር የተባለ ነጭ ቦረቅ ድንጋይ በአፋር ምድር የሚገኝ እሱ በአሰበት የእሳት ዲን እሰ፡ መርዛማ ነው፡ እሱ በአሰበት የመነጨን ውኃ አትጠጣ፡ እንዲሁ ለባሩድ የሚሆን አፈር አብሮ ይገኛል፡ ለሌላ ለመጠበብ ለመፈላሰፍ ካልሆነ አትጠቀምበት።

68. **ሶፈር** ፡- የአፋር ጥሩ ወርቅ ድንጋይ ነው፡ በአፋር አፍሪላ ካውያን ወይም በአፋር አፍሪካ፣ አፍሪቃ፣ አፍሪካና፣ አፍሪክ፣ ተብሏል፡ ጥቁር ድንጋይ አፈር በበዛበት ይገኛል።

አፌር ከቡር የኦፌር አፋር ወርቅ ሲሆን መልኩ በጣም ጥቁር ሆኖ የጠራ ነው፡ ፌር የተባለው ነጭ ወርቅና ብር መዳብ ለብር የሚሆነውም አለት ድንጋይ ይገኝበታል። ለአልማዝ መደገፊያ ለፈርጥ ማጣበቂያ የሚሆን ወርቅ ነው።

69. **ኣፌዝ** ፡- ንጹህ ወርቅ ከድንጋይ ውስጥ የሚገኝ ነው፡ መልኩ አረንጓዴና ቀይ ነው፡ የድንጋዩ መልክ ምከላ አፈር መስሎ ጥቁርም አፈርማም ነው፡ ከወርቁ ጋር ያክንት የሚባለው እንቁ ይገኝበታል፡ ለወርቁ ፈርጥ ይሆናልና አብረህ አሰርተህ ብትይዘው መፍትሔ ሐብት ወሥራይ ይሆንልሃል፡ በዘመንህ ጤነኛ ሁነህ ትኖራለህ፡ በክብደቱ ከሌላው ወርቅ ትለየው አለህ፡ አፌዝ ወርቅ የተገኘበትን ድንጋይ በበርአፍህ ቅበረው፡ ለበረከት ይሆንልሃል።

70. **ቆፍ** ፡- ብዙ አመታት የሚያኖር የእድሜ ድንጋይ ነው፡
በዋሻ ውስጥ ገብታ ወይም እንደሰፌድ መስሎ ታገኘው አለህ፡ በበላዩ ላይ በልሳነሰብእ ሱባ ቃል የተጻፈ ፊደል አለው፡ በየጊዜው በውኃ አጥበህ ጠጣ፡ ወይም ከምትጠጣው ውኃ ወስጥ ከተተው ወይም በጋን ውስጥ ከተህ በበላዩ ውኃ ሞልተህ አዘውትረህ ከሱ ጠጣ፡ በየጊዜ ትታደሳለህ፡ እድሜ ትጠግባለህ።

71. **ረበገዮቅ** ፡- ቀዳዳ የበዛው ድንጋይ ነው፡ ይህ ድንጋይ ሲያዩት የምስጥ ቤት ወይም ምስጥ የሠራው ይመስላል፡ በደጃፍህ በመስኮት በኩል አንጠልጥለው፡ የጠላኸው ሰው ከአንተ ይርቃል፡ አይቶ ይፈራሃል፡ ከተላላፊም በሽታ ይጠብቅሃል።

72. **ፈርድ** ፡- ለፈርጥ የሚሆን ድቡልቡል ከዛጐል ውስጥ የሚገኝ እንዲሁ አንተም ፈርድ የተባለውን የአልማዝ ድንጋይ እየሰበርክ በባህር ውስጥ በአለ በዛጐል ቅርፍት ውስጥ አስገብተህ ከበሐሩ ጣለው፡ በሌላው አመት ፈርቅተህ አውጣው ተድበልብሉ ታገኘው አለህ /PEARL/

73. **ሱፋይ** ፡- የጋለ ድንጋይ እሳትን የሚፈጥር ነው፡ መልኩ ቡላ ነው፡ በግለቱ ታውቀውአለህ፡ በእጠገቡ ልብስ አታኑር፡ ያቃጥለዋል፡ ነገር ግን ከቡኽቃ ከጋን ስር ብታስቀምጠው ያፈላዋል።

74. **ፋፋሽ** ፡- የነዳጅ ጭቃ በአሰበት የሚገኝ ድንጋይ ነው፡ የሞከላ አፈር መስሉ ጠንካራ ነው፡ በብረት ማንጠሪያ አንጥረህ ለተሽከርካሪ ብረት ብታደርገው ለሰረገላ እግር እንዲሽከረከር ብታደርገው የተሻለ ከቀን ወደቀን እየሳለ የሚሽከረከር ይሆንልሃል፡ በዚህ ተፈላሰፍ፡ ብዙ ዘዴ ታገኝበታለህ።

75. **ፎር - ፍርም** ፡- ክብረሰማይ የሚባል ሰማያዊ ድንጋይ፡ ይህ ድንጋይ ከቀይ አፈር ጋር ቀላቅለህ ከብረት ጋር ብታስቀምጠው ቀይ መዳብ ያስመስለዋል፡ ብረቱን ሁሉ ከጋን ውስጥ ከተህ እሱን አቡክተህ ብትሰነብትና ጢሱ እንዳይወጣ አድርገህ በእሳት ብትቀቅለው ወርቅ ያስመስለዋል፡ ወርቅ የመሰለ አፈር አለ፡ እርሱም እንደዚሁ ብታደርግ ወርቅ ይመስላል እንጂ ወርቅ አያደርገውም፡ የሉሚ ውኃ በበላዩ ጨምርበት።

76. **ፋፎ** ፦ የሚያረካ የሚያስደስት ድንጋ! ነው፣ የዘይት ቀለም የተቀባ ይመስላል፡ መልኩ ቀያቴ ጥቁር ነው፡ ሲጠርቡት ይጠረባል፡ በመሰለህ ቅርጽ በእንስሳ ወይም በአውሬ መልክ አስቀርጸህ በመንበርህ ላይ አስቀምጠው፡ ለቤትህ መልካም ነው፡ ከተለያዩ ጌጦች ቅርጾች ጋር አስቀምጠው የተመልካችን ዓይን ይስባል፡ የአየው ሁሉ ይወደዋል፡ ምሕሳበ አእምሮ ወምሕሳበ ለብእ ነው።

77. **ፍንዱቅ** ፦ የሚባል የፍትወት ድንጋይ የሴት ብልት የመሰለ አለ፡ እርሱን ብትይዝ ዝሙተኛ ትሆናለህ፡ አፍረተ ሥጋው ለሞተበት ቢያሽበት ይነሣለታል፡ በውኃ በጥብጦ ቢጠጣው ፍትወት ያበዛለታል፡ ይህ ድንጋይ ባለበት ሁሉ ዝሙት ይበዛል፡ ይህ ድንጋይ በአለበት ሰዶማውይነት ይበዛልና ምድር በሰዶማዊነት ግብረ እንዳትረከስና ወደርኩሰት ጉዳና እንዳትመራ ሕዝብ በሚኖርበት አገር አታኑረው፡ በዚህ እርኩሰት ብዙ አገሮች ጠፍተዋልና፡ እንደፍንዱቅ ያለ ባባን የሚባል ትልቅ ድንጋይ አለ በመልክ ይለያያሉ።

78. **[illegible]** ፦ የሚያስደስት ይባቤ ድንጋይ መልኩ የሰው ገላ ይመስላል፡ ሲነኩት ያዝ ያደርጋል፡ ለስላሣና ጠፍጣፋ ነው፡ በመሰለህ ቅርፅ ቀርፀህ በመንበርህ ፊት ለፊት አስቀምጠው፡ ሁልጊዜ ደስ ይልሃል፡ አይከፋህም፡ ቤተሰብህ በሰላም በፍቅር ይኖራል፡ ለገበያም ይሆናል፡ መክስተ ሐብት ነው።

79. [redacted] ፡- ቀልብ የሚስብና የሚያምር የእንቁ ድንጋይ መልኩ የወይን ጠጅ ወይም ዋርዳ ወፍ ይምስላል፣ በድንጋይ ውስጥ ታገኘው ዘንድ እለህ ከባድ ነው፣ ከእሳት ውስጥ ብትከተው እምር ይወጣል እንጂ አይቃልም፣ እሳት የማይደፍረው ጠንካራ እንቁ ነው፣ በጥበብህ በንጭ ወይም በቢጫ ወርቅ መሃል አድርገህ ያዘው የአየህ ሁሉ ያከብርሃል፣ በአእምሮው ትቀረጻለህ፣ ለሰው እታውሰው አእምሮህ ይሰለባል፣ ህሊናህ ይደክማል፣ ትጃጃለህ፣ በዚህ የእንቁ ምስጢር አለ።

80. [redacted]፡- ስር ያለው ድንጋይ ከምድር ውስጥ እንደተቀበረ ወይም እንደወደቀ ብዙ ስሮች እንዳበቀለና እንዳጕጠጕጠ የከብት ቀንድ ይመስላል፣ እርሱ ባለበት ዘጭ መረጭ ይብቅላልና በስሩ እያሞቅህ እበጡን ተኩሰው፣ ደቁሰህም ከከፋ ቁስል ላይ ደምድመህ እሰረው ይፈወሳል። በጆማት ስር ላይ ለወጣ ኪንታሮትና ለሌሎችም ቁስሎች ሁሉ መድኃኒት የሚሆን የድንጋይ ስር ነው፣ እስተውለህ ተመራመርበት ለብዙ ነገር ይሆንልሃል።

81. [redacted] ፡- ቀዝቃዛ ድንጋይ ነው፣ ከእሳት ውስጥ ብትከተው ያጠፋዋል እንጂ አይሞቅም፣ በቤትህ ባጥ በመደምደሚያው ላይ ብታስቀምጠው ቤትህን እሳት አይበላውም፣ እሳተ ከላ የሚባል ድንጋይ ይህ ነው፣ ቀዝቃዛ በመሆኑ ብቻ ታውቀው ለለህ።

82. **ሌቡ** ፡- እንደከበሮ እንደነጋሪት ሲመቱት የሚሙህ አራት ማእዘን የአለው ድንጋይ ነው፡ አቅልጠህ ለሙዚቃ መሳሪያ ብታደርገው የአማረና የተወደደ ይሆንልሃል።

83. **ሌቫሌወ** ፡- የድንጋዮች አባት እርሱም እብነ ሕይወት ይባላል፡ መልኩ ሰም የተቀባ ይመስላል በገደል በዋሻ እንደላንታ መሰሉ ተገኘው አለህ፡ እርሱ በሚኖርበት በለስ ይበቅላል፡ ቤተመንግሥትን ቤተ መቅደስን፡ ቤትን ስትሰራ በመግቢያው በኩል ቅበረው፡ እርሱን የተረገጠ ሁሉ አይዋሽም፡ አይከድም፡ ለፍቅር ለሰላም መልካም ነው፡ ከውኃ ብትከተው ያሞቀዋል፡ ከወይን ጠጅ ጥንስስ ቢጨምሩ ያጣፍጠዋል፡ የደከመን የሰውነትን ብልቶች እንዲነቁ ያደርጋል፡ እድሜ ያበዛል፡ መቅሰፍት ድንጋዩ በአለበት ሁሉ አይገባም፡ በዚህ የድንጋይ ጥበብ አለ፡ ለጽላት ዝብታ ብትቀርፀው መልካም ነው፡ እንደዋንጫ ቀርፀህ የፀበል መጠጫ ብታደርገው ከህመም ይፈውሳል፡ እድሜም ይቀጥላል፡ ትንሹ ውኃ ብዙ ይሆናል፡ ሲጠጡት ከባድ የማይዋጥ ይሆናል፡ ቆይቶ ሰውነትን ያዝናናል ድካምንም ያጠፋል፡ እንደመስቀል ቀርፀህ የታመመን ሰው እሽበት ይፈወሳል፡ የእግዚአብሔር ጸጋ አለውና፡፡

84. **እቫ** ፡- የድንጋዮች ልጅ እቨን ድንጋይ ነው፡ የድንጋይ ልጅ የተባለበት ከጠፍጣፉ ድንጋይ ላይ ቅልሞሽ መስሉ ተለጥፎ ወይም ተሰክቶ ስለሚገኝ ነው፡ ይህን ድንጋይ አርባ ዘጠኙን

ሰብስቦ በጕታ በቡሃቃ ከመዝገብ ውስጥ ቢያስቀምጡት ያበረክታል፡ እቃው ሁሉ ረድኤት አይለየውም።

85. **እብነ-ጎጉል** ፡- የሚባል እሱ፡ እርሱ በአለበት ሳር አይበቅልም፡ ስትነካው ትምክ ይላል፡ ከበረሃና ከምድረ በዳ ታገኘው አለህ፡ ድንገት ለታመመ ሰውና ጻር ለበዛበት ያንተራስከው እንደሆነ ይሞታል፡ እርሱ ባለበት ሁሉ ባድማ ጠፍ ይሆናል፡ ሰው አይኖርም የጥፋት ድንጋይ ነው።

86. **እብነሐኪም** ፡- የሚባል መልኩ ልብሰ ማርያም ደማቃ ሰማያዊ ነው፡ በርሃ ይገኛል፡ ከብረሰማይ ይመስላል፡ እሾህ የወጋው አውሬ የነከሰው ሂዶ ሲቆምበት ይፈውሳቸዋል፡ ሰዎችም እንዲሁ ቢታሹበትና ቢቆሙበት ይፈወሳሉ፡ በቤተ መቅደስ አጠገብ አስቀምጠው ከጥፋትና ከመቅሰፍት ይሰውራል፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ያድርበታል።

87. **እብነ - መድሎት**፡ የሚዛን ድንጋይ ተብሎ ይታወቃል፡ ሚዛን ይመስላልና ውኃ ሲሄድበት ከከረመ አሸዋ ውስጥ ታገኘው አለህ፡ ሚስት ስታገባ ክፍልህ እንደሆነች ለማወቅ እንደሚዛን ሰርተህ ስምህን በቀኝ ስሙዋን በግራ ጽፈህ መዝን፡ ክፍልህ ከሆነች የስሙዋ ሐብል የአንተ ስም ካለበት ሐብል ይጠመጠማል።

88. **እብነ ሰንፔር** ፦ እንደፍርሃም ቀይ የሆነ የጠቆረ የፅንቁ ድንጋይ ነው፡ ላዩ ድንጋይ መስሉ ውስጡ በጣም ቀይ የሆነ እንቁ ነው፡ ለፈርጥ ለተለያዩ ጌጦች የሚሆን ነው፡ ከዝሆን ጥርስ ጋር አያይዘህ ብትቀርፀው የሚያስገርም ጌጥ ይሆናል።

89. **እብነ በረድ** ፦ በረዶ የመሰለ ነጭ ድንጋይ ነው፡ ይህ በረዶ ወይም ጨው የመሰለ ድንጋይ ቢጠርቡት የሚጠረብ ነው፡ በፈለከው መልክ ይቀረጻል፡ ጠንካራ አይደለም፡ ይሰበራል፡ ነገር ግን ጠንካራ ለማድረግ ወቅጠህ ቀስመ እብንና ባሩድ የተባሉትን ጨምረህ በአንድ ላይ ቀቅለው ወይም ጥበሰው፡ ነጭ ይሆንልሃል።

90. **እብነ እዝዝ** ፡ ባልጩት ድንጋይ ነው፡ መልኩ ጥቁር ሆኖ ተነባብሮ ታገኘው አለህ፡ የቀመ ፍልጥ እንጨት ወይም የተነባበረ ብረት መስሉ ይገኛል፡ ለቢላዋ ለሰይፍ በእሳት እያጋልክና እያቀለጥክ በዘዴህ ሥራው፡ ከዚህ ድንጋይ የተሠራ ቢላዋ መቁረጫ ስለቱ አይበርድም ለምሳጭም ይሆናል።

91. **እብነ ኩኩህ** ፦ ጠንካራ የሆነ ድንጋይ ነው፡ የእሳት ድንጋይ ነው፡ ከዚህ ድንጋይ ውስጥ የፈሰቀ ውኃ ፀበል ነው፡ ለሰውነት መልካም ነው፡ ድንጋይነቱን የሚፈረከሰው የለም፡ ከእሳቱ ውስጥ ተለይቶ መልኩ ይታወቃል።

92. **እብነ የብል** ፦ የሚባል ድንጋይ በምድረ በዳ በረዶ መስሎ ወድቆ ታገኘው አለህ፡ እሱ በአለበት ውኃ አይገኝም፡ በዝግጅ ሳጥን ውስጥ ከተህ ከምንጭ ራስ ብትቀብረው ምንጩ ይደርቃል፡ ከከፋው መደብ ሥራ ነውና አታድርግ።

93. **እብነ ነበልባል** ፦ የሚባል ጥቁር አለት የመሰለ ነው፡ መልኩ ቀይ ነጠብጣብ አለበት፡ ዲን ነስንሰህ በጨርቅ ሸፍነህ የአስቀመጥከው እንደሆነ እሳት ያወጣል። በዚህ የጥፋትና የእልቀት መንፈስ አለበትና አጥፍተህ እንዳትጠፋ በዚህ ድንጋይ አትመራመር።

94. **ሌቡ** ፦ ሲያጋጩት እሳት የሚያወጣ ድንጋይ ነው፡ በጅረት ድንጋይ በበዛበት ወንዝ መካከል ታገኘው አለህ፡ መልኩ ጥቁር ነው፡ አጋጨው እሳት ይወጣዋል፡ በድንጋዩ ሌላ ብዙ ጥበብ አለውና ተፈላሰፍበት ታገኘው አለህ።

95. **ሽቡደ** ፦ መርዘኛ የሆነና የሚያቆስል ጥቁር ድንጋይ፡ ይህ ድንጋይ በአለበት አካባቢ የከሰል ድንጋይና ዲን ወይም ባሩድ ይገኙበታል፡ በኢትዮጵያ በብዙ ቦታዎች ሲኖር በደብልጥ በመተሐራና በአዋሽ ወንዝ አጠገብ ይገኛል።

96. **ባቡዩ** ፦ ድፍድፍ የመሰለ ሲሆን እሳት ያልነካቸውን የወርቅና የእንቁ ድንጋዮችን የማሳደግ ኃይል የአለውና እንዲሁም ድንጋዮችን የማሳደግ ኃይል አለው፡ ከዚህ ድንጋይ መሐል

እሳት የእልነካውን ወርቅ ብታስቀምጥለት በእሙቱ ክብደት ጨምሮ ታገኘው አለህ፡ በዋሻ ውስጥ እንደ አርባጫ አፈር ተከምሮ ታገኘው አለህ፡ ሁልጊዜ እርጥብ የሚመስል ነው፡ የድንጋይ ጥበብ ለፈላስፋ ሰው ብቻ ነው።

97. [redacted] :- የማር ሰፈፍ የመሰለ ድንጋይ ነው፡ ይህ ድንጋይ ማር ቀብተህ ከቀፎ ውስጥ አስቀምጠው፡ ንቦች ማር ይሰራሉ፡ ጠንካራ ይሆናሉ፡ በሌላው ዓመት አውጥተህ ከምትዝየው እቃ አጠገብ አስቀምጠው፡ ዝያህ የተሙዋሟቀ ይሆንልሃል፡ ምህሳበ ንዋይ ነው።

98. [redacted] :- የድንጋይ ሙጫ የአለውና በክረምት ወለላ የመሰለ ልጋግ የሚያፈልቅ መልኩ ቢጫ አረንጓዴ ከሆነ መርዛማ ነው፡ ሰማያዊ ነጭ ከሆነ ወይም ቀይ መርዛማ አይደለም፡ ለቆዳ ደዌ በውሀ ዘፍዝፈህ አጥለህ አጠጣ፡ ለማይድን ምሺሮ አስርለት ይፈወሳል። በጣም ቀይ ከሆነ ለቀለም ለነድ ቀለም ይሆንሃል፡ ቀምመው በዚህ ብዙ ጥበብ አለና አስተውለህ አጥናው።

99. [redacted] :- በክረምት ወራት የሚበቅል ዘጭመረጭ ድንጋይ ከመሬት ውስጥ የአርባጫ አፈር ወይም ሞላላ እንጉዳይ መስሉ ይወጣል ሲደርቅ ጠንካራ ይሆናል፡ ቡላ ጥቁር የሆነው ለሆድ ህመም ከክርቤ ጋር ዘፍዝፎ መጠጣትና ሰውነትን መቀባት ነው፡ አፈርማ መልክ ያለውን ለቁስል ማድረቂያ ብቻ እንጂ እንዳይጠጣ መርዝነት አለው።

100. **ቤዛ** ፡- የተሸላለመና የአንጠ ድንጋይ ነው፡ በቤት ውስጥ ቢያስቀምጡት ለቅርፅ የተቀመጡትን ጌጦች ውበት ይጨምርላቸዋል፡ ከቀን ወደቀን ያድሳቸዋል፡ ሁልጊዜ ቤዛ ድንጋይ በአለበት ሁሉ አዲስ መስሎ ይታያል፡ ታይቶ አይጠገብም፡ ቤባ ድንጋይ ሰዎች ሸላልመው ያጌጡትና የአሳመሩት የሚመስል ብዙ ዓይነት ቅርጽ የአለው ነው፡ በዚህ የድንጋዮች እንቁ ጥበብ ከበረ፡ በዋሻ ውስጥ በምድረ በዳ ድንጋይ በበዛበት ታገኘውአለህ።

101. **ኩዮቤ** ፡- የገነት ድንጋይ መልኩ ሰማያዊ የመሰለና አረንጓዴ የተቀባ ይመስላል፡ ወዝ የጠገበና የልብስ ማጠቢያ እስትም ይመስላል፡ የሱባን ፊደል የመሰለና የተሚሟረ ጽሁፍ ይገኝበታል፡ ብዙ ግዜ ድንጋይ በበዛበት ወንዝ ይገኛል።

ከዚህ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ የተመኙትን ቢሳሉ ስአለት ይሰማል፡ የአሰቡት ይፈጸማል፡ በእርሱ ላይ ዳኛ ተቀምጦ ቢፈርድ ፍረዱ የተስተካከለ ይሆናል፡ ልጅ ያጣች መካን ሴት ታቅፋው ብትሳል ትወልዳለች፡ በዚህ የድንጋዮች ጥበብ አለ።

ይህ ድንጋይ ባለበት ባህር ውስጥ የዛጉልና የአሣ ዓይነት ዘሮች ይበዙበታል፡ ይረቡበታል፡ ቅርፍቱ ፋጋ የመሰለው ዛጉል ሰማያዊ ደም አለውና ደሙን ከዘር ለተላለፈበት የልብ የኩላሊት የሳንባ የጉበት የአእምሮ ህመም ላለው ሰው ከደሙ ጋር ቢቀላቅሉለት ይፈወሳል። ሥጋውን በባዶ ሆድ ቢበሉት በፋጋው ውኃ ቢጠጡበት ለሁሉ ነገር ይበጃል፡ ወንዱ ጅራት

ሲኖረው ሴቲቱ የላትም፡ ደማቸው ቢጫና አረንጓዴ የሆኑትን ለምግብ አትጠቀም፡ ነገር ግን እንደውኃ የመሰለ ሰማያዊና ቀይ ደም ያላቸው ዛጉሉች ለጤና ለመድኃኒት ይሆናሉ፡ አጥናቸው።

102. ሻሻን ፡- የእንስት ብልት የመሰለ ነው፡ ቅርጹ ይምሰል እንጂ ትልቅም ትንሽም አለ፡ በውስጡ ወይም በጣብቂ የድንጋይ ሙጫ የመሰለ ታገኛለህ፡ መካን ለሆነ ነገር ሁሉ በውኃ ውስጥ አሳድረህ ውኃውን አጠጣ፡ ሆዳቸውን አሸበት፡ ይወልዳሉ፡ እሱን ሸርፎ ቢይዙት አዘውትረው ዘማዊና ዘማዊት ያደርጋል፡ ወንድ ለጠላች ሴት ወይም ተባት ለጠላች እንስት እንስሳ እሰርላት ከጊዜ በኋላ ጠባይዋ ይቀየርና የምትወድና የምታፈቅር ትሆናለች፡ ባባን መልኩ ማንኛውንም ድንጋይ ይመስላል፡ ነገር ግን ሻሻን መስሉ እንደቀይ ሥጋ የመሰረው ፍንዱቅ በጣም ትንሽ ነው፡ ቢይዙትም ፍትወት ያበዛል፡ ጤነኛ አያደርግም በዚህ ይለያያሉ።

103. ሾሻሺ ፡- ለታቦት የሚሆን ድንጋይ እንደ እንጨት የሚጠረብ ለሣንቃ ለሣጥን የሚሆን ነው፡ መልኩ አረንጓዴ ቀይ ነው፡ ነጭም አለው፡ እርሱን ለጽላት ስሌዳ ለታቦት ገበታ ጠርበህ በቤተመቅደስ በክብር ብታስቀምጠውና ወደ እግዚአብሔር ብትጸልይ ይሰማሃል፡ ስእለትህንም ይፈጽማል፡ የተሳልከውን

ባትሰጥ መቅሰፍት ያመጣብሃል፡ እንዲሁ ለተሰያዩ ቅርጾች ብትጠርበው ይሆናል ውበት አለውና።

104. **ባሻ** ፦ እንደማማኔት ብዙ ድቡልቡል የሆኑ ድንጋዮች የተጠባበቁበት ድንጋይ ነው፡ ይህን ድንጋይ አገሩን አዙረህ የወንዝ ድንጋዮች ሰብስበህ ከመሐል አድርገህ ሐውልት ብትሰራበት፡ ብዙ ህዝብ የሚኖርበት የሚከማችበት ከተማ የረድኤትና የበረከት የሰላምና የፍቅር ከተማ ዝና የአለው ከተማ ይሆንልሃል፡ በመልክ ቀለም ተለያይተው በግብር አንድ የሆኑ ሉዋውና ባሻ ናቸው፡ ሁለቱን በአንድ ላይ አገናኝተህ በቤተ መቅደስ ውስጥ በአደባባይ በገበያ መሐል ብትቀብራቸውና በበላያቸው ሐውልት ብታቆምና በሐውልቱ ላይ በሱባ ፊደል የአገሩን ስም ብትፅፍ የማይጠፋ ባለታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ በክብር ስሙ የማይቀየር የታወቀ ከተማ ይሆንልሃል። በዚህ የድንጋዮች ጥበብ እንዳለ ታውቃለህ፡ ለሌላም ሰው ታስረዳለህ፡ ስለዚህ የጥበብ ምስጢር ከበረ።

105. **ቢብያ** ፦ ክብ ሁኖ ቀዳዳ የአለው ድንጋይ ነው፡ ቤተመቅደስ ስታንፅ ቤትህን ስትሠራ ሐውልት ስታቆም በመጨረሻ ከመደምደሚያው ላይ ድምፅ ባለው ብረት ላይ ሰክተህ ስቀለው፡ ባለታምር ይሆናል። ብዙ ነገር ይታይበታል፡ በእመትባል ቀን ሦስት ግዜ ብትዞር ወይም ሕዝቡ በደስታ

በዞረውና ቢያከብረው እስከዓመት ድረስ ክፉ ነገር ለዞረው አይደርስበትም፡ ክብነቱ የጋን ማስቀመጫ የመሰለ ነው፡ መልኩ ማንኛውንም ድንጋይ ይመስላል፡ ሰው የከበበውና የነደለው መስሎ ታየውአለህና በዚህ ታውቀው አለህ።

106. **ቤባንያ** ፡ ቤተብርሃን ወይም ኖህተብርሃን ርእዮተ ብርሃን እብነ ራእይ ኖህተ ሰማይ የሚባል ድንጋይ ዘይት የፈሰሰበት አራት ማእዘን የአለው ነው፡ የአልዘለቀ ቀዳዳ አለው፡ መልኩ ቀይ ደም ይመስላል፡ ከእርሱ ጋር ቅልሞሽ የመሰሉ ድንጋዮች አሉት፡ እነሱን አውጥተህ የያዝካቸው እንደሆነ በሰው ዘንድ የተከበርከና የተወደድክ ትሆናለህ፡ ቤባንያ እብነ ራእይ የተባለውን ድንጋይ ተንተርሰህ የተኛህ እንደሆነ ገነት ተከፍቶ ታያለህ፡ መጠጊያ እንትራስ መስሎ ይገኛልና።

ይህ ድንጋይን ያእቆብ በሉዛ አግኝቶ ተንተርሶት የተኛና በራእይ የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበትና ይወርዱበት እንደነበር የአየበት ነው፡ ስለዚህ ራእይ የአየበትን ስፍራ ድንጋዩን ሐውልት አድርጐ አቁሞ ቤቴል ብሎ ጠራው፡ እግዚአብሔርን አይቶብታልና የእግዚአብሔር ቤት ብሎ ሰየመው፡ ይህን የራእይ ድንጋይ ፍርድ በሚሰጥበት መካከል የቀበርከው እንደሆነ የተስተካከለ ፍርድ ይሰጥበታል፡ ህግ ይፀናበታል፡ በቤተ መቅደስ ደጃፍ የቀበርከው እንደሆነ እርሱን አልፈው የሚሳሉ ሁሉ ስእለታቸው በፍጥነት ይደርሳል፡ በእርሱ ላይ የእግዚአብሔርን ታቦተ ህግ የእስቀመጥከበት

እንደሆነ በዚያ የሚጸለየው ጸሎት ከእግዚአብሔር ፊት ይደርሳል፡ ክቡር ድንጋይ ነው።

107. **ብሄያ** ፡- የሚባል ድንጋይ እንክብልል ሆኖ ከፉ በረንቅ ይመስላል፡ ለበረከት ሶስቱን ድንጋዮች ጉልተህ የቅቤ ዕቃ የወተት ጉርና የእህል ጉታ አስቀመጥበት ይበረክታል፡ ቤት ስትሰራ በሶስት ማእዘን ቅበረው የመሰረት መጀመሪያ አድርገው፡ ሐብታም ትሆናለህ ለቤተ መቅደስም እንዲሁ አድርግ፡ በእርሱ የታመነ አያፍርም መሠረቱ የጸና ነውና።

108. **ብርሌ** ፡- የሚባል በበረሃና በሜዳ የሚገኝ ነው፡ ከበረሃ የወደቀ መስታወት ይመስላል፡ በጣም የጠራ ነው፡ ውኃ ውስጥ አይገኝም፡ ትንሽ ሸርፉህ በወገብህ አድርገህ ባህር ውስጥ ብትገባ አትሰጥምም፡ የፈለከውን አሣ ለመያዝ ወይም ለመግደል አያቅትህም፡ ከመርከብህ ግንባር ቀደም ላይ ብታስቀምጠው ማእበል አያሰጥምብህም፡ በዚህ የድንጋዮችና የእንቁ ጥበብ ምስጢር አለና አስተውለህ መርምር።

109. **ብያ** ፡- የተባለ በመጠኑ እንጉዳይን ይመስላል፡ ሐውልት ለማቆም ወይም የድንጋይ አዳራሽ ለመስራት በብዙ ሰብስቦ የብረት ወይም የእንጨት አራት አራት ሰሌዳ አዘጋጅቶ ሰማያዊ መልክ የአለውና ከመሬት ውስጥ ወደላይ እርጥብ ጭቃ የመሰለ የሚገፋና የሚከምር ቀሌምንጦስ ወይም እብነ አድማስ የሚባል አለ፡ እርሱን አውጥተህ ሰሌዳውን በአራት

ማእዘን እንደሳጥን አስቀምጠህ ቀሌምንጦሱን ከመሃል አድርገው፡ በበላዩ ብያ የተባለውን ድንጋይ ሞልተህ ተወው በበነገታው አቅልጦ አንድ ድንጋይ አድርጉት ታገኘው አለህ፡ ሰሌዳውን ክፍ በማድረግ እንዲሁ ሌላ በበላዩ የመሰለህን ስእል ወይም ቅርፅ ወይም ጌጥ ወይም ጽሁፍ እንዲኖረው በሰሌዳው ገበታ ላይ ቀርፀህ አስቀምጥና ቀሌምጦሱን በውስጥ እያደረክ ብያውን ሞልተኸው ሂድ፡ በዚህ ዓይነት አስክፈለከው ቁመት ድረስ የድንጋይ ሐውልት ማቆም ትችላለህ፡ ቅጽርህንም በዚሁ መልክ ማነጽና የድንጋይ አጥር ግቢ ማድረግ ትችልአለህ፡ ብያ ከፋይ ድንጋይ መስሎ ክርችፍችፍ ያለ ከባድ ድንጋይ ነው።

110. **ባ - ባኤዐ** :- እግዚአብሔር ረዳኝ የሚባል እንደሐውልት የቆመ ድንጋይ ነው፡ ይህ ድንጋይ ባለበት ቤተ መቅደስ ብታንፅ እግዚአብሔር ስእለትን ይፈጽምበታል፡ ቤትህን ብትሰራበት በረከት አይጠፋም፡ ሁሉ ይባረክልሃል፡ ከተማ ብትከትም ዝብያው የደመቀ ይሆናል።

111. **ባሩድ** :- ከእሳት ሲጨምሩት ቦግ ብሎ የሚቃጠል የድንጋይ አፈር መልኩ አረንጓዴም ቀይም ቢጫም አለው፡ የድንጋይ ሳጥን ወይም የድንጋይ ሐውልት ለመስራት ላዩ ነጭ መስሎ ሲወቅሩት የአረንጓዴ አይነት ሆኖ ጥቁር የሆነ ቀለመ አብንን እኩል በኩል ወቅጠህ ዘይትና ውሃ ቀላቅለህ በጥብጠውና ከጋን ውስጥ ከተህ በእሳት አፍላውና በውኃው የድቡሽት

ወይም የንጹህ አፈር አቡክበህ እንደፈለከው ሥራው፡ የድንጋይ ወይም የንጹህ አፈር አቡክበህ እንደፈለከው ሥራው፡ የድንጋይ ይሆንልሃል።

ሐውልት የድንጋይ ቤት የድንጋይ ሳጥን ይሆንልሃል።

ባላቅ ፡- የድንጋይ ሰሌዳ የሚባል በዚሁ ዓይነት የተሠራ ነው፡ የአክሱምን ከተማና ሐውልቶችዋን በጥበበ አእባን ሲሰራ የንጉሦች ንጉሥ አፄ አክሱማይ የተባለው አፊላስ ጠበብቶቹን ብያና ባሩድ ቀሌምንጦስና ቀሰመ እብን በተባሉ እንዲሰሩ ስለ አዘዘ ትእዛዙን በማክበር ከተማዋን በአማረ መልክ ሰርተው ከሰባአሰባት በላይ የሚሆኑ ሐውልቶች እንደክበሩ ተመዝግቦአል።

112. **በሉር** ፡- ከበሐር ከዲብ ውስጥ የሚገኝ ነጭና ሰማያዊ መልክ የአለው የአልማዝ ድንጋይ ነው፡ ይህ የእንቁ ድንጋይ የሆነ በሉር እንደለንፔር እንቁ በታቦት ዙሪያ የሚለጠፍ ወይም ለልብሰ ክህነት የሚሆን እንጸባራቂ ድንጋይ ነው፡ በብዙ ቦታ በድንጋይ ውስጥም ይገኛል።

በሉር የተባለው እንቁ ድንጋይ ባለበት ሁሉ ሕዋሳት ይበዛሉ፡ በባሕር ውስጥ የሚኖሩ የዘራቸው እንቁላል እንዲበዛ ይልሱታል፡ አንዳንዶቹም ከሆዳቸው ውስጥ እንዲኖር ይውጡታል፡ ስታገኘው በከብር ቦታ ጌጥ አሰርተህ አስቀምጠው፡ የታመመን ብታሽበት ይፈወሳል፡ ወይም ሥቃዩና ጻረ ሞት እንዳይበዛበት ይገለዋል። ይህ ድንጋይ ባለበት ሥቃይ አይኖርም።

113. **ብ - ብርቱ** ፦ ወይም ብርቁ ወይም ብርቅርቅ የሚባል ድኟጋይ ሌሊት እንዳአንድ ግዜ የሚያበራ ደግሞም የሚጠፋ ድንጋይ አለ፡ ከዋሻ ውስጥ ወይም ከበሐር ዳር ታገኘው አለህ፡ እርሱ በአለበት ዋሻ ውስጥ እንደ እሳት ላንቃ የመሰለ ይታያል።

ይህን ብርቁን በረውሀ ወይም ሮሃ በተባለ ድንጋይ ወቅረህ አጕድጕደው፡ በጕደጕደው ላይ በጣም የጠራ ነጭ ድንጋይ በሰው ገጽ ወይም ከኮከብ ቅረፅ ወይም በፈለከው የእንስሳ ቅረፅ ቀርፀህ ከውስጡ አድርግና ሐውልት ሥራብት ወይም በቤትህ ውስጥ ቅበረው፡ የነጭ ድንጋዩን ቅርጽ የመሰለ በቤትህ በላይ በሌሊት ቁሞ ይታያል፡ እንዲሁ ጥቁር ድንጋይ ቀርፀህ ከአስቀመጥክበት በቀትር ጊዜ ጥላ የመሰለ ይታይበታል፡ ይህም ድንጋዩ በሚያበራብት ጊዜ ብቻ ነው፡ የሚታይ አንዳአንድ ግዜ በርቶ የሚጠፋበት ጊዜ አለው፡ የድንጋዩ ምስጢር አይታወቅም፡ ምክንያቱም ብርቁ በአለበት አለት ላይ የሚንቀሳቀስ ብርሃን ይታያልና፡ ተከታተለው ታገኘው አለህ፡ ብዙ የሆን ጥበብ በዚህ አለና ተፈላሰፍ።

ይህ ብርቁ የተባለ ድንጋይ ከበሐር ውስጥ ይገኛል፡ መልኩ በመአልት ቢጫ አረንጓዴ ነው፡ ወቅረህ ከተውከው ሌሊት የአበራል፡ ልዝብ አይደለም ሻካራ ነው፡ ደቁሰህ ከቅባት ጋር አድርገህ ተቀባ፡ ግርማ ሞገስ ይሆናል። ደቁሰህ ከምትበላው ከምትጠጣው ጋር ጨምረህ ብትበላ ወይም ብትጠጣ የአየህ

ሰው ሁሉ ያፈቅርሃል፡ ለህዝብ ፍቅር ይሆንሃል፡ መብረቅ ብዙ ጊዜ ይመታዋል፡ ይሰነጥቀዋል፡ ጭራ የመሰለ ይታይበታል። ብርቅ የምትባል አውሬ ተጠግታ ልጇ ትወልድበትአለች፡ ማንኛውም አውሬ መጥቶ ልጇዋን አይበላም፡ ልጇም እስከሚያድግ ከድንጋዩ ስር አይጠፋም፡ አንዳንድ ጊዜም ውስጡ የተከፈተ ይገኛል፡ በውስጡ ብትተኛና መብራቱ ሲበራ ገላህን ብታየው የሆድህን እቃ ሁሉ ታየውአለህ፡ መልክህን በመስታዋት እንደምታየው ከራስ እስከ እግርህ የአለውን ሁሉ አጥርተህ ታያለህ፡ ከደዌህ ከህመምህ ትፈወሳለህ፡ አራዊትም እንዲሁ የአደርጋሉ፡ ሲታመሙ ከስሩ ሄደው ይተኛሉና ይፈወሳሉ።

እንደሰጉን ቁመታም የሆነች ሙሴ የምትባል አንዳአንድ ጊዜ እንቁላል ትጥልበት አለች፡ ድንጋዩን እየወቀረች በእንቁላሉ ላይ ትረጭበትአለች፡ የታቀፈችበት እግሩዋ ፍህም ይመስላል፡ ከእርሱ ስር የተፈለፈለው ጫጩት ሆዱና እግሩ ያበራል፡ "ባሊሃልም በናትሊ ሱሊ ተቀናሂም ሮሜማላ ቦሃቢ ባሀፍዊ ቤሉተዊ መብራቂል መብረቅ ዝውእቱ ማህረኛየ ወመሐሯልየ" እያልክ ጸልየህ ስትመታው ይሰበራል፡ ይደቃልም፡ ምንግዜም የእግዚአብሔርን ስም በክብር እያመሰገንክ ፈትን ይሆንልሃል። በዚህ የድንጋይ ጥበብ አለና ምስጢሩ ለፈላስፋና ለተመራማሪ የተዘጋጀ በመሪራስ አማን በላይ ለእናንተ ለጠቢባን የተጻፈ። መጽሐፈ ጥበበ ዕንቁ አእባን ከትልቁ አእባን የተቀዳ።

114. **ብሪሻና** ፦ ነጸብራቁ የአየለና የሚፈልቅ እንደብራና ወረቀት የመሰለ ነው፣ ተኮብብሮ ታገኘው እሰህ፣ በጥበብህና በዘዴህ አልመህ ደቁሰህ እንደመስታዋት ብታደርገው የራቀውን አቅርቦ ለማየት መነጽር ብትሰራው ይሆንልሃል።

115. **ባርስ** ፦ በጣም የጠቆረ ድንጋይ ነው፣ መርዛማ የድንጋይ ከሰል ካለበት የሚገኝ ሕቡይ የሚባለው ድንጋይ ከሚገኝበትም ይገኛል፣ ነገር ግን እንደ ባሮስ የሚጠቁር ድንጋይ የለም፣ ይህን ድንጋይ አገሩን አዙሮ ቢቀብሩት የሰውን ህሊና ያአደነዝዛል፣ ምክራቸውን ያፈርሳል፣ እርሱ ካለበት የመነጨ ውኃ መርዘኛ ይሆናል፣ ቢጠጡትም በሽተኛ ያደርጋል፣ እንስሳዎች አይጠጡትም።

116. **በረቅ** ፦ ነጭ አፈር ከአለበት የሚገኝ አረንጓዴ ድን ጋይ ነው፣ ይህ ድንጋይ ባለበት ምስጥ አይኖርም፣ ከበድን ጋር ቅበረው አይፈርስም።

117. **በትር** ፦ ቀጥ ብሎ እንደውጋግራ የወጣ ድንጋይ ቡና መልክ ነው። በደጅህ በአደባባይ ብታቆመው መልካም ነው፣ የሰላም ዜና ሁልጊዜ ይሰማበታል።

118. **ብኪዘ** ፦ የወርቅ ማሳደጊያ ድንጋይ ይህም ድንጋይ ከብቶች በሚግጡት ግጦሽ የሚገኝና ከብቶች ከዋጡት በትርፍ አንጀትና በሐሞት ውስጥ የሚያድግና ከሞቱም በኋላ እድገቱ

የሚቀጥል ድንጋይ ነው። አንድን ነገር ለማግባባትና ለማላደን የሚያገለግል ድንጋይ ነው፡ በእሳት ከተጠበሰ ማደጉን ያቋርጣል፡ በውኃ ከኖረ እያደገ እየተለቀ ይሄዳል።

119. **በደቅ** ፡- ድንጋዩንና ድንጋዩን የሚያጣብቅ ከጊዜ በኋላ አንድ ድንጋይ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው። በዚህ ድንጋይ ድንጋዮችን እያያዝክ ያነጽክ እንደሆነ የድንጋይ ቤት ይሆንልሃል። ሉጹቅ እንደተባለው ድንጋይ አጣብቆ አንድ አይነት ያደርግልሃል። ሉጹቅ ቀይ ሥጋ ሲመስል በደቅ የተባለው ነጭ በረቅ ነው።

120. **በጺቃ** ፡- ጠመኔ ነጭ ድንጋይ ነው፡ ለኖራ የሚሆን የሚፍረከረክና የሚፈጭ ድንጋይ ነው፡ በየትም አገር ታገኘውአለህ፡ አድቀህ አልመህ ሉዋዮ ከተባለው ጋር ለውሰህ ቤትህን ምረገው።

121. **ቢርሌ** ፡- ክርስቶ እንደጠርሙስ የሚመስል ንጹህ የጠራ ድንጋይ ነው፡ እንደ ብረሌና እንደ ብርሌ የጠራም ቢሆን ሲወቅሩት ይፈረከሳል፡ ይጫራል፡ የተከበረና የወደደ አይደለም፡ እንደወርቃወርቂ ባልጨት ድንጋይ ነው፡ ለአድል ይሆንሃል።

122. **ቡረሌ** ፡- እንደመስዊት የጠራ ሰፈር' ' ሰጌጥ የሚሆን ሰበረከትም የሚሆን የእንቁ ድንጋይ ነው፣ ከአለት ውስጥ ታገኘው አለህ፣ ነጸብራቁ እንደኮከብ የአለ ነው፣ ብርሌ ከተባለው ለየት የአለ መልክ አለው።

123. **ቤዝ - ቤዛ** ፡- እንደ እንጉዳይ ወይም እንደጥላ የሆነ ድንጋይ ነው፣ የምድር ወፎች በስሩ የሚጠጉበትና እሳርን ጉዝጉዘው እንቁላላቸውን የሚጥሉበት ጫጩታቸውን የሚያሳድጉበት መጠጊያ ድንጋይ ነው፣ ምክንያቱም ከሚፈሩት ጠላት በምድር ከሚሳብና ከሚስለከለክ መርዘኛ እባብ ጠብቆ ይሰውራቸዋል፣ አንተም ሸርፌህ በአንገትህ ብታስር ከምትፈራውና ካላወከው ጠላት ይሰውርሃል፣ መርዝ የሆነ ነገር አይጎዳህም።

124. **ቤዴ** ፡- ድንጋይ ግንብ ስትገነባ መሰረት አድርገህ ብትገነባ አድጉ ታገኘው አለህ፣ ጠላት የማይደፍረው ሌባ የማይገባው ከውስጥ ክፉ ነገር የማያድርበት ቤት ይሆናል። ይህ ድንጋይ በአለበት የተወለደ ልጅ ሐብታም ይሆናል፣ የድንጋዩ መልክ የተነባበረ እጡብ ድንጋይ መስሉ ጠንካራ ቀይ ነው።

125. **እቦርጊላ እበርገቤ** ፡- ከአለት ላይ የጠጣ መጫወቻ የመሰለ የድንጋይ ገበታ ታገኘአለህ፣ በዙሪያው የአሉትን ዓለቶች የድንጋይ ገበታ ታገኘአለህ፣ በዙሪያው የአሉትን ዓለቶች የድንጋይ ገበታ ... ተመልከትና ጠባብ የሆነ ጉድጓድ ወይም በድንጋይ የተዘጋ

ታገኛለህ፡ ከጉድጓዱ ውስጥ ድቡልቡል ድንጋዮች አሉ፡ አገርክን አዙረህ ከቤትህ ቅበራቸው የልጅ ልጅህ ይከብራል።

126. **ቢኒክ** ፦ ድንጋይ ብዙ ዓይነት ቀለም የአለው ነው፣ ከሌላ ፕላኔት የመጣ ድንጋይ ነውና እሱ በወደቀበት ቦታ እፀዋት ይደርቃሉ፡ እንስሳና አራዊት አይኖርበትም እንዲሁ በሃገር ሰው የአኖርም ይሰደዳል ህዝብ የአፈልሳል፣ ትንሽም ትልቅም አለ፡ ከሌላ ዓለም መምጣቱን ለማወቅ ብትፈልግ እንደሌሉት ድንጋዮች ለማንሣት ብትሞክር ይከብድሃል፣ ስትነካውም ሰውነትክን ውርር ወይም ፈዘዝ ያደርግሃል፣ ወስደህ ጨው ባህር ውስጥ ጣለው ሕዋሳትን ይገድላል፣ በዚህ ብዙ የጥፋት ጥበብ አለ፡ ተፈላሰፍበት።

127. **ብሔሞት** ፦ ድንጋይ እባብ የማይለየው በውስጡ ንጹህ ወርቅ የሚገኝበት ነው፡ የታመመን ሰው ብታሽበት ይፈወሳል፣ ብሔሞት ድንጋይ መልኩ የሞከሳ ጥቁር አፈር ይመስላል፣ ከበረሃ ምድረ በዳ /ሣሃራ/ ታገኘው አለህ፡ ስትፈረክሰው ከውስጡ ንጹህ ወርቅ ታገኝበት አለህ፡ ለጌጥ አስርተህ አስረው ሐብታም ያደርጋል።

128. **ቢዳ** ፦ ድንጋይ ቀይ መልክ ያለው የመዳብ ድንጋይ ነው፣ እንዲሁ ቢጫና ቀይ ቀለም የአለውም አለ፡ እርሱ መሆኑን ለመለየት ገጣጥመህ የመጨረሻውን የጋለ ብረት

ብታስቀምጥበት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያሉት ሁሉ ይሞቃሉ። በዚህ ብዙ የጥበብ ሥራ መሥራት ይቻላል።

129. ብርት ፡- ሰናስ የሚሆን ድንጋይ ነው፣ መልኩ ቀይም ቢጫም ነው፡ ነገር ግን እንደ ቢጳ ድንጋይ በሳት ብትፈትነው ሙቀቱ ከአንዱ ወደ ሌላው አይተላለፍም፣ ስመከላከያ ዘዴ በዚህ መፈላሰፍ ትችላለህ፡ እስተውሰህ እጥና።

130. ብእዝ ፡- እንደ ደወል የሚጮህ ድንጋይ ነው፡ በእሳት አቅልጠህ ሰደወል ስቃጭል ብትሰራው ይሆንልሃል። ብርትንና ብእዝን በአንድ ላይ አቅልጠህ ብትሰራው ጥሩ ናስና ብረት መልኩም ያማረ ንጹህ ይሆናል።

131. ባባ ፡- መጠጊያ እንደ ቤት የሆነ ድንጋይ ነው፡ በበላዩ ዛፎችና ሳሮች ይበቅሉበታል፡ በውስጡ ብዙ ሕዋሳት ይፈጠሩበታል፡ አዲስ ፍጥረትን የሚያመጣ ድንጋይ ነው፡ ዘር ይበዛል መካን ሴት መካን ወንድ ከሱ ተጠግተው ቢያድሩና ሽርፈው በወገባቸው ቢያስሩት ይወልዳሉ፡ የተበላሸው ማህፀንና የጽንስ ስፍራው ይታደሳል፡ አዲስ ማህፀን ይሆናል።

132. ባቢ ፡- እንደ መጽሐፍ የመሰሰ ሆነ፡ የተጫጫረ ጠልሰም የአለበት ድንጋይ ነው፡ በእርሱ ላይ ስምህን ጽፈህ በተራራ ስር ብትቀብረው እድሜ ጠግበህ ትሞታለህ፡ ከብዙ አደጋ

ታመልጥአለሀ፡ በአደባባይ ብትቀብረው በህዝብ ዘንድ ተወዳጅና ተሰሚ ትሆናለህ፡፡ በዚህ የድንጋዮት ጥበብ ተወዳጅነትና ተፈላጊነት አለው፡ አንተም ፈላስፋ ጠቢብ ለመሆን አገርክን ለመገንባት ብቁ መሆን አሉብህ፡፡

133. **ሉዊቢ** ፡- ሶስት ማእዘን የአለው ድንጋይ ነው፡ ከተማ ስትቆረቁር በአራት ማእዘን አራርቀህ ቅበረው ወይም በበላዩ የከተማውን ስም ጻፍበት፡ የታወቀ ገበያ የንጋዴዎች መናሐሪያና መሰብሰቢያ ይሆንልሃል፡ ለሁሉም መልካም ነው፡ ማእዘኑን ሰው ጠርቦና ቀርጾ የተወው ይመስላል፡ በበሐር ውስጥ በድንጋዮች መካከል ታገኘው አለህ፡ መልኩ እንደቦታው ነውና በሦስትነቱ ማእዘን ለየው፡፡

134. **ሉሉ** ፡- ለባሩድ የሚሆን ድንጋይ ነው፡ እርሱ በአለበት የዲን አፈር ይገኝበታል፡ በእሳት የሚፈነዳና የሚረጭ ተቃጣይ ድንጋይ ነው፡ ጠንካራ አይደለም፡ ፍርክስ ይላል፡ ከእሳት ውስጥ ስትከተው ተጠንቀቅ ተረጭቶ ፊትህን እንዳያቃጥለው ብዙ ግዜ ማስተዋልና መጠንቀቅ ያስፈልግሃል አስተውለህ አድርግ፡፡

135. **ቢቡቁ** ፡- ድንጋይ ሲመቱት ድምፁ እየጐላና ተደራራቢ ድምፅ የሚያሳማ አስደናቂ ድንጋይ ነው፡ ለሙዚቃ መሳሪያ ብታደርገውና በእርሱ እየተጠቀምክ አምላክህን ብታመሰግን

ከቶ መንፈስ ይርቃል፡ የደስታና የፍቅር መንፈስ ይቀርብሃል፡ ለመንፈስህ መልካም ስሜት ይሆንልሃል።

136. **ቡደቡደ** ፡- የሚባል ቅልሞሽ የመሰለ ሰማያዊ ነጭ ቢጫ ቀይ መልክ ያለው ድንጋይ አለ፡ እነሱን ለቅመህ ወይም ሶስት ዓይነት ወይም ሰባት በወርቅ ለብጠህ እንደ ጌጥ ፈርጥ አድርገህ በአንገትህ ብትይዘው ወይም ከምታድርበት ብታስቀምጠው በዘመንህ ሁሉ መከራ አይደርስብህ ጠላት አያጠቃህም ይጠፋል እንጂ መግረሬፀር ነው፡ ለሃገርም በአደባባይ በቤተመቅደስ ጫፍ ላይ ስቀላቸው መልካም ነገር ይሆናል፡ ሕዝብ በሰላም ይኖራል።

137. **ቦቦ** ፡- እንደሐውልት የቆመ ድንጋይ አለ፡ ባቢ በተባለው ድንጋይ ላይ በተለያዩ ፊደሎች ስምህን ጽፈህ ከበቦ ስር ቅበር፡ ሙሉ ጤነኛ ትሆናለህ፡ ስምህ በክፉ አይነሣም፡ የአየህ ሁሉ ይወድሃል፡ የጠየከውን ይሰጥሃል፡ በሁሉ ዘንድ የተከበርክ ትሆናለህ፡ የጥበብ መንፈስ በዚህ አለ፡ ጥበበ ዕንቆ አእባን ለፈላስፋዎችና ለጠቢባን እንደተሰጠ አእምሮ ያለው ያስተውል።

138. **ቤባን** ፡- የተባለ ድንጋይ አዳምና ሄዋን ከገነት ወደ ምድረ ፋይድ እንደወረዱ ለብዙ ዓመት የኖሩበት የድንጋይ አዳራሽ ቤት ነው፡ ሦስት በሮች አሉት፡ ለብዙ ዘመን አእዋፋትና አሞራዎች የዱር እንስሳና አራዊት በውስጡ ይኖሩበታል፡

ይህ ቤባን የተባለ ድንጋይ ድንኪን መስሉ በኢልዳ ምድር ይገኛል፡ በእርሱ ውስጥ ሆነህ ሱባኤ የገባህ እንደሆን ወደፊት የሚሆነው ሁሉ ይታይሃልና ጽፌህ አስቀምጠው፡፡

139. **ቦባጂ** ፡- ክብ ሆኖ ላይና ታቹ የተደመጠ የመሰለ ነው፡ እርሱ ባለበት ቦታ አዳራሽ ቢሰሩ ቤተ እግዚአብሔር ቢያንፁ የማይናወጽ እንባ ይሆናል፡ የሰላም እንባ ይባላል፡ የእግዚአብሔር ረድኤትና ጸጋ አይለየውም፡፡

140. **በንያ** ፡- የተባለና አጥንት የመሰለ ድንጋይ አለ፡ ሰብሮ ወይም ቀርጾ ቢያስሩት የሰው ናፍቆት ወይም ትዝታ አይኖረውም፡ ከዘመድ ለተለየ አሰርለት እንዳይናፍቅ መርስአ ሀዘን ነው፡፡

141. **ቢያቤ** ፡- የቀመና የተተከለ ድንጋይ ነው፡ ከቆመበት ቢፈነቅሉትና ቢጥሉት ትልቅሰው ይሞታል፡ አገር ይፈልሳል ነገር ግን ቢተክሉትና እንደሐውልት ቢተክሉት የተከሉት ይበቅላል፡ የተወለዱት ያድጋሉ፡ ትላልቅ ሰዎች ይጠጡበታል መልኩ ነጣ የአለ ቡላ ድንጋይ ነው፡፡

142. **ቦዋን** ፡- ውስጡ ክፍት የሆነ ድንጋይ ነው፡ ይህ ድንጋይ በአለበት የምድር ዘይት ተቃጣይ ጋዝ ይገኝበታል፡ በዚህ ድንጋይ ውስጥ የብረት አፈር ወይም የብረት ድንጋይ ከተቀ ብታቀልጠው ጠርቶ ይወጣልሃል፡ ለብረት ማንጠሪያ

እንደዚህ ያለ ድንጋይ የለም፡ እንዲገን መስሉም ታገኘው አለህ።

143. [illegible] ፡- መልኩ የስንዴ ቀይ ዳቦና የዳቢ እንጀራ የሚመስል ድንጋይ ነው፡ በእሳት ላይ በተራራ ስር ተጣብቆ እንዲሁም ከድንጋዮች መሐል ሁብስት መስሉ ታገኘው አለህ፡ ምስሮች የሚመስል ባለሦስት ማእዘን ሐባዝ የሚባል እንጨት አለ፡ በሐበዝ ዘንግ "ያሙዝኤል ያሙዚሉ ያወሐብያኤል ያወሐቡ ይኤልሻዳይ ያሻሂዱ አልበዛቦ ያሐሎ ብለህ ሦስት ግዜ እየደገምክ ሦስት ግዜ ሲሳይ አምጣ በረከት አምጣ እያልክ ደጋግመህ የተመኘኸውን እየጠራህ ንካው ሳትበላ ሳትጠጣ አትውልም፡ ለፈለከው ነገር ሁሉ እየጠራህ በዘንጉ ምታው እግዚአብሔር በድንጋዩ ለስመስሉ ይሰጥሃል፡ የትም ምድረ በዳ ብትሄድ ጦምህን አታድርም፡ እንደለሌዳ ገበታ ጥረበው ባለሦስት ማዕዘን የሆነ እንደሆነ ለምሕሳበ ሲሳይ ባለአራት ማእዘን የሆነ እንደሆነ ለምሕሳበ ሰብእ ባለአምስት ማእዘን ለመስጥመ አጋንንት ወጸር ባለ ስድስት ማዕዘን ለውጊያ ለጦርነት ባለ ሰባት ማእዘን ለደስታ ለሁሉ ይሆንልሃል። በፈለከው መልክ ቀርፀህ በቤተ ጸሎት በክብር አኑረው።

144. ፓፓ ፡- አበባ የመሰለ ድንጋይ፥ ይህ ድንጋይ ዲብ በሆነ ከበሐር ውስጥ እንደ አበባ ዛፍ ሆኖ የሚገኝ ነው፡ ከውስጡ የሚረጨውን አሣዎች ለመብላት ከበውት ታገኛለህ፡ እርሱን

በጥንቃቄ አውጥተህ በጋን ውስጥ ውኃ ሞልተህ በግቢህ ውስጥ አስቀምጠው፡ የታመመ ከህመሙ ይፈወሳል፡ የተቸገረ ችግሩ ሁሉ ይጠፋለታል፡ ውኃውን እየቀየርክ አሣ ከውስጡ አድርግለት፡ በዚህ አበባ በመሰለ ተንቀሳቃሽ ድንጋይ ብዙ የድንጋዮች ጥበብ ምስጢር አለና ተፈላሰፍበት አዋቂ ጥበበኛ ትሆናለህና ፓፓየሚባለው የድንጋይ ዓይነት በአለበት ባለቅርፍት የዛጉል ዓይነት ይኖርበታል፡ መልኩን የሚቀያይር የሚረቅና ለዓይን እስኪማይታይ የሚደርስ የአሣ ዘር አብሮ ታገኛለህ፡ ሐሞቱን በሰውነትህ ብትቀብረው መልክህ እንደ እሱ ትቀያየር አለህ፡ ብትኳለው ብዙ ነገር ታያለህ፡፡

145. **ፔካ** ፡- እብነኤል ነጭ ድንጋይ ይመስልና የማይሰበር ጠንካራ ነው፡ ንጣቱ ወደለማያዊነት የአደላው ነው፡ ቤተ መቅደስ ወይም ቤተ መንግሥት ስትሰራ እንደመንበር አስመስለህ ብታስቀርፀውና በማሃል ብታስቀምጠው ለተመልካች የሚያስደንቅና የሚያስከብር ይሆናል፡ የክብርና የደስታ ቦታ ይሆናል፡ የሰዎችን ቀልብ ይስባል፡፡ ለተመልካቹ ሁሉ የደስታና የፍቅር ስሜት በልባቸው ያሳድራል፡ በውስጣቸው ይቀረጻል፡ የክህነትንና የንግሥናን ሥርአት ስታስፈጽም በፔካ መንበር ላይ /እብንኤል/ አስቀምጠህ ቅባቸው፡፡

146. ጜፕ ፡- ማረሻ የመሰለ ድንጋይ ይህ ድንጋይ ባለበት እህል ብትዘራ ብዙ ፍሬ ይሰጣል፡ ከብት ብታረባ ይበዙልሃል ከእርሻህ መሃል ከጎተራህ ውስጥ ወይም ከከብቶችህ በረት ውስጥ አድርገው፡ የምትነካው ሁሉ ይባረክልሃል የድንጋዩ መልክ ማገኛውን ድንጋይ መስሉ እንደማረሻ ብረት ይመስላል፡ ከእሳት ውስጥ ከአጋምከው የድንጋዩ ጥበብ ይፈርሣልና እንደዚሁ እንዳለ ተጠቀምበት።

147. ጜፔ ፡-ጥንድ የሆኑ ድንጋዮች የተጣበቁ

2. ፔፔ ፡- የተጣበቁ ሆነው ማለያየት የማይቻል ድንጋዮች ናቸው፡ በድንጋይ ጋን ውስጥ አድርገህ የትልቅ ዛፍ ተክል ትክልበት ትልቅ የአድባር ዛፍ ይሆንሃል በቤትህ ውስጥ በገንቦ አድርገህ የእህል ዓይነት ጨምረህ ብትቀብር ቤተሰቦችህ በሰላም ይኖራሉ፡ ዘርህ ሁሉ ይባረካል፡ ተፋቅረው ይኖራሉ፡ አይለያዩም ይተሳሰባሉ።

148. ጜፑፕ ፡- ደስ የሚል የፍቅር ድንጋይ ነው፡ ብዙ ግዜ ወፎች ከበውት ታያለህ፡ መልኩ ልዝብ ሆኖ በጣም ያልጠቆረ ሆኖ ወዝ የጠገበ ይመስላል፡ በቤትህ ውስጥ ብታስቀምጠው ቤተሰቦችህ ይፋቀራሉ፡ ወደ አንተ የመጡ ሁሉ ሥራህን ሁሉ ይሠሩልሃል፡ የጠየከውን ሁሉ ይፈጽሙልሃል፡ ፈቃድህን ሳይፈጽሙ ከአንተ አይርቁም፡ በዚህ የጥበብ ምስጢር አለ።

149. **ፕፔ**፡- ከባድና የማይንቀሣቀስ ድንጋይ ነው፡ ትንሹን ላንሣው ብትል አይሆንልህም፡ ሩይሪ ከተባለው ቀላል ድንጋይ ላይ አድርገህ በሪዶን መሽከርከሪያ ከፈለከው ቦታ ይደርሳል፡ በፐፔ ድንጋይ የተሠራ ግድብ አይፈርስም ተፈላሰፍበት፡፡

150. **ፑዩፓ** ፡- ቀጭን የሆነ ድምፅ የአለው የድንጋይ ደወል ይህን ድንጋይ በምሬንዝ ዘንግ እቃ ቢጠፋ የአገሌን ንብረት የወሰድክ ሰው መልስ፡ ባትመልስ ልብህን እስሬ መታሁህ ብለህ ሶስት ግዜ ምታው፡ ባይመልስ ይታመማል፡ ልቡ በየጊዜው ይደነግጣል፡ ይፈራል ስሌላም ጉዳይ እንዲሁ አድርግ ነገር ግን ክፉን በክፉት አትብቀል፡፡

151/ **ፑዋፓ** ፡ ደብልብል የሆነ ድንጋይ ነው፡ ከባድ ነገር የደረሰበት ሰው ከእሱ ላይ ተቀምጦ ነገሩን ያስብና ድንጋዩን አንክባሉ ነገሬን ከኔ ላይ አንሣ ብሎ ይሂድ፡ ነገሩ ሁሉ ይደመሰስሰታል፡፡

152/ **ፔኒ** ፡- የወንድ ብልት የመሰለ ድንጋይ አለ፡ እርሱን በውኃ ውስጥ አድርጉ አፍልቶ ይጠጣው፡ ይታጠብበት ወይም ድንጋዩን በእሳት አግሉ ከውኃ ውስጥ አድርጉ ይጠጣ፡ መንስኤ ወመጽንኤ እስኪት ነው፡ ያበረታል፡፡

153. **ጽጹዮ** ፡- የጠራ ወርቅ መልኩ ቢጫ የሆነ ነው፡ ነገር ግን እንደሌሎች ጠንካራ አይደለምና ከሌላው ጋር ቀላቅለህ እንጥረው።

154. **ጳዝዮን** ወይም **ጳግዮን** ግዮን በሚፈስባቸው ምድሮች የሚገኝ ቢጫ የወርቅ ድንጋይ ነው፡ ይህ ወርቅ በድንጋይ ውስጥ ታገኘው አለህ፡ ትልቅም ትንሽም ድቃቅም አለው፡ በእሳት ካልፈተንከው በየጊዜው ክብደት ስለሚጨምር አስቀምጠው።

155. **ጳጽ** ፡- ነጸብራቁ የኮከብ ቅርፅ አውታር የሚያሳይ እንቁ ድንጋይ ||ጣም ክቡርና ውድ የሆነ ነው፡ መልኩ ሰማያዊና ነጭ ነው፡ በእጅህ በአንገትህ ላይ በወርቅ አጣብቀህ እሰረው።

156. **ጽሬስስ** ፡- ከድንጋይ ውስጥ የሚገኝ ቀይ አልማዝ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ ለነስር ለደም ብዛት በአንገትህ እሰረው፡ የወር አበባዋ ለማያቋርጥና ለበዛባት ሴት በወገብዋ ትሰረው መልኩ በጣም ቀይ ሆኖ የጠራ የሚያንጸባርቅ ነው፡ ከሰውነትህ አትለየው።

157. **ኤጽ** ፡- ነጸብራቁ ከአንዱ ወደሌላው የሚሻገርና ከነጸብራቁ ኃይል የተነሣ የድንጋይ እሳትን የሚሰነጥቅ ዋሻን የመንደልና የማፍረስ ኃይል ያለው ነው፡ መልኩ የነጣ ሰማያዊና ቢጫ የመሰለ ነው፡ ኤጽን ከድንጋይ ላይ አስቀምጠህ ከፀሐይ

የሚቀበለውን የብርሃን ጨረር ወደሚያሳየው ነጸብራቅ ሌላ ኢጽን አስቀምጥ፡ ከሁለተኛው ኢጽ የሚወጣው ፍልቅታ የአረፈበት ቦታ ሲቀልጥ ታየውአለህ።

158. ቶጳ ፡- ለፊርጥ የሚሆን ነጭ ድቃቃ የእንቁዎች ናቸው፤ ከድንጋይ ውስጥ ስንድድ መስለው ታገኛቸው አለህ፤ የነጭ ዳጉሳ ፍሬ የአክላሉ እነሱን ብትይዝ እድሜ ጠግበህ ትሞታለህ፡ ከብዙ ፈተና ታመልጣለህ።

159. አጼ ፡- የእንቁ ድንጋዮች መፈልፈያና መሞረጃ ሞረድ የመሰለ ሸካራ ሆኖ ወዝ የአለው ድንጋይ ነው፤ ለእንቁ ድንጋይ መሞረጃ ለአንጥረኛ ሰው የሚሆን ነው፤ በቀላሉ በዘዴ ለመጠቀም ተፈላስፍበት፡ በዚህ ጥበብ ዕንቁ አእባን ጥበብ ከበረች አእምሮ ያለው ያስተውልና ያጥና ይፈላሰፍ፤ በዚህን ጊዜ ጥበብ ለጠቢባን ለፈላስፋዎች ሕይወት እንደሆነች ትታወቃለች፡ ትከብራለችም።

160. ቆጳ ፡- በጣም የጠቆረ ሆኖ ዘይት የፈሰሰበት የመሰለ የእንቁ ድንጋይ ነው፤ በነጭ እንቁ ላይ የአይን ቅርፅ አስመስለህ አሰራውና በጥቁር ገበታ ላይ ውሃ ሞልተህ ከውስጥ ከተተው የአሰብከውን ታያለህ፡ በጣትህ አስረህ ተንተርሰህ የተኛህ እንደሆነ በራእይ ወዳጅህና ጠላትከን ለይተህ ታውቃለህ፡ የራቀውን ነገር ለማየት ወይም የአለፈውን ነገር ለማወቅ

የሚወጣውንም ለመመልከት የሚሆን ታላቅ የእንቁ ድንጋዮች ጥበብ ነው፡ በዚህ ብዙ ነገር መለየት ይቻላል፡፡

161. ጰጰ ፡- አረንጓዴ ወርቅ ከሌላ ወርቅ ጋር ሸርቦ ቢያደርጉት መልካም ነው፡ ለዓይን መልካም ነው፡ የፍቅር ወርቅ ነው፡ ከድንጋይ ውስጥ ታገኘውአለህ፡፡

162. ጸጼ ፡- አንጸባራቂ ነጭ ወርቅ ነው፡ እንደ ብር መስሎ በጣም የጠራ ነው፡ አዘውትረህ አሰረው እድላም ትሆናለህ፡ መልካም ነው፡፡

163. ጵጲ ፡- ቡልጭት የመሰለ ለብር የሚሆን አለትና ድንጋይ ነው፡ በተራራ ስር በለ ዋሻ ውስጥ በገደል ነጭ ድንጋይ መስሎ ታገኘው አለህ፡ ለመሰለህ ነገር በእሳት አንጥረህ አብጀው፡ ለቀለበት ለመስቀል ይሆንልሃል፡፡ ሰውነትህ ሲጉሣቆል መልኩ ይዝጋል፡ ሲመችህ ይጠራል፡ አስተውለህ ተመልከተው፡፡

164. ጹጶ ፡- ደማቅ ሰማያዊ የሆነ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ መልኩ ዋርዴ ወፍ ይመስላል፡ ከድንጋይ ውስጥ ታገኘው አለህ፡ ያለወርቅ በአንገትህ አትሰረው፡ ነገር ግን ለዓይን መልካም ነው፡፡

165. **ጺጵይ**፡- ወርቅና ብርን አንዳንዶች እንቁዎችን የሚያቀልጥ ልምድድ ድንጋይ ነው፣ እንዲሁ ሜርኩሪን የሚያጣብቅ፣ አንድ የሚያደርግ ነው፣ መልኩ ነጭም ጥቁርም አለው፣ ነጩ ውኃን ያቀዘቅዝና ያረጋዋል፣ በእሱ የረጋ ውኃ አረንጓዴነት የአለው ሰማያዊ በረዶና ነጭ እሳት ይሆናል፣ በረዶ በተከመረበትና እሳተ ገሞራ በአለበት አገር ብቻ ይገኛል፣ በዚህ ልምድድ ድንጋይ የተለያዩ የጥበብ ዘዴዎችን መፍጠር ስለሚቻል አእምሮው የላቀ ጆሮ ያለው ይለማና ያስተውል ይፈላሰፍ።

166. **ጵዳን** ፡- የእሳተ ገሞራ ድንጋይ ውስጥ ለውስጥ የሚሳብና የአቀለጠውን ወደላይ የሚረጭ ነው፣ ጵዳን ለማግኘት ውቅያኖስ ባህር ውስጥ እሳተ ገሞራ በሚፈነዳበት አካባቢ እንደገመድ ተጠቅልሎ አርባሚ አፈር መስሎ ታገኘዋለህ፣ ትንሽ በጉጠጥ ቀርጠህ ሽሽ የፈለከውን ታቀልጥበታለህ።

167. **ጺዳዲ** ፡- የማግኔት ድንጋይና አፈር ነው፣ በእሳት እንፋሎት ብታቀልጠው አንድ ይሆንልሃል፣ አንዳንድ ብረቶችን ስቦ ይይዛቸዋል፣ ለብረት ማጣበቂያ ይሆናል፣ ተፈላሰፍበት።

168. **ጺዳንያ** ፡- የሰውን ገላ የሚስብና የሚያጣብቅ ድንጋይ ነው፣ መልኩ እንደማንኛውም ድንጋይ መስሎ ከያዘ አይለቅም፣ በማጣበቁ ጺዳንያን ለሙን መፍገዝ ሰብአ ይሉታል፣ ሰውን ከያዘ የሚይዝና የማይለቅ ማለት ነው፣ አራዊትንም እንዲሁ

አጣዝቦ ይይዛል፡ ውኃ ከያዘው ላይ ሲደፋበት ይሰቃል፡ በሌላ በኩል ድንጋዩ በተቀበረበት ቦታ ሰውን ይስባል፡ ለርቢም ይሆናል፡ ጳየ የሚባለው ድንጋይ ግን ያዝ ሰቀቅ ያደርጋል፡ እንጂ እንደጲዳንያ አጣዝቦ አይዝም፡ በዚህ የድንጋይ ምስጢር እለና ተፈላሰፍ ይገለጥልሃል።

169. **ጰደጳኒ** :- የብረት ድንጋይ ነው፡ የብረት ድንጋይ መሆኑን ለማወቅ ስትወቅረው እንደብረት ይጮሃል፡ ጥራቱን ለመለየት ድምፁን አስተውለህ አድምጥ፡ ለብረት የሚሆኑ ድንጋዮች ሻፎ ጥቁር ድንጋይና ድንጋይ መስሉ ጥቁር አፈር የሚመስሉ ሞከላ የመሰለው ሁሉ በእሳት ፈትነው፡ ብረት መሆኑን ታውቀው አለህ፡ የብረት ድንጋዮችና የድንጋይ አፈሮች ብዙ ዓይነት ስላሉ ተመራመር፡ ታውቃቸው አለህ።

170. **ጰዋጳዲ** :- የንብ ሰፈፍ የመሰለ ድንጋይ ነው፡ ከበሐር ውስጥ ታገኘው አለህ፡ መልኩ ነጭ ቡላም ነው፡ አጥንትም ይመስላል፡ ከምትቀመጥበት መንበር ጋር አጣዝበቀህ ሥራው፡ ከእሱ ላይ ሆነህ የአደረገውን ሰውን ብትጠይቅ ይነግርሃል።

171. **ጲጵያ** :- ብልጭት መስሉ እንደነብር ቆዳ ዝጉርጉር የሆነ ነው፡ ድንጋይ በበዛበት ድቡልቡል ሆኖ ታገኘው አለህ፡ ለጌጥ ብትቀርፀው ለጽዋ ለዋንጫ ብትጠርበው የአማረ ዝጉርጉር እቃ ይሆንልሃል።

172. **ጂርያ** ፡- ሲበትኑት መልሶ የሚገናኝ ልምድድ ሜርኩሪ ድንጋይ እርሱ ከአሰበት ቀሻ የሚፈልቅ ወይም የሚንጠበጠብ ውኃ ጉሮሮ ይከረከራል፡ ከባድ ውኃ ይሆናል፡ የብርና የወርቅ ማቅለጫ ይሆናል፡ አረንጓዴ ቢጫ የመሰለው መርዘኛ ነው፡ ጥቁር ሰማያዊ የመሰለው በአካባቢ የሚኖሩትን ተንቀሳቃሽ ሁሉ ይመርዛቸዋል፡ ከአካባቢህ አርቀህ አስቀምጠው እንጂ ዘርህን ይፈጃል፡ በእሱ የቀለጠን ወርቅ በአንገትህ አትሰረው፡ መልኩ ጥቁር ወይም ነጭ ኩል የመሰለው ለአንተም ይሁን ለሌላ አደገኛ አይደለም፡ ተጠቀምበት በዚህ ብዙ የጥበብ ምስጢር አለና ተፈላሰፍበት የጥበብ መንፈስ ሰጠቢባንና ለፈላስፋዎች እንደሆነ አእምሮ የአለው የአስተውል፡ ጆሮ ያለውም ይስማና ያድርግ ይጠበብም በዚህ ይከብራል።

173. **ጳሺድ** ፡- ብዙ ግዜ ከሌሎች ዓለሞችና ከዋክብት በፀሐይ ነጸብራቅ ተከፍለው ወደዚህ ዓለም የወደቁና የተበተኑ ድንጋዮች ናቸውና ብዙ ግዜ መልካቸው የሚለዋወጥ ወይም ከባድ የሆኑ ስለሆነ እሩቅ ባለ ቦታ አስቀምጣቸው እንጂ በምትኖርበት አካባቢ አታኑር፡ ለጤናና ለሕይወት አደገኞች ናቸውና በነርሱም የጥፋት ጥበብ አለ።

174. **ቢያ** ፡- ይህ ድንጋይ ባለበት አለት በጣደ እግርህ ስትሄድ ያዝ ያደርጋል፡ በጉደር ሽለቆዎች በማንደበረት አካባቢ ይገኛል፡ እንደ መናገዘዘ ሰብእ በጣም አያጣብቅም ለገጸያ ይሆናል በበር ቅብረው።

175. **ፀንያ** ፡- ወይም መርኩሪድን (emerald) የወርቅና የብር ዓይነቶችን በቀላል ያቀልጣቸዋል፡ እንዲሁም አንድን ነገር ለማዘጋጀትና ለማንቀሳቀስ ለመሰብሰብና ለመርጨት ያግዛል፡ ኩል መስሎ ከዋሻ ውስጥ ተቆቶ ታገኘው አለህ ጥቁር ቀይም ነጭም ነው።

176. **ፀኒ** ፡- የዲን አፈር ወይም የዲን ድንጋይ ነው፡ ነጫቴ ብጫና አረንጓዴ ዓይነት ቢጫ ነው፡ የድንጋይ ከሰል ማያያዣ ማቀጣጠያ ይሆናል፡ ተቃጣይ ቀላጭ ነው፡ ለብዙ ነገር ይሆናል፡ ለምች አደር ቁስል ለእከክ ሰውነትን ነጭ እያደረገ ለሚያሳክክና ለሚቀረፋ ገላ ደቁሶ በቅቤ መቀባትና በሙቀት ውስጥ በፀሐይ ላይ መቀመጥ እስከሚያልብ መቆየት ነው፡ ደጋግሞ እየታጠቡ ማድረግ ነው፡ ከዋጊኖስ ቅጠል ጋር በቅቤ ለውሶ መቀባት ነው፡ ይፈውሳል።

177. **ጹዲ-ጹዋዲ** ፡- መልኩ ብዙ ቀለም ያለውና የሚብለጨለጭ ድንጋይ ነው፡ ደቁሰህና ከነጭ ኖራ ጋር ለውሰህ የቤትህን ግድግዳ ብትቀባው ከቀን ወደቀን መልኩ ያንጸባርቃል፡ የቀለምን መልክ የሚያሳምር ድንጋይ ነው፡ በዚህ የጥበብ

ምስጢር እሰና አስተውሉ ስተመራመረ ሁሉ ግልጽ ይሆንለታል፡ ከዚህ የላቀ ምስጢርን ይገልጻል፡ የፈለገውን ያደርጋል።

178. **ቁየሻ** ፦ መስቀለኛ ነጸብራቅ የሚያሳይ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ ይህ ድንጋይ ከቤትህ በክብር ብታስቀምጠው የአስከብርሃል፡ ልጅ ይሰጥሃል፡ ሐብታም ያደርጋል፡ ገንዘብ ስትፈልግ የፈለከውን ከእሱ አጠገብ አስቀምጥለት ወተትን ማርን እህልን የመሰለ ሁሉ እንዲሁ የፈለከውን ነገር ከአጠገቡ አስቀምጥለት፡ ስእለት እንዲሰማ ከመቅደስ መሃል በክብር አስቀምጠው፡ መጥፎ ነገር ከእርሱ አርቅ ምሕሳበ ንዋይ ወመስተሳልም ነው፡ አንተም ንጹህ ሆነህ ተፈሳሰፍ አስተውለህ መርምር እንጂ አትጠራጠር የድንጋዮችንና የእንቁዎች ተፈጥሮ ጥበብ እንድትጋራ እግዚአብሔር ፈቅዶልሃል።

179. **ጸኮ**፦ ጥቁር የሆነና በመዶሻ ቢመቱት የማይሰበር ድንጋይ ነው፡ በእሱ ላይ ነጋሪት አስቀምጠህ የጠላትክን ስም እየጠራህ የመታህ እንደሆን አገር ለቆ ይሄዳል፡ አይመለስም የመርገም ድንጋይ ነው፡ ሴት ብትቀመጥበት ትመክናለች፣ መግረሬ ፀር ወመስተባርረ - ጸላእት ነው።

180. ጳጴጺ ፦ ለዘርፍና ለልብስ የሚሆን የወርቅ ድንጋይ ነው፤ ለቀለም ይሆናል፡ አቅልጠው ልብሱንም ቢነክሩበት ተጣብቆ እንደ መስሉ ይኖራል።

181. ጼር ፦ ወርቅና ብር እንደማግኔት የሚያጣብቅ ነው፤ ወርቅ ባለበት አገር ወስደህ ከጉርፍ ውኃ አጠገብ አስቀምጠው፡ ወርቁን ሰብስቦ አጣብቆ ይዞት ታገኘዋለህ፤ የወርቅ አፈር መልቀሚያ ነው፤ ከቀን ብዛት የሰበሰበውን የወርቅ አፈር አንድ አድርጐ አዋህዶት ታገኘው አለህ፤ አንተም ከዚህ ድንጋይ ጥበብ የተነሣ ብልህና አዋቂ እንድትሆን አስተውለህ መርምርና ሥራበት።

182. ጶርስ ፦ ወርቅም ይሁን ብር ማንኛውን ንጥረ ነገሮች የሚያጣብቅና የሚይዝ ነው፤ ነገር ግን ይህን ድንጋይ ለማግኘት እርስ በራሳቸው ተያይዘው ተጣብቀው ስታይ ለማለያየት ስትሞክር ተጣብቆ እንጂ ካለህ እርሱ እንዳለ ታውቃለህ፤ በዚህን ጊዜ ጴጳይ የተባለውን የእንቁ ማቅለጫ አምጥተህ በበላዩ ስታስቀምጥበት ሁሉም ይለያያሉ፤ በዚህን ጊዜ ጶርስ የተባለውን ድንጋይ ከፈለከው ላይ ለቅለህ ከብረት ከወርቅ የተሰሩትን ሣጥኖች አስጠጋለት፤ እንጠልጥሎና አጣብቆ ይይዛቸዋል፤ እንጂ ማንም ወይም ምንም ነገር ሊያስለቅቀው አይችልም። ከጶርስ ድንጋይ ኃይል የተነሣ አንተም አዲስ ጥበብ ለመፍጠር ተፈላስፍ አወቅበት።

183. **ማርሺ ሞሪሺ** ፡- መብረቅ ከወደቀበትና ከመታው መሬት ላይ የሚገኝ ድንጋይ ነው፤ ቤት ስትሰራ ሐውልት ስታቆም ከመሰረቱ ላይ አድርገህ ሥራ፤ መብረቅ አይወርድበትም፤ እንዲሁ መብረቅ ከእብነ በረድ ድንጋይ ላይ ከወደቀ ነጭ ሆኖ የማይፈለጥ ድንጋይ ታገኝአለህ ከመቅሰፍት ይሰውራልና ከቤትህ አኑረው።

184. **መዐክጼዴቅ** ፡- ወይም ማህተመ ክህነት ዘመልከ ጼዴቅ የሚባል ከበረሃ ወይም ከታላቅ ባህር ውስጥ እንደሰፈድ ከብ ሆኖ ቡግ እልም የሚል ብርሃን አለው፤ እርሱ ባለበት እንደመስታዋት የሆነው ቅንቅብ ዓይን የሚባለው የእንቁ ድንጋይና ወርቅ ከሚገኝበት ይገኛልና፤ እርሱን በምላስህ ልሰህ አደባባይ ብትወጣና ብትናገር ነገርህ ሁሉ ተሰሚና ተወዳጅ ይሆናል፡ የአየህ ሁሉ ያከብርሃል፡ ይወድሃል፡ በዋልክበት ሁሉ ሰላምና ፍቅር ይሆናል፡ በምትኖርበት አገር በበላዩ ላይ ስምህን ቀርፀህ አዙረህ ብትቀብረውና በበላዩ ሐውልት ብታቆም ወይም ቤተ መቅደስ ብታሰራ እድሜን ጠግበህ ትሞታለህ፤ እርሱ ባለበት የሚኖር ክፉ አያስብም ክፉ አይናገርም፡ ለሁሉም ፍቅርና ሰላይ የሚሰጥ የመልከ ጼዴቅ ድንጋይ ነው፤ በዚህ ድንጋይ ላይ የእግዚአብሔር ጸጋና መንፈስ አለ፡ እግዚአብሔር ለፈጠረው ሁሉ እንደየአጣው ስጦታውን አድሎታል፡ የአዳምና የሔዋን አጽምን በዚህ ክብ ድንጋይ እስከ ትንሣኤ መልከ ጼዴቅ አትሞታል።

185. **ረግድ** ፡- እንደ ደወል የሚጮህ እንቁ ድንጋይ ነው፡ አረንጓዴና ቡላ መልክ አለው፡ ለደወል ለቃጭል አድርገህ በእሱ እየመታህ ብትጸልይ፡ እግዚአብሔር ጸሎትክን ይሰማል፡ በመከራና በረሃብ ዘመን እርሱን እየመታህ ምህላ ብታደርግ ችነፈሩ ረሃቡ በሽታው ይጠፋል፡ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው የደንጋዮች ኃይል ምስጢር በጥበበ ዕንቆ አእባን ተገልጾ ተአወቀ።

186. **ህዕቅ** ፡- ለወርቅ ጥምዝ የሚሆንና የእንቁዎች መደገፊያና ማሰሪያ የሚሆን ቢጫ ወይም ነጭ ወርቅ ነው፡ ከዜጥ በስተቀር ለሌላ የድንጋይ ጥበብ የለውም።

187. **ሴተምት** ፡- በወርቅ የተጠለፈ የእንቁ ማርዳ የሚሆን የወይን ጠጅ ወይም ሰማያዊ መልክ ያለው የአልማዝ ድንጋይ ነው።

188. **ርግድ**፡- ሰማያዊ አረንጓዴ ቀይ ቀለም የአለውና እንጸባራቂ የእንቁ ድንጋይ፡ ይህ ድንጋይ በቀላል የማይቀረጽ ነው፡ ነገር ግን በጥበብ እሳት ኃይል ከተቀረጸ መልኩ የማይቀይር ሁልጊዜ እንጸባራቂ ንጹህ እንቁ ነው፡ እንደፈለከው ቅረጸው።

189. **ሚሱስ**፡- ልብ የሚነካና አንጸባራቂ የእንቁ ድንጋይ ሲታመመና ለአዘነ ሰው በራሱ ላይ አጨኸህ እሰርለት፣ የጠራ ሲሙቱት ቀጭንና ለስላሳ ድምፅ ያለው አልማዝ ነው፣ ልዩ ልዩ የሆነ ቀለም አለው፡ በድምጹ ለየው።

190. **ሞሶሞ** ፡ ደማቃ ሰማያዊ የእንቁ ድንጋይ ከድንጋይ ውስጥ የሚወጣ ነው፡ ከምትበላው ከምትጠጣው ውስጥ እያስቀመጥክ ብትበላ ወይም ብትጠጣ አዋቂ ብልህ ትሆናለህ፡ ከቡኸቃ ውስጥ አድርገው፡ የጥበብ መንፈስና ጸጋ በዚህ እንደከቦረ አውቀህ አንተም ክበርበት።

191. **ሽም/ ሺም**፡- መስታዋት የመሰለ ድንጋይ አለ፡ አንዱን ትንሽና አንዱን ትልቅ አድርገህ በዘንግ ፈልፍለህ አንዱን በጫፍ አንደኛው በስር ገጥመህ የራቀን ነገር አቅርቦ ያሳይሃል፡ ሽም ብሂል አነጣጥሮና አቅርቦ የሚያሳይ መነጽር ማለት ነው።

192. **ምቀደሀ** ፡- ዝብታ የመሰለ ድንጋይ ነው፡ ሰባት ዓይነት ድቡልቡል ድንጋይ አድርገህ በበላዩ የበግ ደም የዶሮ ደም አፍሰህ ብትጸልይና ብትሳል ይፈጸማል፡ ድንጋዮችን ስቀላቸው።

193. **ስሚር** ፡- የፀሐይ ጨረር ሲያርፍበት ፍልቅታው እንደቀስተ ደመና የተለያዩ ቀለሞች የእሉት የሚያሳይ እርሱን እንደመስታዋት አድርገህ ብትሰራው መልክህን አጥርቶ

ያሳይሃል፡ አሜር ማለት የፀሐይ ጨረር ማለት ነው፡ ሜርም ይባላል፡ ከፀሐይ ብርሃን ላይ አድርገህ ጨረሩን ወደቤትህ አስገባው፡ ለሐብት ይሆናል።

194. **ቆሞ**፡- በእሳት ውስጥ ሲከቱት የሚቀልጥ ነው፡ ይህን ድንጋይ እንደ ብልቃጥ አድርገህ በተለየ ቀለም አየከርክ ብትሰራው ለፈለከው ዓይነትና ለጠርሙስ ዓይነት ይሆናል፡ በእርሱ ውስጥ ፀበል አድርገህ ብትፀልይበትና ብትጠጣው አእምሮህ ብርሃን ይሆናል ልብህ ይጠራል።

195. **ሙቶሙቶ** ፡- የወርቅና የብር ማቅለጫ ጉድጓዳ ድንጋይ ነው፡ ይግላል እንጂ አይቀልጥም፡ በርሃ ድንጋይ እንደጀበታ አድርገህ ጠርበህ ለብረት ለወርቅ ለናስ ማቅለጫ ይሆንሃል።

196. **ማያ** ፡- የጠፋ ምንጭ የሚያመነጭ ነው፡ እሱ ባለበት ስፍራ በምድረ በዳ ቢሆን ውኃ አይጠፋም፡ መሬቱ አለምልሞ ታየውአለህ።

197. **መክስተ ልሳን ልምላክ** ፡- የሚባል የጋመ ብረት የመሰለ አለ፡ ከንጫቱ ከቦረቅ ከፈረፈር የምትበቅል አበባዋ ነጭ ሆና መስቀል የመሰለ አፀመስቀል ትባላለች፡ ከድንጋዩ ውስጥ ፈልፍለህ ከተህ ብትይዝና በጥበበ አእባን የተመዘገቡትንና ያልተመዘገቡ ሌሎች ድንጋዮችንም ታገኛቸው አለህ፡ ምስጢረ አእባንን የሚገልጥ ስለሆነ የድንጋዮች አለቃ ነው፡ በዚህ

የድንጋዮች ጥበብ ይገለጣል፡ ለሌላም ጉዳይ ይሆናልና ተፈላለፍበትና ፈላስፋ ሁንበት።

198. **አሜቴስጢናስ** ፡- ንጹህ የሆን መልኩ የወይን ጠጅ ወይም የዋርዶ ወፍ መልክ የአለው የእንቁ ድንጋይ ነው፡ ሲያስተውሉት ልብን የሚስብ የሚያስደስት ነው፡ በንጭ ወርቅ ላይ ፈርጥ አድርገህ በአንገትህ በእጅህ እሰረው፡ ባለዝና ትሆናለህ፡ ለሰው አታውለው ከሰው አንገት ላይ ቆይቶ ብታስረው እድሜህ ያጥራል፡ በዘመንህ ህመምተኛ ሆነህ ትኖራለህ፡ ቀናተኛ ድንጋይ ነው፡ በዚህ ብዙ የድንጋዮች ጥበብ አለ፡ ከአስተዋልከና ከመረመርከው የድንጋዩን ምስጢር ትገልጻለህ።

199. **ርካብ** ፡- ይህ ድንጋይ የጠፋን ነገር የሚያስገኝ ነው፡ ክብ ሆኖ ቀዳዳ አለው፡ በቀዳዳው በአውራ ጅማት አስረህ ያዝ የፈለከውን ታገኝአለህ።

200. **ርማህ** ፡- ይህ ድንጋይ ባለበት ትርፍ እንጂ ኪሳራ የለውም፡ ሲያዩት የሚያስደስት አረንጓዴ የመሰለ ነው፡ አልፎ አልፎ ነጭ አለው።

201. **ሩካብ** ፡- እሩካም ከበሐር አሸዋ መካከል ጠፍጣፋ ሆኖ ክብ ድንጋይ ነው፡ መልኩ ነጭ በረንቅ ነው፡ ጠንካራ ነው አይፈለጥም፡ ለፍቅር ስምህ ቀርፀህ በቤትህ ውስጥ አትረው ቤተሰብህ ይወዱሃል ያከብሩሃል ለሌላም እንዲሁ አድርግ።

202. **ሩካም** ፡- ከእብን በረድ የተሠራ የመቃብር ሣጥን በድንን የማያፈርስ ነጭ በረቅ ድንጋይ ነው፡ እሱ ባለበት የሞተ ነገር አይፈርስም፡ ፈጭተው በበድኑ ውስጥ ቢከቱበትና በድኑን በጥንቃቄ ቢያስቀምጡት ለብዙ መቶ አመታቶች አይፈርስም ይኖራል እንጂ አይበተንም፡ አንተም በየጊዜው ከቀን ወደቀን የጥበበ ዕንቁን መጽሐፍ አስተውለህ አንብ።

203. **ሪጆን** ፡- ለሠረገላ መሽከርከሪያ የሚሆን ድንጋይ ነው፡ ሲወቅሩት እንደደወል ይጮሃል፡ በድንጋይ ከለል እሳት ይቀልጣልና ለምትፈልገው ነገር በቀረጽከው ላይ አፍስሰውና ውኃ አፍስበት፡ ብረት ሆኖ ታገኘው አለህ።

204. **ረ[illegible]ህ / ሮሃ** ፡- እንደመዶሻ አድርጎ ዋሻ ቢወቅሩበት ድንጋይ ቢጠርቡበት እንቁ ቢነድሉበት የማይሰበር ድንጋይ ነው፡ ከመሬትና ከድንጋይ ላይ ቢያስቀምጡት ወደምድር ጥልቅ የሚገባ እብነአድማስ የሚባለውን ቢያስቀምጡበት እንዳይጠፋ ወይም እንዳይሰጥም ያደርገዋል፡ ይህ ድንጋይ እሳተ ገሞራ ባለበት አገር ይገኛል፡ ሉል ድንጋይ በሚገኝበት በዳሉልና በአፋር በአዜብ ምድር ይገኛል። በሮሃ መዶሻ ወይም መውቀጫ ብረትን አግለህ ስይፍና ጦር አድርገህ ብትቀጠቅጥበትና ብትስለው ስለቱ አይበርድም፡ ጦሩም አይታጠፍም።

ማንኛውም የእንቁ ድንጋይን ሁሉ ብትሞርድበት ብትወቅርበት እንደፈለከው ይሆንልሃል፡ ድንጋዮችን የሚያደቅና የሚፈጭ የድንጋዮች ንጉሥ ነው፡ በዚህ ብዙ ጥበብ አለ።

205. **ራህኤል** ፡ ቦግ እልም የሚል ብርሃን ይታይበታል፡ በቤትህ ውስጥ ብታስቀምጠው ከቤትህ በረከት አይጠፋም ትበለጽግአለህ።

206. **ሮሃኤል** ፡- አረንጓዴ ቀለም የአለው ሆኖ የእሳት ፍህም በሌሊት ይመስላል፡ እርሱን አድቀህና አልመህ የቤትህን ህንጻ ለቅልቀው፡ የደስታ ቤት ይሆንልሃል፡ ሲያዩት ውበት የአለው ቀለም ነውና።

207. **ሮቁ** ፡- ከመሬት ልብ ውስጥ የሚኖር ውኃና አፈር የማይጠጋው እሳት የሆነ ልምድድ ድንጋይ ነው፡ ይህ የድንጋይ ልምድድ በአለበት ቦታ እሳተ ገሞራ ይነሣበታል፡ አንዳንድ ግዜ ከመሬት ልብ ወደላይ ተተኩሶ ወይም ፈንድቶ ሲወጣ ለተወሰነ ጊዜ ከአለት ላይ ጥቁርና ቢጫ የመሰለ ሆኖ ታገኘውአለህ፡ በጽርስ ድንጋይ አጣብቀህ በአገርህ መሃል ብታስቀምጠው ረሃብ አይሆንም።

208. **ቆሬ** ፦ አራት ማእዘን የለሰው ሆኖ ሲወቅሩት ውስጡ ነጭ አረንጓዴ የለሰው ነው፤ የኔን ነገር አሳየኝ "ቶላዱራኢል፤ አዮን፤ አዮና አዮኖ አልሙተከቢር ኡራ ኡራኢል ቂታኢል ኸቢር አልኸቢር ለእገሌ" ብለህ ጻፍበትና አየጸለይክ ተንተርሰህ ተኛ፤ የአሰብከውን በራእይ ያሳይሃል፤ እንዳትረሣው በመጽሐፍ የአየኸውን ራእይ ጽፈህ አኑረው፤ መጭውን ሁሉ ማወቅና ትንቢት መናገር ትችላለህ፤ የእገሌን ነገር አሳየኝ ብለህ ብተኛ በህልምህ ስለሁኔታው ያሳይሃል።

209. **ቆደሬጀ** ፦ ለብረት የሚሆን አፈር ነው፤ መልኩ የዋልካ አፈር ጥቁር ይመስላል፤ በእሳት አግለህ በመዶሻ ውቀጠው፤ ብረት ይሆንልሃል፤ የብረት ድንጋይ አፈር ነው።

210. **ቆርር** ፦ ለጦርና ለቀስት የሚሆን የብረት ድንጋይ ነው፤ ሰው የደደረው ወይም የአቆመው ይመስላል፤ መልኩ ጥቁር ሻሮ ነው።

211. **ርሖ** ፦ የድንጋይ እጣን የሚያወጣ ለሽቶ የሚዘጋጅና የሚነጥር ድንጋይ ነው፤ ርሖ ባለበት ብዙ ልዩ ልዩ የሆነ አለ።

212. **ርእዮተ እብን** ፦ የተጣበቁ መንቶች ድንጋዮች እንዚህን ይዘህ የእንቁ ድንጋይን ብትፈልግ ታገኛለህ፡ መክሰት ናቸው፡ ነጣጥለህ ብትተዋቸው በሌላ ቀን ተጣብቀው ታገኛቸው አለህ፡፡

213. **ሐረር**፦ መብረቅ የመታው ድንጋይ ወይም መብረቅ የወደቀበት አፈር ላይ እንደድንጋይ ሆኖ የሚገኝ ነው፡ በቤትህ በደጃፍህ አትረው እንዲሁ በቅጽርህ በር አፍ የሚቀስፍ መንፈስ አይገባም፡ ይጠብቃል፡ መልኩ መብረቅ የወደቀበትን አፈር መስሉ ይታያል፡ ታውቀው አለህ፡፡

214. **ረርዋ** ፦ ርሳስ አረር የሚሆን በቀላሉ በእሳት የሚቀልጥ ከባድ የሆነ ነው፡፡

215. **ሬስን** ፦ በቀላሉ የሚግም ግለት የሚስብ ድንጋይ ነው፡ ሰጥፋት የሚውል ድንጋይ ነው፡፡

216. **ሩሬ** ፦ እንደቀለበት ክብ የሆነና ቀዳዳ የአላቸው ድንጋዮች ለመካን ሴት እሰርላት ትወልዳለች፡ ለከብቶችህ ባአንገታቸው እሰርላቸው፡ ይረቡልሃል፡ ከመቁጠሪያህ ጋር እሰረውና የፈለከውን ነገር ከጸሎትህ በኋላ ተናገር ይፈጸምልሃል እንደማርዳ ትናንሽ ናቸው፡፡

217. ሩቢሬ፡- እንደኩብት የቀለለ ሆኖ ወደባህር ብትጥለው ይንሳፈፋል፡ በሮሃ ድንጋይ ወቅጠህ የጦር ልብስህን በማጣበቂያ እያጠበክ ብታሲዘውና ለብሰህ ጦር ብትሄድ ጦሩን ይመልሳል፤ በጉማሬ ቆዳ ላይ እንደፋጋና እንደጋሻ አድርገህ ብትይዝ ሰይፉን ይሰብራል፡ ለመርከብ በዚፍት እየለወስክ ብትመርገው ብታጣብቀው መርከቡ ይንሳፈፋል እንጂ አይሰጥምም፡ በአዋሽ ሸለቆ በአፋር አገር ታገኘው አለህ፤ ሩቢሬ የተባለው ድንጋይ እንደኖህያ ቀላል ሆኖ ኩብት ቢመስል ያሰሮሃ ድንጋይ አይወቀጥም፡ ልሰብረው ብትልም አይሰበርም ጠንካራ ድንጋይ ነው፤ የድንጋዮች ጥበብ ታውቀ ከበረ።።

218. ርር ፡- ገበታ የመሰለ ምግብ ያጡ ወፎች በየጊዜው እየሄዱ ይወቅሩታል፡ ወዲያው ይሾሉ ወፎች አሞራዎች እሱ ካሰበት አይጠፉም፡ በየተራ እየሄዱ በአፋቸው ይነኩታል፡ የዚህን ድንጋይ ሺራፊ በአንገትህ በኪስህ ብትይዝ ሰው የአዝንልሃል፡ ሁሉም ሰው ርህሩህ ይሉሃል፡ ሳትበላ ሳትጠጣ አታድርም፡ አገሩን አዙረህ ብትቀብረው በአዞርክበት አገር የሚኖሩ ሰዎች አይራቡም ሁልጊዜ ደስተኞች ይሆናሉ፡ በዚህ የድንጋይ ጸጋ እግዚአብሔር ታውቀ ከበረ።።

219. **ሮንያ** :- መናፍስት የማይለዩት ትልቅ ቋጥኝ ድንጋይ ቅቤ የቀለጠበት ደም የፈሰሰበት ይመስላል፡ ይህ ድንጋይ በአለበት የሚገኙ የቅልሞሽ ድንጋዮች የመሰሉ ብዙ የተለያዩ ድንጋዮች ታገኝ አለህ፡ ሶስት/ሰባት ወይም አሥራ ሁለት ድንጋዮች ይዘህ መናፍስት ብትጠራ ይታዘዙሃል፡ መከስተ መናፍስት ነው፡ በንጽህና ያዘው እንዲያስቀስፍህ።

220. **ረሺ** :- የሰው ራስ ቅል የመሰለ ድንጋይ አለ፡ እንደፋጋ አድርገህ መድኃኒት ብትጠጣበት ይለምርልሃል፡ ለታመመ ሰው በእሱ ውኃ አሳድረህ ግማሹን አጠጣው፡ የተረፈውን ሰውነቱን ይታጠብበት፡ ይፈወሳል፡ እርሱ በአለበት የመነጨ ውኃ ይፈውሳል፡ ፀበል ይሆናል፡ ለከብቶችህም እንዲሁ ውኃ አጠጣበት።

221. **ሮስ** :- በጣም የጠቆረ ሆኖ የአበባ ቅርፅ የአለው ድንጋይ ነው፡ እርሱን ይዘህ ብትሄድ የጠላኸውና የጠላህ ሰው ጋር አያገናኝም፡ ይሰውርሃል የሰው ቅርጽ ያለው ዲያን የሚባል ጥቁር ድንጋይ አለ፡ ከእርሱ ጋር ይዘህ ክፉ መናፍስትን ብትጠራ ይመጡልሃል ያልካቸውን ይፈጽሙልሃል፡ ነገር ግን በመጨረሻ አሰቃይተው ይገድሉሃልና፡ እንዲህ ካለ ክፉ ነገር እራቅ አታድርግ፡ ይቅርብህ መልካሙንና መጥፎን ለመምረጥና ለማድረግ ምርጫው የአንተ ነው፡ የድንጋይ ጥበብ ነው።

222. **አርሆ - አርዞ** :- እሳተ ገሞራ ወይም ሰሐራ በሆነና አሸዋ በተከመረበት ምድረ በዳ የሚገኝ መልኩ አረንጓዴ ቢጫ ድንጋይ ነው፣ ይህ ድንጋይ ባለበት ከምድር ልብ ወደላይ የሚገነፍሊ ሰማዮት የማይቻል ሬን ይወጣል፣ ወላፈኑ በወጣ ጊዜ ብረትም ይሁን አጥንት ወይም እንጨት እንስሳም ይሁን ሰው እንደሰም የአቀልጠዋል፣ ከድቡሽት ጋር ይቀላቅለዋል፡፡ ስለዚህ ተጠንቅቀህ ፈልግ በአገኘሸው ጊዜ እርሱን ይዘህና ታቅፈህ በአንተ ላይ ወላፈኑ አይነካህምና ወስደህ በክብር ከቤትህ አስቀምጠው ከምትፈራው ሁሉ ይሰውርሃል፣ ከውኃ ውስጥ አሳድረህ ውኃውን ጧት ጧት ጠጣ ሰውነትህ ይታደሳል፡፡

223. **ሱዐ** :- የከበረና የተወደደ የእንቁ ድንጋይ ነው፣ በዳሉል በአፋር እሳተ ገሞራ በአለበት ይገኛል፣ መልኩ አረንጓዴ ቢጫ ወርቅ ይመስላል፣ ለቤተ መንግሥት ይሆናል፣ ነገር ግን ለአንገት ጌጥ ቢያደርጉት ቢያስሩት ዘር ያጠፋል፣ በክቡር ቦታ አስቀምጠው እንጂ አትሰረው፣ አታጊጥበት፣ በመንበርህ ፊት ለፊት አስቀምጠው መግረሬፀር ይሆናል፡፡

224. **ሱዘ** :- ሰሌዳ የመሰለ ድንጋይ ነው፣ በእርሱ ላይ ክብ ስምህን ጻፍበትና በአደባባይ ቅበረው ተሰሚና ታዋቂ ትሆናለህ፣ የአገርህ ህዝብ ይወድሃል፣ የአልከውን ሁሉ ይፈጽምልሃል፣ በዚህ ብዙ ጥበብ አለ፡፡

225. **ቆሽሌ** ፡- በሰገነት ላይ የሚቀመጥ የድንጋይ ወንበር ነው፣ ይህ ድንጋይ የእግዚአብሔር ድንጋይ ሰማሰት እባንኤል ልኡል ወይም ሉአሌ ይባላል፡ ኢትኤል በማዮን ዳርቻ ነገሥታት ሲነግሡ እንዲቀመጡበትና ቅባአ መንግሥት ተቀብተው እንዲነግሱበት ሲል አቀምጦታል፡ እንዲሁ ከእሱ ላይ ሆነህ ተቀባ።

226. **ቆጼቅ** ፡- አንድ የሚያደርግ ድንጋይ ነው፡ መልኩ ቀይ ሥጋ ይመስላል፡ መገኛው ከድንጋይ ስር ነው፡ ይህን የድንጋይ አፈር አድቀህ ደቁሰህ እንደጭቃ ለውሰህ ማገኛውን ድንጋይ ወቅረህ እንደህንጻ ስራው፡ በሌላ ጊዜ አንድ ድንጋይ ሆኖ ታገኘውአለህ፡ የድንጋይ ሐውልት ያደርግልሃል፡ እብነ መስተሳልም ነው፡ የድንጋዮችና የዕንቁ ጥበብ በዚህ አለ፡ ለሌላ ጉዳይ ተፈላሰፍበት።

227. **ባፀ** ፡- ወይም ልበ ንጉሥ የሚባል ድንጋይ ከበሐር አሸዋ መካከል ታገኘው አለህ፡ የጠቁት እንደሆነ እንደብረት ይጮሃል፡ ማእዘን የሌለው ድቡልቡል ነው፡ መልኩ ቢጫም ነጭም እንቁላል የመሰለ ነው፡ በድምጹ ታውቀው አለህ፡ እርሱን በልብህ ላይ አድርገህ እግዚአብሔርን ጠይቅ መልስ ታገኛለህ፡ የተመኘኸውን ይሰጥሃል፡ የተሳልከው ሁሉ ይፈጸማል፡ መፍትሔ ሐብት ወመክስተ ምስጢራት ነው፡ በዚህ የድንጋዮችና የዕንቁ ጥበብ ከበረ።

228. **ዓቁ** ፦ እብንሕይወት የሚባል መልኩ ሁልጊዜ ዘይት ወይም ውኃ የፈሰሰበት ይመስላል፡ በጣም ከቡርና ምርጥ ድንጋይ ነው፡ እርሱን በሮሃ ድንጋይ ፈልፍለህ እንደዋንጫ አድርገህ በእሱ ውስጥ ውኃ እያሳደርክ የጠጣህ እንደሆነ ሰውነትህ ይታደሳል፡ እድሜህ ይረዝማል፡ እርሱ በሚኖርበት ነፍስና ሥጋ አይለያዩም፡ ሕያኢልና እንቆሐይና በተባሉ የእንቁ ድንጋዮች ላይ በክብር አስቀምጠው ድንጋዮች እንቁላል ይመስላሉ፡ ድኩላ ወይም አጋዘን እንዲሁም ሌሎች እንስሳት መገጮ የተባለው የጨው አፈር ሲልሱና ሲግጡ በሆዳቸው ውስጥ የሚያድግ እንቆሐይና ወይም ሕያኢል ይባላል፡ የላሉ መቀመጫ አድርገው ይህን ድንጋይ ለአምስት መቶ አመት በላይ የተጠቀመበት ሰንደቅ አላማ የተባለ አፄ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት ነበር፡ እንዲሁ ብዙ መናንያን ባህታዊዎች ለብዙ አመታት እድሜ እንዲሆናቸው ተጠቅመውበታል፡ አንተም እንዲሁ እንደሱ ተጠቀምበት የእድሜ ድንጋይ ነው።

229. **ሔሉ** ፦ ከምድር ልብ ውስጥ የሚወጣና ልምድድ የሆነና እሳት መስሉ እንደውኃ ይፈሳል፡ ድንገት ሮሃ ከተባለው ድንጋይ ላይ ተቆቶ ታገኘው አለህ በጥንቃቄ እስከድንጋዩ አንስተህ እንደቆጥ አልጋ ሰርተህ በበላዩ ላይ ማንኛውን ብያ ድንጋይ የከመርክበት እንደሆነ እንደሰም ቀልጦ አንድ ሆኖ ከስሩ ታገኘው አለህ።

230. **ባሺ** ፡- እንደጣዝማ ሰፊፍ ጡት የአለው ነው፡ እርሱን ከቀፎ ውስጥ የአደረከው እንደሆነ ንብህ ማር ይሰራል፡ እሱ ባለበት ዋሻ ንብ አይጠፋም፡ ምህሳበ ንብ ነው።

231. **ሷንር** ፡- ሐመልማለ ወርቅ ይባላል፡ ይህ ወርቅ እንደቅጠል እንደወረቀት ቢያሳሱት የሚሳሳ ቢጫ ወርቅ ነው፡ በቆዳ ወይም በልብስ ላይ ቢጠልፉት ተሰጥፎ ይኖራል፡ ለተለጠፈበት ሁሉ የክብር ጌጥ ይሆናል፡ ከቆዳ ከልብስ ከመሰሰህ ጌጥ ጋር አቅልጠህ ብትነከረው ተዋህዶ ይቀራል።

232. **ጺዋጺዋ** ፡- እንደወርቅ ቢጫ የሆነና አረንጓዴ ቀይ ድንጋይ ነው፡ በእሳት ውስጥ ስትከተው ይፈነዳል፡ ይበታተናል፡ ለሐረር /አረር/ ብታዘጋጀው ይሆናል፡ እራስከን እንዳይጐዳህ ተጠንቅቀህ አድርግ፡ ያለመጠንቀቅ እንዳትሞክር።

233. **ጺዩድ** - ጥቁር ድንጋይ ነው፡ መርዘኛ ነው፡ እርሱ ባለበት የበቀለን አታክልት የፈለቀን ውኃ አትጠጣ፡ መርዘኛ አቁስሉና እመንምኖ የሚገል መርዝ አለው፡ እርሱ እንቅፋት የመታው ሰው ቁስሉ አይድንም፡ እንደብረት ድንጋይ አግለህ ጦር ቢለዋ ብትሰራው ይሰራል፡ ነገር ግን በእርሱ የተወጋ አይድንምና በቢላዋው የእንስሳ ስጋ ቆርጠህ አትብላበት፡ መርዘኛ ነው፡ ለጥፋት ብቻ የሚሆን ድንጋይ ነው።

234. **ዷዩዷ** ፡- ይህ የድንጋይ ከሰል በማቃጠያ የሚቃጠል ሲሆን እሱን የሚመስልና የማይቃጠል ጥቁር ድንጋይ ከድንጋዩ ከሰል መሐል ታገኘው አለህ፡ በሌሎች መርዘኛ ድንጋይ የታመመን ሰው ብታሸበት ወይም በውኃ እያጠበክ ብትቀባውና ብታጠጣው ይፈወሳል ይድናልም፡፡

235. **ዱበ** ፡- ሻፎ ድንጋይ ስለት የሚወጣው ለሥጋና ለፈለከው ሁሉ መቁረጫና መክተፊያ የሚሆን ነው፡ ከዚህ ድንጋይ የተሠራ ብረት ስለቱ አይበርድም፡ አይዶለዱምም፡፡

236. **ደደ** ፡- በተጋጨ ቁጥር እሳት የሚያወጣ ድንጋይ ነው፡ ይህን ድንጋይ ደቁሰህ እንክብልል አድርገህ በተሽከርካሪ መልክ ሁለት ሁለቱን አገናኝተህ ብታጋጨው እንደ ነጐድ ይፈጥርልሃል፡ ለኃይል ማመንጫ ይሆንሃል፡፡

237. **ዶዶ** ፡- እንደ መዝጊያ የመሰለ ድንጋይ አለ ስትሰብረው ጽሁፍ የመሰለ ጭረት ታያለህ እሱን አስመስለህ በሰሌዳ ላይ ጽፈህ ከእሱ ላይ ሆነህ አጥበህ ጠጣው፡ የአሰብከው ይፈጸማል፡ በጅረትና ድንጋያማ በሆነ ወንዝ ዳር ታገኘው አለህ፡ የበር ደጃፍ በመምሰሉ ትለየው አለህ፡ ለአእምሮህ ብርሃን ይሆናል፡፡

238. **ዲሐም ተምሪድ** :- የሚባል ከፉ ቀይ ድንጋይ አለ፡ እሄን ድንጋይ በጉታ ብታደርገው እህል ይበረክታል፡ በቀፎ ብታደርገው ንብ ማር ይሰራል፡ ዱሐም በአለበት ቤት ሐብት አይጠፋም፡ ምሕሳበ ንዋይ ይሆንልሃል።

239. **ዲን** :- መልኩ ቢጫና አረንጓዴ ቢጫ የሆነ ከፈረፈርና ከበረሃ የሚገኝ የድንጋይ አፈር ነው፡ በእሳት ውስጥ ሲከቱት ተቃጣይ ቀላጭና ፈሳሽ እሳት ነው፡ ወደውኃ ውስጥ ፈሳሹን ሲከቱት ድቃቃ ድብልብል ይሆናል፡ ለድንጋይ ከሰል ማያያዣ ቀልጠ ለሚረጋ ወይም ፈሳሽ ለሆነ ነገር እንዲረጋና ብትን እንዲሆን ያደርጋል፡ አረንጓዴ የሆነው መርዘኛ ነውና ሲቃጠል ለዓይን አደጋ ያመጣል ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡ ዲን በሚኘበት አካባቢ ባሩድና የባሩድ ጭቃ ይገኛል፡ በዚህ የሐራራ መስሪያ ወይም የጥበብ ምስጢር አለ።

240. **ደዲሐ** :- የሚባል መልኩ የወርቅን አፈር የመሰለ ነገር ግን የሚወቀጥና የሚደቅ ነው፡ ጥሩ ወርቅ ይመስላል፡ ብረቱን ናሱን ወርቅ ለማስመሰል በጋን ውስጥ ሁሉንም ከተህ በውኃ በጥብጠውና ጋኑን ሙላው አሽገውም፡ ጢሱ እንዳይወጣ ዙሪያውን እሳት አንድድበትና በሌላ ቀን አውጣው፡ ወርቅ መስሎ ታገኘው አለህ፡ ለወርቅ ቀለም ከቀይ አፈር ጋር አቡክተህ ቀቅለውና እንዲረጋ አድርገው፡ ለቀለም የሚሆነው ንጥር በበላዩ ተለይቶ ታገኘው አለህና እንደመሰለህ አንጥረህ

ተጠቀም የሰውነትን ቆዳ ለማደስና ለማሳመር የተነጠረውን ንጥር የገላህን ቆዳ ደፍድፈህ ሙቀት ካለው ወይም እንፋሎት ካለው ጉድጓድ ውስጥ ገብተህ ቆይ፡ በየእመቱ እንደዚሁ አድርግ መልክህ ያምራል፡ ከውበት ላይ ውበት ይሆንልሃል፡ በዚህ የድንጋዮች ጥበብ ይከብራል።

241. **ጺጣ** ፡- ለጥንቆልና የሚጠቀሙባቸው ድቡልቡል ድንጋዮች ወይም ከዛጉል ቅርፍት ጋር የሚያጋጯቸውና በትነው የሚያዩዋቸው ሲደራረቡ መልካም ሲበተኑ መጥፎ አተባለ ይመለከባቸዋልና ዛጉል ከሚጥሉ አፈር ከሚያጉደጉድ ጠንቅዋዮች ጋር አትዋል፡ ጠቢብ ለመሆን ከፈለክ አስተውለህ መመርመርና በመፈላሰፍ ጽና እንጂ ሰውን ለማታለል አታስብ፡ በእውነት ጽና።

242. **ጠሚ** ፡- በክረምት ወራት እንደ አረንጓዴና እንደ ጠጉር የመሰለ የሚያበቅል ሲደርቅ የሪዝ ጠጉር የሚመስል ከድንጋይ ላይ የሚበቅል አለ፡ እርሱን ወቅጠህ ከቁስልህ ላይ ደምድመው ከፈወሰህና እርሱ መሆኑን ካረጋገጥክ ጠጣው፡ የውስጥን ይፈውሳል።

243. **ጡንያ** ፡- ጉንዳን የሚከበው ጥቁር ድንጋይ ነው፡ ይህን ድንጋይ ሸርፈህ ለቤተሰብህ ሁሉ እሰርላቸው፡ ከመካከላችሁ አንዱ ቢጠፋ ጠላት ቢማርከው ወይም ቢከበልል ተመልሶ ይመጣል። በአንዱ የደረሰው ደስታም ይሁን ችግር

ሌላው ቤተሰብ ይሰማዋል፡ የልብ ማግኔት የሆነ ድንጋይ ነው፡ ለሌላም ይሆናልና አስተውለህ መርምር የድንጋዮችና የ... ጥበብ ስለዚህ ድንጋይ ከበረ፡፡

244. **ተርሴስ** ፡- እንደመስታዋት የጠራ የእንቁ ድንጋይ መገኛው በባህር ዳር ነው፡ ሰብረህ በቤሖር ውስጥ በእሳ በቆርቫናት ዛጉል ቅርፍት ውስጥ አድርገህ ብትተውና በአሙቱ የማጉሉን ቅርፍት ከፍተህ ብታየው እንደቅልምሽ ሆኖ ጠርቶ ታገኘው አለህ፡ ለፈርጥ ጌጥ ይሆንሃል፡ ለመቁጠሪያም እንዲሁ ይሆናል፡፡

245. **ተንካሬ** ፡- ቶጳዝዮን እንቶጳዝዮን እንቁዮጵያ ይባላል፡ መልኩ አረንጓዴና ቢጫ ነው፡ ይህ የእንቁ ድንጋይ ግዮን በሚፈስበት ምድር ይገኛል፡ ከእርሱም ጋር ሰማያዊና ነጭ ድንጋይ ይገኛል፡ ከነሱ ውስጥም ተጣብቆ ታገኘው አለህ፡ በጣም ክቡር የሆነ ድንጋይ ነው፡፡

በመሰለህ ነገር አስመስለህ ቀርፀህ በምትቀመጥበት በምታድርበት ክፍል አስቀምጠው የአስከብርሃል የክብር ድንጋይ ነው፡፡

246. **ኢትዮጵ** ፡- ለስጦታ የተዘጋጀ ንጹሕ ቢጫ ወርቅ ኢትኤል ከእግዚአብሔር ጸጋ የተገኘ ለእግዚአብሔር የቀረበ ጋሻ ገጸበረከት ነው፡ ይህ ወርቅ ግዮን በሚፈስባቸው ምድሮች የሚገኝ ነው፡ የኮከብ ስእል አድርገህ በበራሪ ደም በዶር ደም

አንግስህ በደረትህ የአደረከው እንደሆን የሰው ፍቅር ይሆንሃል፡ በእጅህ ሐብት አታጣም፡ በቀይ በግ ደም ሰውስህ በፀሐይ አውስህ የአሰርከው እንደሆነ ግርማ ሞገስ ይሆንሃል፡ በስስት ደም ቆልተህ እንደቀሰበት አድርገህ ካደረከው የፈለከው አያመልጥህም፡ ለሲሳይ ይሆንሃል፡ የተመኘኸውን ሁሉ ታገኛለህ፡ ይሆንልሃል፡ መፍትሔ ሐብት ነው።

247. **ታቱ** ፡- የተለያዩ ቀለሞች የአሉት የእንቁ ድንጋይ እንደ መረጥከው የእንስሳ ወይም የአውሬ መልክ አስመስለህ ቀርፀህ በግቢህ የቀበርከው እንደሆን ሌባ ቤትህን አይደፍረውም፡ ቢወስድም መልሶ ይጥለዋል፡ ወይም ይያዛል ማእሰረሰብእ ነው።

248. **ሐቶ** ፡- ቀይ ሆኖ የጠራና የማይጫር የእንቁ ድንጋይ ነው፡ በዘንግህ ጫፍ አድርገህ የያዝከ እንደሆነ የሚደፍርህ የለም፡ ከተሾምክ አትሻርም፡ መግዝአ ሰብእ ነው።

249. **ቴታ** ፡- ቀንጫጭ ወይም የተለያዩ ህዋሳት የሚከቡት ባለጺጋ ድንጋይ ነው፡ ይህን በወርቅ ለብጠህ የአሰርከ እንደሆነ የታወቅህ ባለዝና ትሆናለህ፡ ተከታይህና ደጋፊህ ይበዛል፡ ከደረትህ ላይ ሁልጊዜ አትለየው አድርገው።

250. **ቶቃሺ** ፡- እንደብረት መስሎ የተጠመዘዘ ድንጋይ ነው፤ እርሱን ለፈለከው እንስሳ ለፈርስ ለበቅሎ በእግሩ አሰርለት፡ ፈጣን ይሆንልሃል፡ የከሣ የአወፍሯል።

251. **ቶም** ፡- መልኩ በሬንጅ መስሎ ብልጭልጭ ይበዛዋል መሐሉ ከፍት ቀዳዳ ነው፡ ይህን ድንጋይ በክብር ልብስ አልብሶ በሚፀልዩበት ቦታ ቢያስቀምጡት መክስተ ራእይ ወመፍትሔ ሐብት ይሆናል፡ በቤት በረከት ይሞላል።

251. **ቱም** ፡- ሥርጋዊ ህብር የሆነና የተሸላለመ ነጸብራቅ የአሰው የእንቁ ድንጋይ ነው። አስቀርጸህ በአንገትህ በክንድህ የአደረከው እንደሆነ ግርማ ሞገስ ምስሐበ ሰብእ ይሆንሃል፡ ለሰው አሳልፈህ አትስጠው አታውሰውም፡ ሐብት እንደኝ እንዳይከዳህ ከዘርህ እጅ አይውጣ።

253. **ቅሶንይ ሙራሂ** ፡- የሚያበራ ድንጋይ የጨረቃ ስባሪ የሚሉት ግማሽ ጨረቃ የመሰለ ነው፡ ቤት ስትሠራ ከቤትህ ቋንጮ ላይ ወይም ከድምድሙ ውስጥ አድርገው ሐብት ከበረከት ፍቅር ከሰላም አድሜ ከጤና ጋር ይሆንልሃል። መከራና ሥቃይ በቤትህ ውስጥ አይታይም።

254. **ቅሱ** ፡- ጉድጓዳ የልብስ ማጠቢያ ገበታ የመሰለ ውኃ ሞልተህ አሳድረህ ታጠብበት ከህመምህ ትፈወሳለህ፡ የታመሙ ወፎች መጥተው ከእሱ በተቋተው ውኃ ሲታጠቡ

ይፈወሳሉ፣ ይወልዳሉ፣ ይህ ድንጋይ በአሰበት የፈሰቀ ምንጭ ሁሉ ፈዋሽ ጸበል ይሆናልና ከፈለከው ምንጭ ራስ ላይ ቅበረው ገቢታ ወይም ዳካ በመምሰሉ ታውቀዋለህ።

255. **ስዙዌ** ፡- ለእንጨት መቁረጫ የተሳለ የመሰለ ሻፎ ድንጋይ ሲሆን ምስሐል ለስላሣ ልዝብ መሳያ ድንጋይ ነው፣ በማንኛውም ጅረትና ሸንተረር ታገኘውአለህ ለሰይፍ ለቢለዋ በእሳት እያጋልክና እያጋምክ በመዶሻ ደብድበው ስለት ያለው ብረት ይሆንልሃል ወይም አቅልጠው።

256. **ሶረሶር** ፡- የጀርባ አጥንት የመሰለ ድንጋይ እባጭ ለወጣበት በእሱ **እግለህ** ተኩሰው ይፈነዳል፣ ይፈወሳል፣ በከርቤ ውኃ አጠበውና ገራም ጡንጅት ቅጠል ወቅጠህ አሰርለት።

257. **ስሬሲርት** ፡- የተቀጣጠለ ባለአርከን ድንጋይ ሁሉን አንድ በአንድ ብታየው የዛፍ ቅጠል የትል ስእል የተለያዩ ፍጥረቶች ቅርጽ ታገኛለህ፣ የድንጋዩን እድሜ ለመመርመርና ለማወቅ ለመቁጠርም ከረምቱን አሳልፎ በየአመቱ አንድ መስመር ይጨምራልና በማጉያ መነጽር እያየህ ከሽረሪት ማግ የቀጠኑትን መስመሮች ከመሐል ጀምረህ ቁጠራቸው እድሜውን ታውቀዋለህ በመስመሩ ልክ ነውና።

258. **ሰርዲኖን** ፡- ሰማያዊ ነጭ እንቁ ድንጋይ ከአለት ዋሻ ውስጥ የሚገኝ ነው፡ እንደወርቅ ይቀልጣል፡ ለኮከብ ለመስቀል ለመስለህ ቅርፅ ይሆናል፡ ለአይን መልኩና ጥራቱ ያማረ ነው፡ ይህ ድንጋይ ባለበት ሰማያዊ እብነበረድ አለ።

259. **ሰርዶዮን** ፡- ቀይ ደም የመሰለ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ በአንገት አዘውትረው ቢያስሩት ከነስር ከደም ብዛት ይጠብቃል፡ ያድናል፡ እንደጌጥ አሰርተህ ያዘው ለፈርጥ ይሆናል፡ ከቀን ወደቀን የመልኩ ቀለም ያምራል።

260. **ሰራዶዮን** ፡- ሩቢ የእንቁ ድንጋይ መልኩ አረንጓዴ ሰማያዊ ነጭ ቀይ እንደመስታዋት የጠራ ነው ለዘውድ ለአክሊል ይሆናል በወርቅ እየለበጥክ ስራው ያምራል።

261. **ስቁር** ፡- ቀዳዳ የበዛበት ድንጋይ ነው፡ መልኩ ቡላ ጥቁር ሆኖ ከርችፍችፍ ያለ ነው፡ በደጃፍ በአጥርህ ስቀለው ክፉ ነገር ትድናለህ።

262. **ስኑን** ፡- ጥርስ የመሰለ የእንቁ ድንጋይ፡ ይህን ድንጋይ እንደጥርስ ሞርደህ ጥርሱ ለወለቀ ብትገጥምለትና ብትተክለው ጥርስ መስሎ ከድዱ ጋር ይጣበቃል፡ መልኩ በጣም ነጭ ነው።

263. **ሰንቃጭ** ፡- እንደብረት ሲመቱት የሚጮህ ድንጋይ ነው፡ በእሳት አቅልጠህ ለደወል ለቃጭል ብታደርገው የደወል ብረት ይሆንልሃል።

264. **ሰንኮሬስ** ፡- ከሰው ጋር የሚያዋድድና የሚያስታርቅ ድንጋይ ነው፡ በደጋ አገር በረዶ በሚበዛበት ይገኛል፡ መልኩ ቀይ ሆኖ ዘይት የፈሰሰበት ይመስላል፡ ሲያዩት በጣም ደስ ይላል፡ የተጣሉትን ሰዎች አስተቃቅፈህ ብታሻቸውና ብትዳብሳቸው በፍቅር አይለያዩም።

265. **ሰንደቅ** ፡- ቀጥ ያለ ድንጋይ ባለማእዘን ውጋግራ የመሰለ ነው፡ የጥንት ሰዎች ተክለውት ታገኛለህ፡ ጠላት እንዳያቸንፍህ እንደወንድ ብልት አስመስለህ ስምህን ጻፍበትና ትክለው በስሩም ሽናበትና ወደዘመቻ ሂድ ታሸንፍአለህ።

266. **ሰንፔር** ፡- እሳት የማያግለው የማይሰበር ክቡር የእንቁ ድንጋይ ነው፡ መልኩ እንደፍህም ቀይ ነው፡ የጋለ ይመስላል፡ በቢጫ ወርቅ ለብጠህ ብታስረው ትከበር አለህ፡ ሕዝብ ይወድሐል፡ በነጭ ወርቅ እንዲሁ አድርግ፡ ትንቢተ ኢሳ. 54 "አንቺ የተቸገርሽ በአውሎ ነፋስም የተናወጥሽ ያልተጽናናሽም እነሆ ድንጋዮችሽን ሸላልሜ እገነባለሁ፡ በሰንፔርም እመሠርትሽ አለሁ፡ የማንበሽንም ጉልላት በቀይ እንቁ በሮችሽንም በሚያብረቀርቅ ዕንቁ ዳርቻሽንም ሁሉ በከበሩ ድንጋዮች እሠራለሁ።

267. **ሰኮናን** :- እግርን ያዝ የሚያደርግ ድንጋይ ነው፤
ጠፍጣፋ ሆኖ ግማደ መስቀል የመሰለ አሰው፡ መልኩ በጣም ቀይ ነው፡ በቤትህ ወይም በቤተ መቅደስ ወይም በገበያ መሃል ሶስት ግዜ አዙረህ ብትቀብረው ምሕሳበ ሰብእ ይሆናል። የህዝብ መሰብሰቢያና መናሃሪያ ይሆናል፡ ቀይ መልኩ ያዝ ሲያደርግ ሌላው ደግሞ ከተጣበቀና ከአጠበቀ ውሃ ካላፈሰሱበት አይለቅም። መናገዘዘ ሰብእ ይባላል ይህ ለማእሰር ነው፡ በዚህ ድንጋይ ጥበብ አሰ፡ በቤትህ ጉልላት ላይ አድርገው፡ በሐውልት ራስ ላይ ስቀለው።

268. **ሰደሬ** :- ሻሮ ድንጋይ ነው፡ ስእለት አለው "ሲፓራ ሚስቱ ባልጩት ወሰደች የልጆችዋንም ሸለፈት ገረዘች ወደ ሙሴ እግርም ጣለችው፡- አንተ ለእኔ የደም ሙሽራ ነህ አለች። ዘጸአት ፡ 4÷25"

269. **ሲሩደ** :- ብዙ ቀለም የአለው ድንጋይ ነው፤ በክረምት ወይም በበጋ መልኩ ተቀይሮ ታየው አለህ፡ ይህን ድንጋይ በቤትህ ፊት ለፊት ቅበረው፡ ወይም በበርህ ደጃፍ ቅበረው እንግዳ ሰው ወይም ሰላይ ቢመጣ የሚያደርገውን ሁሉ ይነግርሃል።

270. **ሶሬ** :- ዝጉርጉር ድንጋይ ይህ ድንጋይ በአሰበት የምድሩ አፈር ቀያቴ ቢጫ ይመስላል፡ ፈልገህ ሶራን ድንጋይ ልታገኝ ቤተመቅደስን ስትሰራ ወይም ቤትህን አብረህ ከህንጻው ጋር ስራው ውበት ይሰጠዋል።

271. **ሶርዮን** ፡- ውድ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ የተለያየ ቀለም አለው ሶራና ሲሩይ ከተባሉት ድንጋዮች ውስጥ ታገኘው አለህና ለጥበብ ያዘው፡፡

272. **ጽቤ** ፡- ለጽላት ለሴዳና ለታቦት ዝብታ የሚሆንና የሚጠረብ የእለት ድንጋይ መልኩ ነጭም ቡላም አለ፡ ለፈለከው ነገር በቀላሉ እንደ እንጨት የሚጠረብ ነው፡፡ እንደ ሳጥን አድርገህ መጻሕፍትን አልባሳትን በውስጡ አስቀምጥ ብል አይበላውም፡፡

273. **ፀዳስ** ፡- ወርህ የሚባል ማጭድ ይመስላል፡ ለታመመ ሰው ይሹበት ወይም ከእመመው ላይ በእሳት እያሞቁ ማሸት ነው ይፈወሳል፡ ከምታት ከምች ይጠብቃል፡፡

274. **ኡይዳ** ፡- የጦጣ ጭቃ የመሰለ መልኩ የነጣ ቦረቅ ድንጋይ የማይደርቅ በመሆኑ ታውቀው አለህና ሲባጉውን በኡይዳ አሽገህ በስንጥቅ እለት ውስጥ ከተህ ጫቱን ብታቃጥለው እለቱን ፈንድቶ ይበታትነዋል፡ ለእለት ድንጋይ መፈርቨሻ ይሆንሃል፡ አስተውለህ ተፈላለፍበት ለፈለከው ጉዳይ ያግዝሃል፡፡

275. **ዳ[illegible]** :- መልኩ ብያ የተባለውን አረንጓዴ ድንጋይ ይመስላል፡ እሳት ሳይነካው ግሉ ታገኘው አለህ፡ ከውኃ ውስጥ ብትከተው ውኃውን ሙቅ ያደርገዋል፡ እርሱ በአለበት የመነጨ ውኃ ሁልጊዜ ምንጊዜም ሙቅ ይሆናል፡ በቤትህ ውስጥ ብታኖረው ቤቱ ሁሉ ይሞቃል፡ ብርድ አይኖርም።

276. **ፀዳል** :- አብነ ንስር ይባላል፡ ግልገል አንሳ ወይም የሰማይ ቀበሮ የሚባል አሞራ አለ፡ ይህን ድንጋይ አንስቶና ወስዶ በጉጆው ውስጥ ያስቀምጠዋል፡ ሲያረጅና አይኑ ሲታወር ታቅፎት ይተኛል። ከብዙ ቀን በኋላ ይታደስና አዲስ ቆዳ ለብሶ አዲስ ክንፍ አብቅሉ እንደ አሞራ ጫጩት ሆኖ ዝል ዝል ይላል፡ በመጨረሻ መብረር ይጀምርና አጥንትን በመስበር ግልገል በማንሳት ይውላል፡ እንዲሁ አንተም ከአሞራው ቤት አምጥተህ ስትደክም ብትታቀፈው ትበረታለህ፡ ታመህ እንደሆነም ትፈወሳለህ፡ አርጅተህ ከሆነም ወጣት ጉልማሳ ትሆናለህ፡ ለደካማ ኃይልን የሚሰጥ ጉልበት ለሌለው ብርታትን የሚሰጥ እንደዚህ ያለ ድንጋይ የለም፡ በዚህ ጥበብ አለ፡ ይህ ፀዳል ድንጋይ መልኩ አረንጓዴ ነው።

277. **[illegible]** :- ይህ ድንጋይ ባለበት አውሉ ንፋስ ይነሣል፡ የመብረቅ ብልጭታ ይታይበታል፡ መልኩ ሻካራ ሆኖ ቡሬ መልክ ወይም ሶራ መልክ አለው፡ ስትወቅረው ውስጡ ቀይና

ለማያዊ ቀለም አለው፡ ለፈርጥ የሚሆን አልማዝ ታገኝበት አለህ።

278. ዜ :- የባሩድ ዓይነት ሲሆን ሲቃጠል ዓይን ይጨልማል፡ አእምሮ ይሰልባል፡ መርዝነቱ ለሰውና ለእንስሳ ቀርቶ አፀዋት ሁሉ ጢሱ ከጤሰባቸው ይደርቃሉ።

279. ዜዎ :- የተጠባበቁ ድንጋዮች የተሰያየ ቀለም ያላቸው እነዚህ አዙረህ ከገበያ መሐል ብትቀብራቸው ገበያው ሁልጊዜ ይደምቃል፡ የህዝብ መናኸሪያ ይሆናል። ለምስያጥ እንዲሁ ከቤትህ መድረክ ላይ ቅበረው፡ ወይም በበርእፍ ቅበረው፡ ለሌላም ጉዳይ ይሆንልሃል።

280. ዙዮዘ :- የመብረቅ ድንጋይ ወይም ጥቁር ድንጋይ፡ ይህን ድንጋይ የሰው መልክ አስመስለህ በሮሃ ድንጋይ ቀርፀህ ከቤተ መንግሥት ከቤተ መቅደስ ከቤትህ ላይ እንደጉልላት አድርገህ ብታስቀምጠው እሳት አይበላውም፡ ጠላትም አይደፍርህም፡ መብረቅም አይወርድም፡ መልኩ ጥቁር ሆኖ ዘይት የፈሰሰበት ይመስላል።

281. ዙዮሻ :- ከድንጋይ ውስጥ የሚወጣ ትል አለ፡ እርሱን አቃጥለህ ለማይድን ቁስል ብትደመድመው ይድናል። በዚህ ብዙ ጥበብ አለና ቢያስሩትም መልካም ነው፡ ተፈላሰፍበት።

282. **ዙር** ፡- የሚባል የፈረፈር ድንጋይ አለ፡ መልኩ ወርቅ ይመስላል፡ ናሱን ብሩን ብረቱን ወርቅ ላስመስለው ካልክ በብዙ ወቅጠህ በጋን ከተህ አቡካውና የብረቱን አይነት አብረህ ከውስጥ አድርገህ ዙሪያውን እሳት አንድበት ጢሱ እንዳይወጣ አፍነው፡ ወርቅ ያስመስልልሃል፡ ለወርቅ ቀለም ይሆንሃል። ተፈላሰፍበት በዚህ ጥበብ አለና፡ እግዚአብሔር በፈጠረውና እንድንጠቀምበት በፈቀደው ጥበብ ለመላቅ ትጋና እወቅ።

283. **ዘሀብ** ፡- ለገንዘብ የሚሆን የወርቅ ድንጋይ ነው፡ አቅልጠህ ለፈለከው ጌጥ ይሆንሃል።

284. **ዛጉል** ፡- በባሕር በጨው ባሕር ውስጥ የሚገኝ የዛጉል አይነት ቅርፍቱ ለጌጥ የሚሆን ነው፡ የዛጉል አይነት ከሰባት መቶ በላይ ቢሆኑም ግማሾች በቅርፍታቸው ውስጥ የእንቁ ድንጋይ ቢያስቀምጡባቸው አድበልብለው አለስልሰው ስለሚይዙት አውጥቶ ለፈርጥ ጌጥ ማድረግ ይቻላል።

284. **ዞዚያ** ፡- ጠፍጣፋ ሆኖ ክብ የሆነ ድንጋይ ነው፡ ቤተመቅደስ ወይም ቤትህን ስትሰራ አንዱን ከመሰረቱ መሃል ሁለተኛውን ከመደምደሚያው ላይ አድርገህ ስምህን ጽፈህ አሽገው፡ ከጊዜ ብዛት መንፈስ በአንተ አካል መልክ ተመስሎ በቤትህ ውስጥ ይኖራል፡ ለብዙዎችም ታይቶ ይሰወራል፡ አንተን መስሎ ብዙ ሥራዎችን ይሰራል፡ ወይም

የምትወደውን የመልአክ ስም ቅረጽበት፡ በእሱ ስም ይታወቃል፡፡

285. **ዛንዶ** ፡- ነጭ የሆነና በቀላሉ የሚጠረብ አብክበረድ ድንጋይ ነው፡ ስፈለከው ነገር ከጠረብከ በኋላ ኖህያ የተባለውን ድንጋይ ወቅጠህ ቀባው፡ የማይሰበር ጠንካራ ይሆንልሃል፡፡

286. **ኢሙ** ፡- ለሸክላ የሚሆን የድንጋይ አፈር ነው፡፡

287. **ጨዕፐ** ፡- ሣጥን ወይም ገበታ የመሰለ ነው፡ በቤትህ ደጃፍ ብታደርገውና የጠየከውን ነገር ሰው ብትጠይቀው ይሰጥሃል፡ ለክብት ርቢ ይሆናል፡፡

288. **ኢቹየ** ፡- የተጠላለፈ ጌጥ የአለውና የሚያንጸባርቅ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ በፈለከው መልክ አስቀርጸህ ጧትና ማታ በምታየው ቦታ አስቀምጠው፡ የአስከብርሃል፡ የሰው ፍቅር ይኖርሃል፡፡

289. **ቹደ ቹደ** ፡- ከባሕር ውስጥ የሚገኝ ከፍት ግጥም የሚል የጋን አፍ መስሎ ታገኘው አለህ፡ እርሱ በአለበት የዛጐል ዓይነት ባለዛፍ ባለቅርፍት ታገኝአለህ፡ እርሱን አምጥተህ እንደሳጥን ድንጋይ ፈልፍለህ በውስጥ የፈለከውን ነገር አብረህ የአሸከሙ እንደሆነ አይከፈትም፡ አንተ ግን በአሸግህበት እጅህ ሦስት ጊዜ መታ መታ አድርገህ እጅህን

ጣል አድርገህበት ቆይቶ ይከፈትልሃል፡ አንተ ከሞትክ ግን ተዘግቶ ይቀራል፡ አይከፈትም ሌላ ምስጢር አለው።

289. **ቅሞቅዩ** ፡- ስትወቅረው ቀጭን ድምፅ የሚሰጥ ለሿሿቴ የሚሆን ለአክሲል ዘርፍ የሚሆን ድንጋይ ነው፡ በእሳት አቅልጠህ እንደለፌድ በስሱ አብጅተህ እየቀረጽክ ለዘርፍ አድርገው ለሙዚቃ መሳሪያ ለጸናጽል ለጽንሃ ይሆንልሃል፡ ለሌሎችም እንዲሁ ይሆናልና ተፈላሰፍበት።

290. **እሹዋ** ፡- ለቃጭል ለደወል የሚሆን የብረት ድንጋይ መልኩ ማገኛውን ብህያ የተባለውን ይመስላል፡ ስትመታው በድምጹ ትለየው አለህ፡ ተመራምረህ እወቀው።

291. **ሾሑደ** ፡- ለጺም ምላጭ የሚሆን ሻፎ ድንጋይ በእሳት አግመህ ብትወቅረው ለቢልዋ ለሰይፍ ለማረሻ ይሆንልሃል፡ በጣም የሳለ ይሆንልሃል።

292. **ሾሑዋ** ፡- መልኩ አረንጓዴ መስሉ ስትወቅረው ቢጫ መልክ የአለው ነው፡ ይህን የድንጋይ አፈር በእሳት ውስጥ የከተትከው እንደሆን ይበተናል፡ አሸገህ ከእሳት ውስጥ የጣልከው እንደሆን ይፈነዳል፡ ተጠንቀቅ እንዳይጉዳህ ሰውም እንዳትጉዳ የጥፋትን ሥራ አትሥራ፡ በሰራኸው ክፉ ሥራ አጥፍተህ እንዳትጠፋ።

293. ፻፷፪ ፡- መልኩ ከሰል የመሰለ ጥቁር ድንጋይ ነው፤ ከድንጋዩ ውስጥ በጣም የጠቆረና የጠራ እንቁ ታገኝለሰህ፡ በነጭ ወርቅ አድርገህ በጣትህ ወይም በደረትህ አድርገው፡ ጠላት አያይህም፡ በአንተ ላይ አስተውሉ ቀስት አይወረውርብህም።

294. ፻፷፫ ፡- አረንጓዴ መልክ የአለው ሆኖ ስትሰብረው ቢጫ ይሆናል፡ ጥንክርና የለውም፡ ሾሹዋ ከተባለው ጋር የሚሰያዩት እንደኩበት ፍርክስ ፍርክስ ስለሚል ነው፡ ነገር ግን በቀስት ላይ አጣብቀህ አቃጥለውና ወርውረው ከገመትከው በላይ እየነደደ ይወረወራል፡ ለአረር የሚሆን ነው።

295. ፻፷፬ ፡- ነዳጅ አፈር ሰባሩድ የሚያገለግል በፈንታሌ ተራራ ላይ ታገኘው አለህ፡ እርሱ ባለበት ጺን ይገኛል፡ ለአረር የሚሆኑ አፈሮች ሁሉ ይገኙበታል።

296. ፻፷፭ ፡- እሳት የማያቀልጠው የብረት ማንጠሪያና መቀጥቀጫ የሚሆን ጽኑ ድንጋይ ነው፡ ብረት መስሉ ታገኘው አለህ።

297. **ጀንጠፍ** ፡- የሚባል ደማቃ በረዶ የመሰለ ነው፡ በእሱ ላይ ስምህን ቀርጸህ ጧትና ማታ ከምታየው ብታስቀምጠው የጠላኸው ሰው ይርቃል፡ በአንተ ላይ ክፉ ሲያደርግ ቢኖ ክፋቱ ለእርሱ ይሆናል ይጠፋል፡፡

298. **ጀሰባ** ፡- መልኩ ሰማያዊ ቀለም ይመስላል፡ ለጠፍ ያለ ጡት የመሰለ አለው፡ በምንጭ ራስ ብትቀብረው አይነጥፍም፡ ከውሃ ውስጥ ስታደገው ውኃው አያልቅም፡ አይሸትም ጡት የመሰለውን ሽፍን አድርገህ ይዘህ በረሃ ብትሄድ ውኃ አይጠማህም፡ ለከብቶችህም እንዲሁ አድርግ፡ ውኃ አይጠማቸውም፡ በዚህ የድንጋዮችና የዕንቁ ጥበብ ምስጢር አለ ይገለጽልሃል፡፡

299. **ጁዋሺ** ፡- የብረት መዶሻ ወይም ምሳል የመሰለ ነው፡ የዋሻ ቤት ለማድረግ አለቱን ብትወቅርበት በቀላሉ ይጠረብልሃል፡ የዋሻ ቤት የአለት ምድር ቤት ለማበጀትና ለማጊጥ እንደዚህ የአለ ድንጋይ የለም፡ ሰይፍ አድርገህ ብታስረው የሰው ገላና እንጨት ይቅርና አለቱን ብትመታበት ይሰነጥቀዋል፡ ዛፉን እንደሳር አጭዶ ይጥለዋል፡ መልኩ ሰው የሰራው መዶሻ መስሎ ጥቁር ቡላ ድንጋይ ነው አይወቀርም፡፡

300. **ጅጉደ** ፡- የአሳተ ገሞራ ድንጋይ መልኩ ቢጫ ሆኖ ልምድድ ነው፡ ከምድር ልብ ወደ መልካአ ምድር ብቅ ሲል የመሬትን ገላ የአቀልጠዋል፡ እንደ አለት ዳቦ ያደርገዋል፡ ረውሀ ወይም

ሮሃ ከተባለ ድንጋይ ወይም ተንካራ ቶጳዝዮን ከተባለ ከእንቁ ድንጋይ ላይ ተቆቶ ታገኘው አለህ፡ በጥንቃቄ ከድንጋዩ ጋር ወስደህ በበላዩ ብያ የተባለውን ድንጋይ ብታስቀምጥበት ግም ይቀልጣል፡ አለት ወይም ብረት ይሆንልሃል፡ በዚህ የድንጋይ ሐውልት አቅልጦ ለማቆም የድንጋይ ሳጥን የድንጋይ ቤት ለመስራት ይሆናልና በዚህ ልምድድ ድንጋይ ጥበብ አለና ተፈላሰፍበት።

301. **ጌራ ጌራራ** ፡- በራስ ወርቅ ላይ በአራት ማእዘን የሚጣበቁ የእንቁ ድንጋዮች ናቸው። ከድንጋይ ውስጥ ታገኛቸው አለህ፡ አራት ዓይነት ቀለም መልክ አላቸው፡ ሳትለያይ የአደረካቸው እንደሆነ በወርቅ የለበጥካቸውና በራስህ ላይ የአደረካቸው ከሆነ ትሾምትአለህ፡ በእድሜህ ሙሉ ባለሥልጣን ትሆናለህ፡ ነጣጥለህ የያዝካቸው ከሆነ በውርደት ትኖራለህ፡ የአሰብከው ሁሉ አይሆንም፡ በዚህ የእንቁ ድንጋዮች ጥበብ አለና አስተውል።

302. **ሉዩጉ** ፡- ከውስጡ እንደብርሃን እንደ ፍህም የመሰለ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ ይህን ድንጋይ ሳትሞርድ ሳትፈለፍል በክብር ቦታ በአካባቢህ ብታስቀምጠው የራቀውንና የሚመጣውን ወደፊት የማደረገውን ሁሉ በልብህ ይገለጸል። ህልምህ እሙን ይሆናል፡ መክስተ ራእይ ነው፡ ከሰበርከው ከውስጥ

ይጠፋል፡ ነገር ግን ቢጫ የመሰለ ታገኛለህና እንዳታየጊጠው እድሜህን ያሳጥርብሃል የሚቀስፍ ድንጋይ ነው።

303. **ጋጉደ** ፡- ይህ ድንጋይ እርጥብ ውኃ የፈሰሰበት ይመስላል፡ ከውኃ ብታገባውና ብታወጣው ውኃ ሳይነካው ታየውአለህ፡ እንደሚዛን ሰርተህ አፈርን ውኃን እሳትን ነፋስን ብትመረምርበት የሆነ ምልክት ያሳይሃል። በመሰለህ ዘይ ብታዘጋጀው ለፍልስፍናህ ያግዝሃል፡ በዚህ ብዙ ዓይነት ሥራ መፈላሰፍ ትችላለህ፡ አስተውለህ መርምርበት በጥበቡ ትረካለህ።

304. **ጊባ' ዘ■ገቅዴሳን** ፡- የሚባል እንደ እጅ ጌጥ አምባር የመሰለ ድንጋይ ነው፡ በወገብህ ብትይዘው ድካም ረሃብ ጽም አያጠቃህም፡ ጠላትም ቢነሣብህ አያሸንፍህም ከምትፈራው ነገር ይሰውርሃል፡ የማትወደው ነገር ከአንተ ይርቃል፡ የእግዚአብሔር ቸርነት የሚገለጽበት ነው፡ መልኩ ቀያቴ ቢጫ ነው፡ ማጭድ ይመስላል።

305. **ገ■ዘ** ፡- ሶስት ሶስት ማእዘን ያለው ድንጋይ ነው፡ በቅጽርህ ዙሪያ ትከለው፡ ብዙ ሰማያዊ ምስጢር ታያለህ፡ በዚህ ከትልቅ ነገር ትደርሳለህ፡ የአሰብከው ይፈጸማል።

306. **ጊንፋ** ፡- የሚባል ጉልቻ የመሰለ ድንጋይ በዋሻ በባሕር ዳር

ታገኘው አለህ፡ ለስቱን ጉልተህ የአልበሰለ ምግብ ብታቀያብት የአበስለዋል፡ ለአፍልሆ ወይም ጠጅ ቀሉ ለማድረስ ይሆናል፡ እግዚአብሔር ሰውን በብዙ ዓይነት ይረዳዋል፡ እንዲጠቀም ያደርገዋል።

307. **ቀንድብ** ፡- የሚባል መልኩ ቡላ ሆኖ ወይም የምናየውን መስሉ የዱላ ጅንፎ ይመስላል፡ በዘንግህ ጫፍ ወይም በደረትህ ብትይዘው ጠላት አያጠቃህም፡ ድል ታደርጋለህ።

308. 1. **እቁ** ፡- የአንቁ ድንጋዮች ነጸብራቁ አንድ ብቻ ከሆነ በወርቅ ለብጠህ በአንገትህ እሰረው።

2ኛ. ነጸብራቁ ሁለት ከሆነ በሰውነትህ አታድርገው፡ ኑሮህ በካና ይሆናል።

3ኛ. ነጸብራቁ ሦስት ቀስት የአለው ከሆነ በጦር ጊዜ በመከራ ጊዜ በአንገትህ አድርገው፡ ይጠብቅሃል በሰላም ጊዜ አትሰረው እድሜህን ያሳጥራል፡ ለከፉቀን ብቻ ተጠቀምበት /መልኩ ደማቃ ሰማያዊ የወይን ጠጅ የሆነ ብቻ/

4ኛ. ነጸብራቁ መስቀለኛ ከሆነ በቢጫ ወርቅ ላይ አድርገህ በእጅህ ጣት በደረትህ የአደረከው እንደሆነ ለሐብት ለበረከት ይሆንሃል። በነጭ ወርቅ አድርገህ የአሰርከው እንደሆን ለግርማ ሞገስ ለፍቅር ለሲሳይ ይሆንሃል፡ በነጭ ብር ለብጠህ የያዝከው እንደሆነ ለአቃቤ ርእስ ይሆንሃል፡ ብርሃን መስቀል ነውና ከምትፈራው ነገር ይጠብቅሃል፡

መልኩ ነጭ ወይም ቀይ አረንጓዴ ነጣ ያለ ሰማያዊ የሆነው ነው።

5ኛ. ነጸብራቁ አምስት ቀስት ወይም ባለአምስት ቀስት የኮከብ ምሳሌ ተቀርጾበት ከአየህ ለሁሉ መልካም ነው፡ ሹመትንና ሐብትን ያመጣልና፡ በፈለከው አድርገህ ከአንገትህ እሰረው መልኩ ነጣ ያለ ሰማያዊ ከሁሉ የተሻለ ነው።

6ኛ. ነጸብራቁ እንደ ዳዊት አርማ ስድስት ቀስት የአለው ኮከብ ከሆነ በቤትህ በቤተ መቅደስህ በአለው መንበር ላይ ለጥፈህ አስቀምጠው፡ እግዚአብሔርን በጸሎት በምትጠይቅበት ጊዜ ዳብሰው እንጂ አትሰረው ጠላት ይበዛብሃል፡ ነገር ግን አያሸንፍህም።

7ኛ. ነጸብራቁ ሰባት ቀስት የአለው የኮከብ ምስል ከሆነ በክብር አስቀምጠው እንጂ ለጌጥ ብለህ አታስቀርጸው።

የእንቁ ቀለሞች ቀይ ነጭ ቢጫ ሰማያዊ ለሁሉም መልካም ነው፡ ጥቁር ዋርዳ ደማቃ ሰማያዊ አረንጓዴ የወይን ጠጅ ያለ ቢጫ ወርቅ አትሰረው፡ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል፡ ዘርህን ያከስላል፡ ለጤና ጥሩ አይደለም፡ ለሚቀመጥና ለሚታይ ብቻ በመንበርህ አጠገብ አኑረው።

309. **ቂቃይ** ፡- ነጸብራቁ ዓይን የሚያደክም የእንቁ ድንጋይ ነው፡ መልኩ እንደመስታዋት እንደክርስቶ ድንጋይ ነው፡ ነገር ግን በቀላል መሳሪያ አይደፈርም፡ እሳትም አያግለውም፡ ለመንኮራኩር ይሆናል፡ በዚህ እንቁ የታገዘ ሳጥን ፈጽሞ

እሳተ ገሞራ አይነካውም፣ ከሌላ ዓለም ተከፍሉ የመጣ ነውና።

310. **ቁየቃዲያ** ፡- እንደ ረውሃ የጠነከረ ሆኖ መልኩ የጠራ መስታዋት የመሰለ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ ይህ እንቁ ከቲቃያ እንቁ ድንጋይ ጋር አንድ አይነት ጥንክርና ሲኖራቸው፡ በነጸብራቅነት በፍልቅልቅነት ይለያያሉ፡ ነገር ግን ለጥበብ ለፍልስፍና አንድ አይነት ናቸውና እስተውለህ ተፈላሰፍበት፡ በእነዚህ ብዙ የጥበብ ምስጢር አለ።

311. **ቀቡት** ፡- የውሃ ማጠራቀሚያ ሆኖ ማድጋ የመሰለ ድንጋይ ነው፡ ከዚህ ድንጋይ የሚገኘን ውኃ ቢታጠቡበት ከህመም ይፈውሳል። በቤትህ በር አድርገህ ውኃ ሞልተህ ተወውና የጠማው ከእሱ ይጠጣ ይረካል፡ መንፈሱ ይታደሳል፡ ሥቃዩን ይረሣል፡ መልካም ድንጋይ ነው።

312. **ቀርነበ■** ፡- መአዛ የአለው ከርቤ የመሰለ የሽቱ ድንጋይ ነው፡ ይህ ድንጋይ ባለበት የሚፈልቅ ውኃ ጥሩ ሽታ የአለው ይሆናል፡ ከቀርነሰው ድንጋይ የሽቱ ዘይት ይወጣልሃል፡ ብትቀባው ቆዳህን ያሳምረዋል።

313. **ቀርኚ** : ቀንድ የመሰለ ድንጋይ ሆኖ ውስጡ ድፍን ነው፡ ቤት ሰርተህ ስትጨርስ በጉልላቱ ላይ አድርገው፡ ለቤተ መቅደስም እንዲሁ፡ ቤትህን ጠላት አይደፍረውም፡ ቤቱን

ለማፍረስ ቢሞክር አደጋ ይደርስበታል፡ ከከፉ ነገር ሊያመልጥ አይችልም።

314. **ቅቡእ** ፦ ቅባት የአሰው ድንጋይ በእሱ ላይ ሁኑህ ጸሎት ብትጸልይና ቅዱስ ቅባት ብትቀባ በህዝብ ዘንድ የተከበርክና የተወደድክ ትሆናለህ፡ የፍቅርና የሲመት ድንጋይ ነው፡ የድንጋዮችና የእንቁ ጥበብ በዚህ ይከብራል፡ ጆሮ ያሰው ይስማና ያስተውል ዓይን የአሰውም ይይና ይመልከት፡ አእምሮ የአሰውም ተመራምሮ ይፈላሰፍ።

315. **ቂፋዝ** ፦ ከድንጋይ ውስጥ የሚገኝ የወርቅ ድንጋይ ነው፡ ከአለት ዳባ ላይም ተጣብቆ ይገኛል፡ መልኩ አረንጓዴ ጥቁር ነው፡ መስቀል አሰርተህ የታመመን ብታሽበት ይድናል፡ ወይም ይሞታል እንጂ አያስቃይም፡ ጻረሞት አያሲዝም።

316. **ቂቆና** ፦ መልኩ አረንጉዋዴ ይመስላል፡ ስትወቅረው ውስጡ ቀይ ቀለም ይመስላል፡ በጨለማ ስታየው ፍህም ይመስላል፡ እንደሙሴ ጽላት እንደ ዳዊት አርማ ኮከብ እንደ እየሱስ ክርስቶስ መስቀል አስቀርጸህ በቤትህ በቤተ መቅደስህ ብታስቀምጠው እግዚአብሔር የተሳልከውን ይሰጥሃል፡ ይፈጽምልሃል፡ ይህ ድንጋይ ባለበት ውሉ የአደረ ሰው ሁሉ ህመሙ ይጠፋል፡ ህይወቱ ይታደሳል፡ የእግዚአብሔርን ቸርነት ያይበታል።

የእግዚአብሔርን ስም ሶስት ጊዜ የአገሩን ስም ሁለት ጊዜ የአንተን ስም አንድ ጊዜ እንደማህተም አስመስለህ በበሳዩ ቅረጽበትና በክብር ቦታ አስቀምጠው፣ ምህሳበ ሰብአ ወምህሳበ ንዋይ ይሆንሃል፣ በዚህ ክቡር ድንጋይ ብዙ ጥበብ አለ፣ አስተውለህ በመንፈስ እእምሮህ መርምረው፣ ይገለጽልሃል።

317. **ቅንፋል** ፡- ከረምት ውኃ ይዞት በበጋ ከሚደርቅ ወንዝ አሸዋ ውስጥ ሶስት ድቡልቡል ድንጋዮች ተያይዘው ታገኛለህ።

"በጉንሄ ኩኩምናሄ ቶብጹራ ትንም ቃአሞ ምጻሄ ያሽደራን ቃያሽም ተያሽም አብ መዋዒ ወልድ መዋዒ መንፈስ ቅዱስ መዋዒ መሂዶ አብርሮ ወቅትሉ ሰፀርየ እ/ ብስህ ተቃዋሚህ ወደአለበት አገር በእንጻሩ ወርውራቸው አገር ለቆ ይሄዳል፣ ወይም ይጠፋል፣ ወይም መከራ ይመጣበታል፣ ሆኖም ክፋን በክፉ አትቃወም፣ የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል አክብረህ ፈጽም እንጂ እበቀላለሁ ብለህ በሰው ላይ ክፉ ማድረግ ይቅርና አታስብ፣ ይህን ብታደርግ እግዚአብሔር ይበቀልልሃል።

318. **ቀበሚምንሞስ** ፡- መልኩ ሰማይ ይመስላል፣ ይህ ድንጋይ በአለበት እንደ እርባሜ አፈር እየመሰለ ከመሬት ወደላይ ይወጣል፣ ይከመራል፣ ከጊዜ ብዛት ወደ ድንጋይ ይቀየራል፣ ብያ የተባሉትን ድንጋዮች ለማድቀቅ ወይም ለማቅለጥ ብረት

ወይም ሳንቃ እስመስለህ ወይም ሣጥን ሰርተህ ቀሴምንጦሱን በውስጥ ብያ የተባሉትን ድንጋዮች በላዩ አድርገህ ገጥመኸው ሂድ፡ አቅልጦ አንድ ድንጋይ አድርጎ በበላያቸው ሆኖ ታገኘው አለህ፡ ድንጋዮች ቀልጠው ሳይረጉ ከደረስክ እጅህ ሳይነካው በብረት ፋጋ ዝቀህ እንደጭቃ ድንጋዩንና ድንጋዩን አገናኝተህ እንጻው፡ አንድ ይሆንልሃል፡ ለሐውልት በዚህ መልክ መስራትና ማቆም ትችል አለህ፡ ብያ የተባሉት ድንጋዮች እንጉዳይ ይመስላሉ፡ በጣም ጠንካራ እንዲሆንልህ የቀለጠውን ድንጋይ በእሳት ተኩሰው ጥቁር የድንጋይ ሐውልት ይሆንልሃል፡ በዚህ ድንጋይ ብዙ የሆነ የድንጋይ ጥበብ አለ፡ ጠቢብ ፈላስፋ ለመሆን እስተውሉ ይመርምር ፡ እግዚአብሔር የጥበቡን መንፈስ ይሰጠዋል፡፡ እንዲሁ ቀሴም የምትባል ወፍ ጉጆዋን ቀሴምንጦስ ከከመረው አፈር ወስዳ ትሰራለች፡ ድንጋይ ይሆንላታል፡፡

319. **ቀሰመእብን** ፡- ዘአካለ ምድር የሚባል መልኩ በሩቅ ስታየው ነጭ ቀለም የተቀባ ይመስላል፡ በገጣቱ ይለያል፡ ሲወቅሩት ውስጡ አረንጓዴ መስሎ ጥቁር ቀለም ይመስላል፡፡ ይህን ቀለመ እብን የተባለውን ወቀጠህ አንድ እጅ ስፍር ባሩድ አንድ እጅ ስፍር ዘይት ሶስት እጅ ስፍር ውኃ ሶስት እጅ ስፍር ቀለመ ዕብን አድርገህ በብረት ሽክላ ውስጥ ሞልተህ ቀቅለውና በቀቀልከው ውኃ በንጹህ ቀይ አፈር ወይም በላመ አሸዋና ድቡሽት እንደጭቃ እቡክተህ ለውስህ ቤትህን

መርገው፡ ጧት ልሙጥ ድንጋይ ሆኖ ታገኘው አለህ፡ የጠለሰው ኩል ውኃ ይመስላልና ሴት ብትጠጣው ትመክን አለች፡ ለቁርጥማት እንዲሁ አጠጣ ለፈለከው ነገር እንደ ሲሚንቶ እያስጦህ ከአፈር ከአሸዋ እየቀላቀልክ ሥራበት፡ አለት ድንጋይ መስሎ ይቀራል። እንደ ሸክላ ማድጋ አድርገህ ብትሰራው የድንጋይ ጋን ይሆንልሃል፡ በዚህ ብዙ ዓይነት የጥበብ ሥራ አለ፡ ተፈላሰፍበት።

320. **ቁርቁ ማንሰብ** ፦ የሚባል መልኩ ነጭ እጣን የሚመስል ድንጋይ ከባሕር ዳር ታገኘውአለህ፡ ቤተመቅደስ ወይም ቤትህን ስትሰራ ከመሃል ላይ ቅበረውና መሠረቱን ጾምርና አንፀህ ጨርስ ለረድኤት ለበረከት የሚሆን ድንጋይ ነውና ሁልጊዜ ሐብት ያለበት ቦታ ይሆናል፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ያድርበታል፡ ትንሽም ትልቅም ነው።

321. **ቃለሕይወት** ፦ የሚባል መልኩ ስስ በረንቅ መስሎ ሲመቱት እንደ ደውል ድምጹ ይጮሃል፡ በቤተ መቅደስ ደጃፍ ስቀለውና ጸሎት ስታደርግ ምታው፡ መግረሬ ሰይጣናት ነው፡ ጋኔን ለሚጥለው ሲጥለው በጆሮው አስጠግተህ ብትመታው አፈራግጦት እንደፍድፎት ይሄዳል፡ ሁለተኛ አይጥለውም፡ የጠላኸውን ሰው አገሬን ከዚህ አገር አርቀው ብለህ ብትመታው ይሰደዳል፡ ተመልሶ አይመጣም፡ መስተባርረ ፀር ነው።

322. **ቆና** ፡- የሚባል እንደ እንቁላል ድብልብል ብሎ ጫፍ ጫፉ ትምክ ያለ ነው፤ ጠንካራ ነው፤ አይሰበርም፤ እሱን ከምትጠጣው ውሃ ውስጥ ብታደርገው እንደ ወይን የሚጥም ይሆናል፤ ብዙ ጊዜ ከበረሃ ታገኘውአለህ።

323. **ቆቅቦ** ፡- የሚባል ጉታ ወይም የጋን አፍ የመሰለ ድንጋይ አለ፤ እህል ለከሰከሰው ለአስጠላው ትንሽ ሽርፍ ቢይዝ እንደልቡ ይበላል፤ ነገር ግን መርገመ እብን ስለሆነ አርቀው ድኃ ችጋራም ያደርጋል፤ ሕዝብ ያፈልሳል፤ የጥፋት መሳሪያ ድንጋይ ነውና፤ አትጠቀምበት ከህዝብ አርቀው።

324. **ቅንደበ ዓደን** ፡- እንደመቁጠሪያ የመሰለ ነው፤ ከበሐር ጠረፍ ካለ አሸዋ ጋር ታገኘው አለህ፤ ከእግርህ እንደአልቦ ጎጥ ብታስረው ጠንካራ ፈጣን ሩዋጭ ትሆናለህ፤ በአንገትህ በወገብህ ብታስረው የወገብ ህመም ይጠፋል።

325. **ቁዶን** ፡- በረዶ የመሰለ ነጭ እንቁ ድንጋይ ከሌላ እንቁ ጋር ቀላቅለህ በወርቅ ለብጠህ ብታስረው ሐብታም ትሆናለህ ለዘውድ ጥሩ ነው፤ ብቻውን ግን ብትይዘው ድኃ ትሆናለህ፤ የአየህ ሁሉ ይጠላሃል፤ የሚያከብር የሚያደኸይ ድንጋይ ነው።

326. **ከርከዴ** ፡- በጣም ጥቁር የሆነ የእንቁ ድንጋይ ነው፤ ለመግረሬ ፀር በወርቅ ቀለበት ላይ ፈርጥ አድርገህ እሰረው።

327. **ክርትም** ፡- የሚባል ከዋሻ ውስጥ ሙቀጫ መሰሉ ታገኘው አለህ፡ በጣም ጠላት ሆኖ ሲተነሣብህ የእርገፍጋፎ ሙቀጫ ልጅ አበጅተህ ስሙን በወረቀት ጽፈህ ከተህ እንዲህ ውቀጠው፡ ይታመማል።

328. **ክቡድ** ፡- ከባድ ድንጋይ በአማርኛ ስሙ ክብረ ሰማይ ይባላል፡ መልኩ ሰማያዊ ነው፡ ኩልን ይመስላል፡ ወቅጠህ ከሎሚ ውኃና ከዘይት ጋር ለውሰህ ቀቅለውና ብረቱን ብትቀባው ናስ ይመስላል።

329. **ኩሄል** ፡- ለአይን የሚያስደስት ለይተውት የማይጠገበ መልኩ የወይን ጠጅ ዋርዴ ደማቃ ሰማያዊ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ በነጭ ወርቅ ለብጠህ ከቤትህ በክብር አስቀምጠው የአሰብከው ሁሉ ይሆናል፡ ትከብርአለህ።

330. **ክርስቲሎቤ** ፡- የብዙ ቀለም መልክ የአለው የእንቁ ድንጋይ ነው፡ ዝጉርጉርም ነው፡ ለክብር በቤትህ አኑረው።

331. **ኩሬ** ፡- መልኩ ደማቃ ሰማያዊና የወይን ጠጅ የመሰለ ነው፡ ነጭም አለው፡ ነጩ ወቅጠው በውኃ ውስጥ አድርገው ቢጠጡት የውስጥ የደም ስርን ያጣራል፡ ሰማያዊ የሆነ አይን ቢኳሉት ዓይኑ ይጠራል በዚህ ጥበብ አለ።

**ክርስቶ** ፡ እንደ ጠርሙስ የጠራና ነጸብራቅ የአለው ድንጋይ ነው፡ እንደ እንቁ ጠንካራ አይደለም፡ ነገር ግን በቤትህ በእጅህ

አይጥፋ፤ ያዘው ያላሰብከውን ሐብት ያመጣልሃል፤ አድዛኝ ሰው ትባላለህ፤ መፍትሔ ሐብት ነው።

332. **ኮኬ፡ ኩኩሕ** ፡- ሰማያዊና ነጭ አለት የሆነ ጠንካራ ድንጋይ ነው፤ ይህ ድንጋይ ሕይወት በአለው ቃል ሲነገር የኖረ ነው፤

"እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም /አጋንንት/ አይችሉትም" የተባለለት ጠንካራ ድንጋይ ነው።

"እግዚአብሔር ዓለቴ! አምባዬ! መድኃኒቴ! አምላኬ! በእርሱ የምተማመንበት ረዳቴ መታመኛዬና የደህንነቴ ቀንድ መጠጊያዬም ነው። መዝ. 172"

የተባለና በእግዚአብሔር እርዳታና ቸርነት የተመሰለ የአለት ድንጋይ ነው፤ ይህን ድንጋይ ቤት ስትሰራ ስምህን አስቀርጸህ ቤተ መቅደስ ስትሰራ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ቃላቶችና የእግዚአብሔርን ስም አስቀርፀህ እርሱን መሰረት አድርገህ ብታንፅ ጠላት አይንደውም አያፈርሰውም፤ በቦታው የእግዚአብሔር መላክ አይለየውም፤ በጼዴሳ በረሃ ካፎች በሚኖሩበት አገር ሞልቷል፤ ሰማያዊ እብነ በረድ ይባላል፤ ይህ ድንጋይ በአለበት ምድር ቢጫ ወርቅ አለ።

333. **ኦደኪ** ፡- ወርቃወርቄ መልኩ የሚብረቀረቅ የድንጋይ አፈረ ሳጊጥ በፈለከው ነገር እየለወስክ አጣብቀው፤ ይፍለቀለቃል እንጂ ለሌላ አይሆንም።

334. **ከኩዩ** ፦ በሳይም ይሁን ስትፈልጠው መስቀለኛ የሆነ ጭረት የአለው ነው፡ በቤትህ አንጻር አስቀምጠው፡ ከተሳሳፊ ይጠብቅሃል፡ ይሰውርሃል፡ ከፉ ነገር አያገኝህም፡ አቃቢ ሕይወት ነው።

335. **ከኩ** ፦ ስመ አንፋር የሚባል የድንጋይ መርዝ እርሱ በሚገኝበት አካባቢ እንደ ድንጓይ እጣን መስሎ በክረምት እንደ ሙጫ ከድንጋይ ውስጥ ይወጣል፡ እርሱን በቀስት በጦር ጫፍ ቀብተህ የወጋኸው አውሬ አይድንም፡ ይመረዛል፡ መልኩ እንደስመ አንፋር ነጭ አይደለም፡ ቢጫ አረንጓዴ ነው፡ ሲደርቅ ቀያቴ አረንጓዴ ይመስላል፡ በዚህ ድንጋይ ለጥፋት የሚሆን ከፉ ነገር ይሰራብታል፡ ነገር ግን አንተ ከክፋት ስራ ሁሉ ራቅ፡ ክፉን በክፉ አትቃወም፡ ሥራው /ያጠፋዋልና/ ለሠሪ የተባለ በዚህ ነውና።

336. **ኩደኬ** ፦ የድንጋይ ከሰል ከዲኝ ጋር አድርገህ አቃጥለው ይነዳል፡ ለብረት ማቅለጫ ያገለግልሃል፡ እንዲሁም ለሌሎች የብረት ሥራዎች ስለሚሆን ተፈላሰፍበት።

337. **ኮካሺ** ፦ ለቆርቆሮ ለንኬል ለብረትድስት የሚሆን የብረት ድንጋይ አይነት በእሳት እያጋልክ ወይም አቅልጠህ ፈትነው፡ እንደፍላጎትህ የሚሆነውን ታውቀው አለህ።

338. **ኩዮኩደ** ፡- የወርቅ መመርመሪያ የእንቁ ድንጋይ መልኩ ከጥራቱ የተነሣ ከአላስተዋሉት የማይታይ ነው፡ እርሱን በርሀ ድንጋይ አጉድጉደህ ወርቅንም ይሁን አልማዝን እንደመነፅር አድርገህ እየው፡ የውስጡን ንጥረ ነገር አጉልቶ የአሳይሃል፡ እንዲሁ የገላህን ቆዳ ብታየው በውስጡ የአሉትን ጅማትህን ደምህን አጥርተህ ማየት ትችላለህ። ብዙ ዓይነት ማወቅና ማፈላሰፍ ትችልአለህ፡ በጥበበ እእባን ስማቸው የተመዘገቡትንና የአልተመዘገቡትን ሁሉ አጉልተህ የምትመረምርበት ይሆናል፡ በዚህ የድንጋዮች ጥበብ ይከበራል።

339. **ኬንዓም** ፡- መልኩ በጣም ነጭ ወተት የመሰለ ነው፡ በምድረ በዳ በበረሃ ከምንጭ አጠገብ ብትፈልገው ታገኘው አለህ፡ እሱ ባለበት ምንግዜም ውኃ አይጠፋም፡ እንዲሁ ከጠፋ ምንጭ አምጥተህ ብትቀብረው ውኃው ይወጣል፡ ከተማ ስትቆረቁር አዙረህ ቅበረው ጥሩ ዝነኛ ከተማ ይሆንልሃል፡ መስተሳልመ ሰብእ ነው።

340. **ሊኩደ**፡- የሚባል ድንጋይ ሳሩን ዛፉን የሚያደርቅ የሚያነግል ድንጋይ ነው፡ ይህን ድንጋይ ለማግኘት ለጥ ካለ ሜዳ ላይ አካባቢው ሁሉ አለምልሞ ድንጋዩ ባለበት ሥፍራ አሸዋ የተንከባለለበት ደረቅ ሆኖ ምንም እፀዋት የሌለበት ሆኖ ታየው አለህ፡ እሱን ቆፍረህ አውጥተህ ከምንጭ ራስ

ብትቀብረው ይደርቃል፡ አገር አዙረህ ብትቀብረው ይፈልሳል፡ ኬንሃምና ኢኩይን በአንድ ላይ አድርገህ ወይም ኬንሃምን በላይ ኢኩይን በታች አድርገህ አገሩን አዙረህ ብትቀብረውና በበላዩ ሃውልት ብትሰራ የዓለም መናሐሪያ ከተማ የሰላም የፍቅር ከተማ ይሆንልሃል፡ ክፉና ደጉ ሰው ሁሉ ተፋቅረው ይኖራሉ።

341. **ሁይሁ** ፡- መልኩ እንደ መስታዎት እንደ ክርስቶ የመሰለና የጠራ ንጹህ የእንቁ ድንጋይ ነው፡ የፀሐይ ጨረር ሲያርፍበት የሚያፈልቀው የነጸብራቁ ጨረር ከአረፈበት ላይ ስታየው ብዙ ዓይነት ቀለም የአለው ሆኖ እንደቀስተ ደመና ምልክት ቀለም ታያስህ፡ ይህን ሁይሁ የተባለን እንቁ በመሰለህ ፍልስፍና እንደመነጽር ማጉያ አድርገህ ብትሰራው፡ የራቀን አጉልቶና አጥርቶ ያሳይሃል እንጂ አቅርቦና አጉልቶ ለማሳየት እርቀት አያግደውም። በዚህ የእንቁ ድንጋይ ጥበብ አለ።

342. **ሐሙራ ሐምራዊ** ፡- የወይን ጠጅ የመሰለ ሰማያዊ ቀይ ቀለም የአለው በእሳት ሲከቱት የሚቀልጥ የድንጋይ አፈር እንደማርዳ ሰጌጥ ብትሰራው ወይም እንደብርሌ ብትሰራው የአማረ ጌጥ ያለው እቃ ይሆንልሃል። በባሕር ውስጥ ታገኘው አለህ፡ ለጤና ለሰላም ለፍቅርም ቢይዙት ይሆናል።

343. **ሐመዐ** ፡- እንደዘጭመረጭ ሆኖ ከምድር ውስጥ አሞልሙሎ በክረምት ወራት የሚወጣ አለ፡ ዘጭመረጭ መሰሉ ከሚወጣበት ብትቆፍረው ሐውል የሚባለውን የድንጋይ ጭቃ ታገኘው አለህ፡ እርሱን አውጥተህ እንደጭቃ ድንጋዩን የአነጽክበት ወይም ሐውልት የሠራህበት እንደሆን ለጊዜው አጣብቆ ይይዘዋል፡ ብዙ የክረምት ወራቶችን ከአሳለፈ በኋላ አንድ አድርጎ የአለት ድንጋይ የአስመስለዋል፡ ድንጋዩ ባለበት ህዝብህ በሰላም ይኖራል፡ ክፉ ሰው ቢነሣ ይጠፋል።

344. **ሐሰደ** ፡- ድንጋይ ልብሱ ኢሊን የመሰለ ነው፡ ውስጡ ግን ድፍን ነው፡ እርሱን አምጥተህ በጐተራህ በጐታህ ስር ብትቀብረው በረከት በቤትህ ይሆናል፡ የምትበላው አታጣም፡ ችግርና ረሃብ በአንተ ዘንድ አይደርሱም፡ መልኩ ወተት የመሰለ ነጭ ድንጋይ ሐሊብ የሚባለውንና ሔለይን በአንድ ላይ እንደመስቀል አስቀርጸህ ምግብህን ብትባርከው ይበረከታል፡ በአንገትህ ብታስረው ሐብታም ትሆናለህ፡ እግዚአብሔር የረድኤትና የበረከት ጸጋ ሰጥቶታልና አንተም ተካፋዩ ወይም ጸጋውን የምትጋራው ትሆናለህ።

345. **ሄና** ፡- የሚባል መልኩ አረንጓዴ ሆኖ ቀይ ቀለም የተረጨበት የመሰለ ሲያዩት የሚያስደስትና ምስሐበ ዓይን የአለው ነው፡ ብትይዘው ከፊትህ ባታርቀው የአየህ ሁሉ ይወድሃል፡ ለመከን በውሃ አጥበህ አጠጣና አሲዝ የመከነ

ሁሉ ይወልዳል፡ ህመሙን ከሆድ ውስጥ ነቅሉ ያወጣል፡ እብነ መድኃኒት ነው፡፡

346. **ሔብረፀሑይ** ፡- የሚባል ከአንድ ቦታ አሥራ ሁለት ሆኖ ታገኘው እለህ፡ ብቻውን አይገኝም አስተውለህ ስትመለከተው እንደፀሐይ የመሰለ የብርሃን ጨረር ታይበታለህ፡ እርሱን ወስደህ ቤተመቅደስ ስትሰራ ከመሠረቱ ላይ ቅበረው፡ ሥራው በቶሉ ያልቃል፡፡ የተቸገረ የታመመ መጥቶ ለእግዚአብሔር ስእለት ቢሳል ይፈጸምለታል፡ ያጣም ያገኛል ምሕሳበሰብእ ነው፡፡

347. **ሄንብርተ ምድር** ፡- የሚባል ላይ ነጭ መስሉ ውስጡ ሲወቅሩት በጣም ቀይ ነው፡ ብዙ ግዜ በደጋ አገር ቀይ አፈር ከአለበት ኮረኮንች ቦታ ታገኘው እለህ፡ ይህን ድንጋይ በበላዩ "ሻህኒ ቶላም ሸኒለም ግራህ አግኙ ሰኒታስ ታእስ እብኖዲ" ብለህ ሰባት ጊዜ ጸልይበትና ለመካን ሴት ሆነ ለእንስት ከብት አፈማህፀንዋን እሸበት፡ ለከብት ርቢ ኩብቶች ኮሚጠጡበት ውኃ ውስጥ አስቀምጠው፡ ለእህል በጉተራህ ውስጥ አድርገው ይበረክትልሃል፡ እብነ በረከት ወእብነ ረድኤት የሚባል ይህ ድንጋይ ነው፡፡

348. **ሔብዐ** ፡- የሚባል ያልዘለቀ ቀዳዳ የእለው መልኩ እረንጓዴ ሆኖ ስትወቅረው ቢጫ ይሆናል፡ ለእምጽአ ንዋይ በበላዩ መቀመጥ የተመኙትን መናገር በቀዳዳው የተመኘኸውን

ገንዘብ መውተፍ ነው፡ ለሴት ፍቅር ስሙንና ስሙዋን ጠርቶ በበላዩ መሸናት ነው።

349. **ሁሩብ** ፦ የሚባል ጥቁር አለት መስሉ እንደሰፈፍ ቀዳዳ አለው፡ በደጋ አገር በገወቻ ታገኘው አለህ፡ ሁሩብ ድንጋይ በአለበት ሥፍራው ይሞቃል፡ በባሕር ወይም በምንጭ አጠገብ ካለ ውኃው ይሞቃል፡ ነገር ግን አያቃጥልም፡ አይፋጅም፡ ብርድ ሲሆን ወፎች አሞራዎች ድንጋዩ ባለበት ይሰበሰባሉ፡ ቁር አያገኛቸውም እሱን ስትፈልግ ዓይናማ መስሉ የአልዘለቀ ቀዳዳ የአለው ሆኖ ታገኘው አለህ፡ እሱን ወስደህ በቤትህ ብታስቀምጠው ቤትህ ሁሉ ይሞቃል፡ ሰውነትህ ይፍታታል፡ የብርድ በሽታ ያለው ቢታቀፈው ይለቀዋል፡ ከህመሙ ይፈወሳል።

350. **ሕያሔዐ** ፦ ከአለት ላይ ከዋሻ ላይ መልኩ ተለይቶ ገበታ ወይም ሰሌዳ መስሉ ይታያል፡ በጣም ጥቁር አይደለም፡ የአልቀላ ሉሚ መልክ ያለው ይመስላል፡ ፈልፍለህ አውጥተህ እንደገበታ አድርገህ በሱላይ መስዋእት አዘጋጅ፡ እግዚአብሔር ልብህን ከፍቶ መንፈሳዊ አእምሮ ያሳድርብሃል፡ የእግዚአብሔር ጸጋና ረድኤት አይለየውም፡ ለጽላት ገበታ ይሆንልሃል፡ እንቆሐይና የተባለውን የእንቁ ድንጋይ በአራቱ ማእዘን ላይ ፈልፍለህ አስገባ፡ ባለተአምር ብዙ ምስጢር

የሚገለጽበት ስእሰት የሚፈጸምበት ይሆናል፡ መጽሐፈ አእምሮና መክሥተ ምስጢር ነው።

እግዚአብሔር ለፈጠረው ፍጥረት ሁሉ እንደ እጣ ክፍሉ ወይም እንደየድርሻው እንደኛው ፍጥረት ከሌላው ፍጥረት የሚለያይበት ምክንያት የተፈጥሮ ምስጢር ባህርይ የእሰው ፍጥረቱም ሁሉ በተሰጠው የተፈጥሮ ምስጢር ባህርይ አንደኛው ከሌላው በክብር በኃይል በጥራት በእድገት በቀለም መልክ የተለያየ ሆነ፡ ነገር ግን የተሰጠውን የተፈጥሮ ባህርይ ምስጢርን ለሌላው ለእግዚአብሔር ፍጥረት ለሆነው ለሰው ልጅ እንዲያጋራና አስተውሎ ፈጽሞ እንዲያውቀው እንዲሰለጥንበትም የእግዚአብሔር ፍቃድ ሆነ፡ የእግዚአብሔርም ቸርነትና ለጋሽነት በዚህ ታውቆ ከበረ፡ ተመሰነገም፡ የድንጋዮችንና የእንቁዎችን የጥበብ መንፈስን ዓይን የእሰው እተኩሮ ይይና ይመልከት፡ ጆሮ የእሰውም አድምጦ ይሰማና ያስተውል፡ አእምሮ ያሰውም መርምሮ ይወቅና ይፈላሰፍ፡ በዚህ የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ምሳሌ እንደሆነ ታውቆ ከበረ።

የጥበብ ሁሉ መሰረትዋና መጀመሪያዋ እግዚአብሔርን አውቆ መፍራትና እግዚአብሔር የአዘዘውን መፈጸም ፍቃዱንም ማድረግ ነው፡ ለዚህ ነው እግዚአብሔር በመልኩ እንደምሳሌው የፈጠረን፡ እግዚአብሔር እንድንሰለጥንባቸው በፈቀደልን ፍጥረቶቹ ላይ የምንፈላሰፍባቸውና የምንመራመርባቸውን ሁሉ የጥፋትን ከቶ ስራ ለመተው ሕይወትንና ብልጽግናን የሚሰጠውን መልካሙን

ሥራ ለመምረጥ የእግዚአብሔር ልጆች እንባል ዘንድ ከእግዚአብሔር የሥልጣን መንፈስ ተሰጥቶናልና እግዚአብሔር ለፈቀደልን ለመልካም ጥበብ ሥራ የተዘጋጀን እንሁን፡ ነቅተንም እንጸልይ፡ ወደፈተና እንዳንገባና እንዳንወድቅ የእግዚአብሔርን መንገድ እንጂ የወልጋዳዎችንና የጠማማዎችን አስተሳሰብና መጥፎ ስራ እንዳንከተል አስተውለን መለየትና መተው አለብን፡ ከከፉዎች ጋር የተባበሩ ሁሉ በክፉ ሥራቸው ጠፍተዋልና፡ እንግዲህ የሐሰተኞችን መምህራንና የከንቱዎችን ትምህርትና ምክር እንዳንቀበል እንዳናደርግም እንዳንጠፋም አስቀድመን መጠንቀቅ ከክፉው ሥራ ሁሉ መራቅ የእኛ ነው፡ እግዚአብሔር እንደምህረቱ ብዛት ይማረን፡ ቸር አባት ጌታ ነውና ሰላሙንና ፍቅሩን እንደቸርነቱ ይለግሰን፡ ጥበቃውም አይለየን፡ እግዚአብሔር አምላካችን ለዘለዓለም ከእኛ ጋር ነውና ስሙ በእኛ ላይ ይንገስ ይከበር ይመስገን፡ አሜን፡ ይሁን።

መሪራስ አማን በላይ

2003

# ስመጽሐፈ ጥበበ ዕንቆ አእባን

## መዝጊያ ቃልፍ

ለምወዳችሁና በእግዚአብሔር ስም መልካም ክብርና ጸጋ ለምመኝላችሁ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት ሁሉ አስተውላችሁ ትመረምሩትና ትተረጉሙት ዘንድ ስለአየሁት ህልም እነግራችሁ አለሁ።

ይህን መጽሐፍ በእግዚአብሔር አብ ፈቃድ በእግዚአብሔር ወልድም ጎላጭነት በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም አነሣሽነትና አስፈጻሚነት ጽፌ ስጨርስ በህልሜ አንድ ቀንዳም ድኩላ ከገደል ውስጥ ወጥቶ እኔ ወደቆምኩበት ተራራ ይመጣል፡ ሊወጋኝ እንደመጣ አወኩና ድንጋይ አንስቼ ልመታው ድንጋይ ስፈልግ አንዲት ድንጋይ ከተራራው ላይ ወጥታ ሳልነካት ተወርውራ ግንባሩን ትመታው አለች፡ እኔም ነፍሱ ሳይወጣ ልባርከው ብዬ ከወደቀበት ሄጄ ቢለዋ ስፈልግ በጣም ተመትቶ ኑሮ ደሙና ፈርሱ በአፉ ወጥቶ አየሁት፡ አሁንም ሳልነካው ቆዳው ተገፎ የሥጋ ብልቶቹ በስነ ሥርአት ተዘጋጅተው አየሁ፡ ግን ከሥጋው የወሰድኩትና የበላሁት ነገር የለም፡ ይህን ልጽፍላችሁ የወደድኩበት ምክንያት ስለ ድንጋይ የጥበብ ምስጢር ጽፌ ስጨርስ ድንጋይ በህልሜ በማየቴ ነው እንጂ እኔም የህልሙ ትርጉም ይሄ ነው ብዬ አልፈታሁትም።

እግዚአብሔር ህልምን እንዲተረጉም የፈቀደለት ሰው ብቻ ያፍታው፡ ምንጊዜም በእግዚአብሔር ፊት ስላለን እራሳችንን

ለእግዚአብሔር እያስገዛን እርስ በእርሳችንም በፍቅር ሰላምታ እየተሰጣጠን እግዚአብሔር በፈቀደልን በጥበብ ጉዳና ለመጓዝና ለመራመድ ያብቃን። ሰልፋችንም ሥርአት የአለው ይሁን፡ በዚህ የእግዚአብሔር ሰራዊት ከመባል ሌላ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናልና ልጆች ከሆን ወራሾቹ ነን፡ ከዚህ የበለጠ የለም፡ እኛ ሁላችን በእግዚአብሔር እንደተወደድን እግዚአብሔርም በእኛ ዘንድ ለዘለዓለም ስሙ ይክበር ይመስገን፡ አሜን።

# ምዕራፍ ፮

ተራ .ቁጥር ተሰጥቶዋቸው የተመዘገቡት የማእድን ድንጋዮችና እንቁዎች አፈሮችም፡

| English | አማሪኛ | Symbol | Amharic number |
|---|---|---|---|
| Actinium | አክቲኒዩም | Ac | 89 |
| Aluminum | አሉሚኒዩም | Al | 13 |
| Americium | አሜሪኪዩም | Am | 95 |
| Antimony | አንቲሞኒ | Sb | 51 |
| Argon | አርጐን | Ar | 18 |
| Arsenic | አርሰኒክ | As | 33 |
| Africanium | አፋር-አፈርንዩም | Af | 111 |
| Astatine | አስታቲን | At | 85 |
| Ethiopinium | ኢትዮጵኒዩም | Et | 112 |
| Einsteninium | ኢንስቲኒዩም | Es | 99 |
| Erbium | ኢርቢዩም | Er | 68 |
| Europium | ኢሮፒዩም | Eu | 63 |
| Iodium | አዩዲየም | In | 49 |
| Iodine | አዩዲን | I | 53 |
| Iridium | አሪዲዩም | Ir | 77 |
| Iron | አይረን | Fe | 26 |
| Osmium | አስሚየም | Os | 76 |
| Oxygen | አክስጂን | O | 8 |
| Uranium | ዩራኒየም | U | 92 |

| English | አማርኛ | Symbol | Amharic number |
|---|---|---|---|
| Neodymium | ኒዮዲሚየም | Nd | 60 |
| Neon | ኒዮን | Ne | 10 |
| Neptunium | ኒፕቱኒየም | Np | 93 |
| Nickel | ኒክል | Ni | 28 |
| Niobium | ኒዮቢየም | Nb | 41 |
| Nitrogen | ናይትሮጂን | N | 7 |
| Nobelium | ኖቤሊዩም | No | 107 |
| Fermium | ፌርሚዩም | Fm | 100 |
| Fluorine | ፍሉሪን | F | 9 |
| Francium | ፍራንሲዩም | Fr | 87 |
| Vanadium | ቫናዲዩም | V | 23 |
| Barium | ባሪዩም | Bv | 56 |
| Berkelium | በርከሊዩም | Bk | 97 |
| Beryllium | በሪሊየም | Be | 4 |
| Bismuth | ቢስሙዝ | Bi | 83 |
| Bohrium | ቦሪዩም | Bh | 107 |
| Boron | ቦሮን | B | 5 |
| Bromine | ብሮሚን | Br | 35 |
| Palladium | ፓላዲዩም | Pd | 46 |
| Phosphorus | ፎስፈረስ | P | 15 |
| Platinum | ፕላቲኒዩም | Pt | 78 |

| English | አማርኛ | Symbol | Amharic number |
|---|---|---|---|
| Polonium | ፖሎኒየም | Po | 84 |
| Potassium | ፖታሲየም | K | 19 |
| Praseodymium | ፕሬስዲሚየም | Pr | 59 |
| Promethium | ፕሮሜቴየም | Pm | 61 |
| protactinium | ፕሮታክትኒየም | Pa | 91 |
| Magnesium | ማግኒዥየም | Mg | 12 |
| Manganese | ማንጋኒዝ | Mn | 25 |
| Meitnerium | ሜይንርየም | Mt | 109 |
| Mendelevium | ሜንዴሌቪየም | Md | 101 |
| Mercury | ሜርኩሪ | My | 80 |
| Molybdenum | ሞሊብዴኒየም | Mo | 42 |
| Radium | ራዲየም | Ra | 88 |
| Radon | ራዶን | Rn | 86 |
| Rhenium | ሬሄኒየም | Re | 75 |
| Rhodium | ሮሆዲየም | Rh | 45 |
| Rubidium | ሩቢዲየም | Rb | 37 |
| Ruthenium | ሩቴኒየም | Ru | 44 |
| Rutherfordium | ሩተርፎርድየም | Rf | 104 |
| Lanthanum | ላንታኒየም | La | 57 |
| Lawrencium | ላውሬንሲየም | Lr | 103 |
| Lead | ሊድ | Pb | 82 |
| Lithium | ሊቲየም | Li | 3 |
| Lutetium | ሉቲቲየም | Lu | 71 |

| English | አማርኛ | Symbol | Atomic number |
|---|---|---|---|
| Darmstadtium | ዳርመስታድቲዩም | Ds | 110 |
| Dubnium | ዱብኒዩም | Db | 105 |
| Dysprosium | ዲስፐሮዚዩም | Dy | 66 |
| Tantalum | ታንታለም | Ta | 73 |
| Technetium | ቴክነቲዩም | Tc | 43 |
| Tellurium | ቴለሪዩም | Te | 52 |
| Terbium | ተርቢዩም | Tb | 65 |
| Thallium | ታሊዩም | Ti | 81 |
| Thorjum | ቶሪዩም | Th | 90 |
| Thulium | ቱሊዩም | Tm | 69 |
| Tin | ቲን | Sn | 50 |
| Titanium | ቲታኒዩም | Ti | 22 |
| Tungsten | ታንግስተን | W | 74 |
| Samarium | ሳምሪየም | Sm | 62 |
| Scandium | ስካንዲዩም | Sc | 21 |
| Seoborgioum | ሰበርጊዩም | Sg | 106 |
| Selenium | ሰለንዩም | Se | 34 |
| Silicon | ሲሊኮን | Si | 14 |
| Silver | ሲልቨር /ብር/ | Ag | 47 |
| Sodium | ሶዲዩም | Na | 11 |
| Strontium | ስትሮንቲዩም | Sr | 38 |
| Sulphur | ሰልፈር | S | 16 |

| English | አማርኛ | Symbol | Amharic number |
|---|---|---|---|
| Cerium | ሲሪየም | Ce | 58 |
| Cesium | ሲሲየም | Cs | 55 |
| Zinc | ዚንክ | Zn | 30 |
| Zirconium | ዚሪኮንየም | Zr | 40 |
| Gadolinium | ጋዶሊየም | Gd | 64 |
| Gallium | ጋሊየም | Ga | 31 |
| Germanium | ጀርማኒየም | Ge | 32 |
| Gold | ጐልድ /ወርቅ/ | Au | 79 |
| Cadmium | ካዲየም | Cd | 48 |
| Calcium | ካልሲየም | Ca | 20 |
| Californium | ካሊፎርኒየም | Cf | 98 |
| Carbon | ካርቦን | C | 6 |
| Chlorine | ክሎሪን | Cl | 17 |
| Chromium | ክሮሚየም | Cr | 24 |
| Cobalt | ኮባልት | Co | 27 |
| Copper | ኮፐር | Cu | 29 |
| Curium | ኩሪየም | Cm | 96 |
| Hafnium | ሀፍኒየም | Hf | 72 |
| Hassium | ሀሲየም | Hs | 108 |
| Helium | ሂሊየም | He | 2 |
| Holmium | ሆልሚየም | Ho | 67 |
| Hydrogen | ሃይድሮጅን | H | 1 |


FLUORITE ON QUARTZ
SCAPOLITE
BENTONITE
HALLOYSITE
ILLITE
BROWN NONTRONITE
GREEN NONTRONITE
CALCITE
WILLEMITE AND CALCITE
GYPSUM
SODALITE


MARBLE BRECCIA
TYPES OF MARBLE
GRAY MARBLE
OLIVINE MARBLE
GREEN MARBLE
POLISHED SLAB OF BLUE MARBLE
MALACHITE HABITS
Malachite comes in a variety of habits, all of which provide beautiful and interesting patterns when cut and polished.
Radiating crystals
Growth layering
STALACTITIC
STALACTITIC CROSS SECTION
FIBROUS
MALACHITE WITH AZURITE
GRANITE VARIETIES
White orthoclase feldspar
Gray quartz
Feldspar phenocryst
WHITE GRANITE
PORPHYRITIC GRANITE
ORBICULAR GRANITE
GRAPHIC GRANITE
HORNBLENDE GRANITE

# CLASSIFYING MINERALS

Mineralogists classify minerals according to their chemical composition (see pp. 88–89). Shown below are the major chemical groups, with an example of each. Within chemical groups, minerals are further classified into subgroups, taking their name from their most characteristic mineral. For example, gold, silver, platinum, and copper are all members of the native elements chemical group, but they are also classified as part of the gold group of minerals, because they have an identical arrangement of their atoms.







OCTAHEDRAL GOLD CRYSTAL

**GOLD GROUP**
*Metals of the gold group all have a cubic arrangement of close-packed atoms with bonds in all directions. The atoms stack up in a sequence of layers, with the atoms of one layer fitting into the hollows in the layers above and below, so that each atom has 12 neighbors.*



COPPER



CHALCOCITE



RUBY

**OXIDES**
*When oxygen combines with a metal or semimetal, an oxide mineral is formed. Aluminum oxide is corundum, the red variety of which is called ruby.*

**NATIVE ELEMENTS**
*Native elements are minerals formed of a single chemical element. They include metals such as gold and copper and nonmetals such as sulfur and carbon.*

**SULFIDES**
*The sulfides are formed when a metal or semimetal combines with sulfur. In chalcocite the metal element is copper.*

**HALIDES**
*A halogen element (chlorine, bromine, fluorine, or iodine) combined with a metal or semimetal makes a halide. Sylvite is a compound of chlorine and potassium.*



SYLVITE

**HYDROXIDES**
*Hydroxide minerals contain a hydroxyl (hydrogen and oxygen) radical combined with a metallic element (magnesium in the case of brucite).*



BRUCITE

SMITHSONITE



**ARSENATES, PHOSPHATES, AND VANADATES**
*In these minerals a radical of oxygen and either arsenic, phosphorus, or vanadium combines with a metal or semimetal. Apatite is a phosphate.*



APATITE

COLEMANITE



**BORATES AND NITRATES**
*These minerals contain, respectively, radicals of boron and oxygen, and of nitrogen and oxygen. Colemanite is a borate in which boron and oxygen combine with calcium and water.*

**CARBONATES**
*The carbonate radical, consisting of carbon and oxygen, combines with a metal or semimetal to form carbonate minerals. In the case of smithsonite, the metal is zinc.*

AMETHYST



AMBER



**ORGANIC MINERALS**
*Organic compounds with well-defined crystal structures are classified as minerals. Amber, however, which originates as a resin, is classified as a mineraloid.*



CELESTINE

**SULFATES, CHROMATES, TUNGSTATES, AND MOLYBDATES**
*Sulfur, molybdenum, chromium, or tungsten form a radical with oxygen that combines with a metal or semimetal. Celestite is a sulfate.*

**SILICATES**
*In this group, silicon and oxygen form a tetrahedral silica radical that combines with various metals or semimetals. Silica also occurs on its own as quartz. Amethyst is a variety of quartz.*


DULL
A dull luster, such as that of this sample of hematite, is nonreflective, but not as granular as earthy luster.
EARTHY


"What do you not drive
human hearts into,
cursed craving for gold!"
VIRGIL, AENEID
HABITS OF GOLD
Gold occurs in several habits: as crystalline masses, as flat plates, and as nuggets and grains recovered from stream and river placers.
GOLD CRYSTALS
FLAT GOLD PLATES
PROPERTIES
GROUP
CRYSTAL SYSTEM
COMPOSITION
COLOR
FORM/HABIT
HARDNESS
CLEAVAGE
FRACTURE
LUSTER
STREAK
SPECIFIC GRAVITY
TRANSPARENCY
Actual size of nugget
LARGE GOLD NUGGET IN SMITHSONIAN COLLECTION




**RUBY CRYSTALS**
*Ruskin's ruby (far left) was donated to the Natural History Museum, London, by John Ruskin in 1887. It is about 162 carats. The central crystal, embedded in calcite, is from the Mogok region in Myanmar. The crystal below is part of the Smithsonian Collection.*

ለቆስት ለተወርዋ፤
የታይታኒየም-Titanium

## ለሰው ልጅ ቆዳ ቀለም

ነጭ ዳማ /ለነጮች/

ቀይ ዳማ /ለአረቦች/

ብጫ ዳማ /ለእስያዎች/

ጥቁር ዳማ /ለአፍሪካዎች/

---

## የሰው መልክ

ዳማ ||

ጠይም ||

ጥቁር || አረር

ቢጫ || ነጮ

ቀይ ||

ዳዊት ቀይ ዓይኑም የተዋበ መልኩም ያማረ እንደ እናቱ ወገኖች ቀይ ዳማ ነበር። መ/ሳሙ/ቀ. 16፥12

## ለወንድ ለተባእት

አረንጉዋዴ ቀለም

ቀይ >>

ቢጫ >>

ቡና >>

ሰማያዊ >>

## ለሴት ለእንስት

ሮዝ ቀለም

ሐምራዊ ነጽ ቀ/

ብርቱካን ቀ/

ጥቁር

ነጭ

| | |
|---|---|
| ሐመር >> | ቤዥ |
| ዋርዳ /ጥቁር ሰማያዊ/ | የወይን ጠጅ /ልብሰ ማርያም/ |
| ነጫቴ >> | ቦረቅ |
| ቡላ >> | /ጉራቻ/ ጉራቴ |
| ከፋይ >> | ሳፍራዊ ኤፍራን |

## ሁለገብ ቅጽል ቀለም

| | |
|---|---|
| ሰራን /ሰራ/ | ገብስማ |
| ወሰራን | ቀቅማ |
| አፈርማ | ፈንዛ ፈንዛማ |
| ዳልቻ | ጉራቻ |
| ወርቅማ | ብርማ |
| ግራጫ /ጃርት/ | ነብርማ - ቦራ - ቡራቡሬ |